አሃድ
ሳምንታዊ መፅሔት
ቅፅ. 1 - ቁ.13 ታህሳስ 2011

## ከውስጥ ገፆች በከፊል



ገፅ 3

ኦነግ ራሱን ወደ ማጥፋት ጎዳና?



ገፅ 6

ያልተቀደሰው የኦነግና የህውሃት ጋብቻ እና የቲም ለማ ስጋት



ገፅ 9

‹‹አዲስ የፖለቲካ ፉዐዩ እንግበናል››

አሃድ
ሳምንታዊ መፅሔት

ምርትና አገልግሎትዎን ያስተዋውቁ!

0913582164

ይደውሉ!

## Editorial
## የአዘጋጅ መልእክት

# ሱቅ በደረቴ ፓርቲዎች በቃችሁን

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ለለዉጥ ያደረጉት ጠንካራ ትግልና እንቅስቃሴ ይህ ነዉ ተብሎ ከፍ ባለ ድምፀት የሚነገርለት አይደለም፡፡ ፓርቲዎቻችን በጠንካራ መሰረት ላይ ቆመዉ የህዝብን ቀልብና ፍላጎት በሚገዛ መልኩ የፖለቲካ ስራ ሲሰሩም አይስተዋሉም፡፡ ምናልባትም በፓርቲ ፖለቲካ የትግል ታሪክ ዉስጥ የ1997 ዓ.ም ቅንጅት ነዉ በአዎንታ ሊጠቀስ የሚችለዉ፡፡

ቅንጅት በዚያ ጊዜ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ የህዝብን ቀልብ ገዝቶ ኢህአዴግን ሊያንገዳግድ የቻለዉ አራት ፓርቲዎች ተቀናጅተዉ በአንድነት ስለሰሩ ነዉ እንጂ አራቱ የፖለቲካ ድርጅቶች በተናጠል ቢንቀሳቀሱ ኖሮ ኢህአዴግን የሚገዳደሩበት አቅም መፍጠር አይችሉም ነበር፡፡

አሁንም ጠቅላይ ሚንስተር ዶ/ር አብይ አህመድ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ደጋግመዉ የሚለግሱት ምክር ‹‹ ተሰባሰቡ፣አንድ ሁኑ›› የሚል ነዉ፡፡ የህብረት፣የቅንጅት የአንድነት ጉዳይ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ወሳኝ ጉዳይ ነዉ፡፡

ስማንያ ፓርቲ ሀገር አያቀናም፡፡ የፓርቲ ጋጋታ ዴሞክራሲን አያረጋግጥም፡፡ ሱቅ በደረቴ መሳያ፣ መሀተማቸዉን በኪሳቸዉ ይዘዉ የሚዞሩ ፓርቲዎች ከፓርቲ መዝገብ ዉስጥ መፋቅ አለባቸዉ፡፡ በሀገራችን አሁን ላይ ፓርቲ ተብለዉ የሚነገርላቸዉ አብዛኛዎቹ ከግሮሰሪ ያነሰ ቁመና ነዉ ያለቸዉ፡፡ ግሮሰሪ እንኳን ደንበኞች አሉት፡፡ ብዙ ነገር ይወራበታል፡፡ ግሮሰሪ ዉስጥ የሀሳብ ልውውጥ አለ፡፡ የሀገራችን ብዙዎች ፓርቲ ተብዬዎች ግን ለዚህ አልታደሉም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ፓርቲ ተብዬዎች ቢኖሩም አይጠቅሙም፡፡ ባይኖሩም አይጎዱም፡፡ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የይስሙላ ፓርቲዎች ሳይሆኑ ትክክለኛ የፓርቲ ቁመና፣ አላማ እና ግብን አስቀምጠዉ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችን ነዉ፡፡

ፕሮግራምና እስትራቴጂ ነድፈዉ የፖለቲካን ስራ የሙሉ ጊዜ ስራቸዉ የሚያደርጉ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሀገራችን ትፈልጋለች፡፡ ለኢትዮጵያ የሚበጃት የፓርቲ ብዛት ሳይሆን ጥራት ያለዉ ዉስን ፓርቲዎችን ነዉ፡፡ አዲሱ የምርጫ ቦርድ አወቃቀርም ለዚህ ጉዳይ ቦታ እንዲሰጠዉ ማሳሰብ እንወዳለን፡፡

በዚህ አጋጣሚ አርበኞች ግንቦት ሰባት ንቅናቄ አሁን ላይ እያደረገ ያለዉ እንቅስቃሴዉ የሚበረታታ ነዉ፡፡ ለሰላማዊ ትግል ወደ ሀገር ቤት ከገባበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ስራዎችን እየሰራ ነዉ፡፡ ህዝብ መሃል ገብቶ ስለ አላማ እና እቅዱ ሰፊ የማስተዋወቂያ መንገዶችን እያዘጋጀ ነዉ፡፡ ከተለያዩ ፓርቲዎች ጋር በአብሮነት ለመንቀሳቀስም ዝግጅት ጀምሯል፡፡ ይህ አይነቱ እንቅስቃሴ ሊበረታታ ይገባል፡፡ ሌሎችም ፓርቲዎች ራሳቸዉን ቢፈትሹ መልካም ነዉ፡፡ በተግባር የሌለን ፓርቲ ፣ፓርቲ አለን ብለዉ ባይመፃደቁ ጥሩ ነዉ፡፡

አድል የህትመትና የማስታወቂያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በንግድና ኢንዱስትሪ የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር የንግድ ፈቃድ ቁጥር፡- YK/AA/14/672/770192/2010 ተመዝግቦ በየሳምንቱ የምትታተም በፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የምታተኩር ሳምንታዊ መጽሔት መስከረም 2011 ተቋቋመ

**ማኔጅንግ ዳይሬክተር**
ፋጡማ ኑርዬ

**ዋና አዘጋጅ**
ዮናስ ወ/ሰንበት
ልደታ ክ/ከ ወረዳ 10
0913914929

**ዋና ስራ አስኪያጅ**
ጀማል መሀመድ
0913582164

**አምደኞች**
ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም
ዶ/ር ዘላለም ተክሉ
ረ/ፕሮፌሰር ዳንኤል መኮንን
ዶ/ር ፍቃዱ በቀለ
ዶ/ር መሀመድ አሊ
ያሬድ ሀ/ማርያም
ታምራት ታረቀኝ
ሳዲቅ አህመድ
መልካም ሞላ
ድንቃየሁ መኮንን
ምስጋናው ታደሰ

**ኮምፒውተር ጽሁፍ**
ቤዛዊት ወዳጆ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
የካ ክ/ከ ወረዳ 11 የቤት ቁ. አዲስ
0913914929


**አታሚ**
ሰላማዊት ማተሚያ ቤት
አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 262
ስልክ 0966833177

SIRAK Advertising & Printing
Cover & Layout Design
+251- 911 50 33 22

በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ማንኛውም ፅሁፎች ማተሚያ ቤቱን አይመለከቱም

# ኦነግ ራሱን በማጥፋት ጎዳና?

የኢትዮጵያ ፖለቲካ በአስገራሚ ትዕይንቶች እንደተሞላ ቀጥሏል፡፡ በዶ/ር አብይ ዘመን ተስፋ ሰጪ የለዉጥ እንቅስቃሴዎች እየተስተዋሉ ቢሆንም ስጋት የሚያጭሩ እና ተስፋ የሚያስቆርጡ ሁነቶችም በኢትዮጵያ መሬት ላይ እየታዩ ነዉ፡፡



ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት የተባረረዉ ህወሃት የሸንፈት ሂሳቡን ለማወራረድ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ግጭቶችን እያደራጀና በገንዘቡ ስፖንሰር እያደረገ የማተራመስ ስትራቴጂዉን ቀጥሎበታል፡፡ ለዚህ እስትራቴጂዉ ደግሞ ኦነግ የተሰኘዉ ሀይል ጥሩ መሳሪያ ሆኖለታል፡፡ ባለፈዉ ሳምንት እንኳን በጉጂ ዞን ወደ ሻኪሶ ንግድ ባንክ ያቀኑ የነበሩ ሁለት ተሸከርካሪዎች በኦነግ ታጣቂዎች በጥይት ተመትተዉ ሶስት ሰዎች ተገድለዋል፡፡ እነዚህ ታጣቂዎች አላማቸዉ ወደ ባንክ የሚገባዉን ገንዘብ መዝረፍ ነበር፡፡

ይሁንና በአንድ ሾፌር ብልጠት ስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ከታጣቂዎቹ እጅ እንዳይገባ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል የኦነግ ታጣቂዎች በአማሮ ኬሎ አካባቢ ላይ ተንቀሳቅሰዉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ከብቶችን እንደዘረፉና የቡና ማሳዎችን እንዳቃጠሉ ተነግሯል፡፡ ይሄ የአንድ ቀን ክስተት ሲሆን የኦነግ ታጣቂ የተባሉት ሀይሎች በወለጋና በተለያዩ ክፍሎች ለወራት ሰዉ ሲገድሉ ፣ንብረት ሲያወድሙ፣ ሲዘርፉ ቆይተዋል፡፡ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ወደ ሀገር ቤት ገብቻለሁ ያለዉ ኦነግ በማን አለብኝነት እየተንቀሳቀሰ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ስርዓት አልበኝነትን እያነገሰ ሳለ መንግስት ከዝምታና ከትዕግስት ባለፈ ተግሳፅም ሆነ ህግና ስርዓትን የማስከበር እርምጃ ሲወስድ አለመስተዋሉም አነጋጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ሲጀመር የአብይ አህመድ (ዶ/ር) መንግስት ኦነግ ወደ ሰላማዊ ትግል መጥቻለሁ ብሎ ወደ ሀገር ቤት በገባበት መንገድ ላይ ክፍተት ሳይፈጥር እንዳልቀረ ይነገራል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ኦነግ ሰላማዊ ትግልን እና መሳሪያ አንግቶ መንቀሳቀስን ባልደፈረ ነበር እየተባለም ነዉ፡፡ ኦቦ ዳወድ ኢብሳ ‹‹ከመንግስት ጋር የነበረን ስምምነት ትጥቅን ስለመፍታት አይመለከትም›› ብለዉ ሲናገሩ የአብይ አስተዳደር ደግሞ ‹‹በአንድ ሀገር ሁለት ሰራዊት የለም›› ባይ ነዉ፡፡

ሁለቱ አካላት በዚህ እሰጣገባ ዉስጥ ከከረሙ በኃላ መንግስት ባለፈዉ ሳምንት ኦነግን ከዚህ በኃላ እንደማይታገሰዉ በከባዱ ያስጠነቀቀበትና እርምጃ እንዲወሰድ ያዘዘበትን መግለጫ አዉጥቷል፡፡ አቶ ዳወድ ኢብሳም ሰራዊታቸዉ እራሱን እንዲከላከል (እንዲዋጋ) የአፀፋ ትዕዛዝ ሰጥተዋል፡፡ የሚገርመዉ ነገር ሁለቱ አካላት ይህንን ትዕዛዛቸዉን ያስተላለፉት አዲስ አበባ ላይ (ያዉም በአራት ኪሎ በቅርብ እርቀት ላይ) ተቀምጠዉ ነዉ፡፡ ምናልባትም ይህ ነገራቸዉ በአለም ላይ ባልተለመደ መልኩ በአንድ ከተማ ላይ ሁለት አካላት ተቀምጠዉ የጦርነት ትዕዛዝ የሰጡበት አጋጣሚ ያደርገዋል እየተባለ ነዉ፡፡

የዶ/ር አብይ መንግስት በህጋዊ መንገድ ሀገር እያስተዳደረ ያለ አካል እንደመሆኑ መጠን የሀገርና የህዝብን ሰላም እና ደህንነት ማስከበር ዉዴታዉ ብቻ ሳይሆን ግዴታዉ በመሆኑ ያንን ትዕዛዝ ማዉጣቱ ተገቢ ነዉ ሲሉ ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ በአንፃሩ አቶ ዳወድ ኢብሳ ኦነግ ወደ ሀገር ቤት የመጣዉ ለሰላማዊ ትግል መሆኑ እየታወቀ ‹‹ ጦሬ ምንም ቢያደርግ ማንም አይንካብኝ›› ፣ከተነካም እራሱን እንዲከላከል አዝዤዋለሁ›› ማለታቸዉ ብዙም የማያስኬድ ተደርጓል፡፡

ስማቸዉ እንዲገለፅ ያልፈለጉ አንድ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅት ከፍተኛ አመራር ‹‹ አቶ ዳወድ ጦራቸዉን ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ ያስገቡት (ያስገቡት ጦር ካለ) በአስመራና በኬኒያ በኩል ወደፊት አልገፋ ያለዉ ትግላቸዉን መንግስት ባመቻቸላቸዉ መንገድ አዲስ አበባ ላይ ተቀምጠዉ ትዕዛዝ በመስጠት ሊያቀላጥፉት ነዉ እንዴ? ሲሉ ለአሃድ

ወደ ገፅ 31 ዞሯል



ዶ/ር ዘላለም ተክሉ

# ዶ/ር አብይ ለብቁ መሪነት ይመጥናሉን ?



ዶ/ር አብይ አህመድ በጠቅላይ ሚኒስተርነታቸው እያሳዩት ያሉትን አስተዋይነት፣ አዋቂነት፣ ለውጥ ፈላጊነት፣ አንደበተ ርቱእነት፣ ሩህሩህነትና ባብዛኛው ህዝባችን ያላቸው ተወዳጅነትን ስንመለከት ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ "ብቁ መሪ" እንዳገነች ያስረዳናል።

ዶ/ር አብይ እያስመዘገቡ ያሉት ለውጦች አበረታች ቢሆኑም ሌሎች አንገብጋቢ የሆኑ የፖለቲካ እንቅፋቶችን በማስወገድ ረገድ የሚያሳዩት ከመጠን ያለፈ ገራገርነት አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱንም መግለጽ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ አሳምኖናል።

ብዙ ኢትዮጵያውያንን እያሰጉ ካሉት አንገብጋቢ ጉዳዮች ውስጥ፣

- በህዝባችን ላይ ኢሰብአዊ የመብት ገፈፋና የሃገር ሃብት ዝርፊያ ያካሄዱ የኢሃአዴግ ቁንጮ መሪዎችን ወደ ህግ ለማቅረብ በሚደረገው ሂደት ከህወሃት መሪዎች በኩል እየተደርጉ ያሉትን ተቃውሞዎችና መስተጓጎሎች ለማስቆም ብዙ መለሳለስ እያሳዩ መገኘት፣

- በፍጥነት እየተካሄደ ያለውን የለውጡጥ ሂደት ለማደናቀፍ ከህወሃት አፍራሽ ቡድን ጋር በመተባበር የህዝብ አለመረጋጋት፣ ግድያና መፈናቀል እያባባሱ ባሉት የኦነግ አመራሮች ላይ ቁርጠኛ እርምጃ ለመውሰድ ዘገምተኛ መሆን ዋነኞቹ ናቸው።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ ማስተካከያ አርምጃዎች አለመውሰድ የተጀመረውን አበረታች ለውጥ እንዳያስተጓጉለው ብዙዎችን እያሳሳበ የመጣ ጉዳይ ሆኗል።

ይህ ገራገርነታቸውና መለሳለሳቸው በብቁ መሪነታቸው ላይ የሚጋረድ ጥላ ይሆን ወይ ብሎ በመገመትም በዚህ ጽሁፍ ለመመርመርና መፍትሄ ሃሳብ ለመጠቁም ተሞክሯል።

ለመሆን የብቁ መሪ ዋና ዋና ባህርያቶች ምን ምን ናቸው?

ሮቢንስ፣ ኮልተርና ዲቼንዞ በጻፉት Fundamentals of Management የአካዳሚክ መጽሃፍ አተረጓጎም መሰረት፡

"ብቁ መሪ ማለት የተሰጠውን የማስተደደር ስልጣን በመጠቀም የብዙ ቡድኖችን ወይም ህዝቦችን ሃሳብ በበጎ መልኩ መቀየር የሚችልና ተጽኖ ፈጣሪ የሆነ ግለሰብ ማለት ነው"።

ብቁና ውጤታማ የሆነ መሪ የሚከተሉትን ስምንት ባህርያት እንደሚያሟላም ይሄው መጽሃፍ ያስረዳል፡

- ተነሳሽነት (Drive) — ብቁና ውጤታማ መሪ ያቀዳቸውን አላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ተነሳሽነት ያለው፣ የጀመራቸውን ስራዎች ሳያሳካ ደከመኝ የማይልና ያለውን ሃይል ሁሉ የሚጠቀም ብርቱ ግለሰብ ነው፣

- ለመምራት ፍላጎት ያለው (Desire to Lead) — ብቁና ውጤታማ የሆነ መሪ ጠንካራ የሆነ የመምራትና ተጽኖ የመፍጠር ፍላጎት አለው።

- ታማኝነትና የሞራል ብቃት (Trust & Integrity) — ብቁ መሪ ሃቀኛ በመሆን የተከታዮቹን ሙሉ እምነት ያገኛል እንዲሁም ቃል የገባቸውን ሁሉ ስራዎች ተግባራዊ በማድረግ የሞራሉ ብቃቱን ያረጋገጠ ነው።

- በራስ መተማመን (Self Confidence) — ትክክለኛ መሪ ሊያሳካ የተነሳሳባቸውን አላማዎችና የወሰናቸው ውሳኔዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በሙሉ በራስ መተማመን ካረገጠጥ ብዙ ተከታዮች ይኖሩታል።

- የአእምሮ ብቃት (Intelligence) — ብቁ መሪ ብዙ መረጃዎችን ባጭር ጊዜ በመሰብሰብ፣በመተንተንና በመተርጎም ችግሮችን የመፍታትና መፍትሄ እርምጃዎችን የመውሰድ የአእምሮ ብቃት ያለው መሆን አለበት።

- ከስራው ጋር ተያያዥነት እውቀት (Job Related Knowledge) — ውጤታማ የሆነ መሪ ስለሚመራው ድርጅት ወይም ሃገር ጥልቅ የሆነ እውቀት ያለውና ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች ጥቅምና ጉዳት አስቀድሞ ግንዛቤ ያለው መሆን አለበት።

- በጣም ተግባቢ የሆነ (Extraversion) — እውነተኛ መሪ ህዝብ ወዳድ፣ ተግባቢ፣ ተጫዋችና በማህበራዊ ኑሮዎች ውስጥ ተሳታፊ መሆን አለበት።

- ጥፋትኝነቱን አምኖ የሚቀበል (Proneness to Guilt) — ብቁ መሪ ጥፋቱን አምኖ የሚቀበል ነው፣ ምክያቱም ለጠፋው ጥፋት ሃላፊነቱን ሲወስድ በተከታዮቹ ታማኝነቱ ይጨምራል ሌሎችም የሱን አርአያ እንዲከተሉ ያደርጋል።

ዶ/ር አብይ የብቁ መሪነትን ትርጉምና ባህርያቶች ምን ያህል አሟልተዋል?

ተነሳሽነትን በተመለከት ዶ/ር አብይ በበዓለ ሲመታቸው ዕለት ቃለ መሃላ ሲፈጽሙ ቃል የገቧቸውን ፖለቲካዊና ህጋዊ ማሻሻዎችና ለውጦች ለመፈጸም ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ጠንካራ ግለሰብ መሆናቸውን አስመስክረዋል፡፡ በዛ ንግግራቸው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን በነጻነት እንዲገልጽ ይደረጋል ብለዋል፣ በውጭ ያሉት የገዢ ፓርቲ ተፎካካሪዎች ሁሉም ወደ ሃገር ገብተው በሰላማዊ መንገድ እንዲታገሉ ጋብዘዋል፣ ከኤርትራ ጋር ያለውን የብዙ አመታት ፍጥጫ እንደሚፈቱ ቃል ገብተው ነበር፡፡ በእዚች ስምንት ወራት ውስጥ ቃል የገቧቸውን ብዙዎች ግቦች ሁሉ እንዲሳኩ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሌት ተቀን ስራ የሚሰሩ ብርቱና ብቁ መሪ መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ አብዛኛውን ቃል የገቧቸውን ተግባራት ወይ ፈጽመዋል ወይ ደግሞ ለቀጣይ አፈጻጸም መስመር አስይዘዋቸዋል፡፡

ዶ/ር አብይ ከፍተኛ የሆነ የመምራት ፍላጎት አላቸው፡፡ ከራሳቸው አንደበት እንደሰማነው ከልጅነቱ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ መሪ በመሆን ለውጥ ለማምጣት እንደሚፈልጉ ይገልጹ እንደነበር ይታወቃል፡፡ አሁን እንደምናየውም ለአስርት ዓመታት የዘለቀውን የኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት በቀዳሚነት አመራሩን እየሰጡ ይገኛሉ፣ በየክልሎቹ መካከል የተከሰተውን የብሄር ብሄረሳቦች እርስ በርስ ግጭት ለምፍታት፣ በሱዳንና ደቡብ ሱዳን መካከል የተፈጠረውን ግጭት ለመፍታት፣ የመንን እያፈራረሱ ያሉትን ተዋጊ ቦድኖች ለማስታረቅ ያሳዩት ተነሳሽነት፣ በየውጭ ሃገራቱ የታሰሩትን ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በማስፈታት ረገድ፣ በሙስሊሙ መጅሊስና መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ መካከል ያለውን ችግር በመፍታት ሂደት፣ በስደተኛውና በሃገር ውስጥ የኦርቶዶክስ ሲኖዶሶች መካከል ያለውን ግጭት ለመፍታት፣ የኢትዮጵያንና የኤርትራ ግጭት ለመፍታት ሁሉ የመሪነቱን ሚና እየተጫወቱ ያሉት ዶ/ር አብይ ናቸው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህዝባችን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳዮች ረገድ ለአመታቶች ያጋጠመውን ችግሮች ሁሉ ተረድተው፣ ኢህአዴግ ለነዚህ ችግሮች ሁሉ ተጠያቂ መሆኑን አምነው፣ ችግሮቹን ለመፍታት ቃል የገቡ በመሆኑና የተወሰኑትን መሰረታዊ ችግሮች በአጭር ጊዜ የፈቱና እየፈቱ ያሉ በመሆናቸው የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ እምነት አትርፈዋል፡፡

ዶ/ር አብይ በሚያደርጉት ንግግርም ሆነ የለውጥ እርምጃዎች የሚወስዱት ከፍተኛ የራስ መተማመን በተሞላበት መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የኢትዮ-ኤርትራ ድምበር ኮሚሽን ባድሜና ሌሎች አካባቢዎችን ወደኤርትራ እንዲካለሉ የወሰኑት ውሳኔ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለማስፈጸም መነሳታቸው ሲገልጹ ከትግራይ ክልልና ህወሃት ተቃውሞ ደርሶባቸው ነበር፡፡ ባድመ ወደ ኤርትራ እንድትካለል የተስማሙት እሳቸው ሳይሆኑ አቶ መለስ መሆናቸውንና እሳቸው ያንን ውሳኔ በአገሮቹ መካከል ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ዘላቂ ልማት ሊያመጣ እንደሚችል በመተማመን ለማስፈጸም መነሳታቸውን በከፍተኛ ራስ መተማመን ሲያስረዱ አብዛኛው የፓርላማ አባል እንዲሁም መላው ኢትዮጵያዊ በደስታ ነው የተቀበላቸው፡፡

ዶ/ር አብይ ከፍተኛ የአእምሮ ብቃትና ከስራቸው ጋር ተያያዥነት ያለው እውቀት የተጎናጸፉ ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸው፡፡ በአካዳሚ እውቀት በኮምፒዩተር ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ቢዝነስ አድሚኒስትርሬሽንና፣ ፖሊቲካል ሳይንስ ትምህርቶች ከባችለር እስከ ዶክተሬት ዲግሪዎች የተጎናጸፉ ሲሆን፡፡ በስራ ልምድም በመካላከያ ከተራ ውትድርና እስከ ኮለኔልነት ማእረግ የደረሱ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ መረጃ መረብ ደህንነት (INSA) እና ሌሎች የመንግስት ተቋማት በአመራርነት ከፍተኛ ክህሎትና ልምድ ያካበቱ ባለሙያ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስለ ኢትዮጵያና የዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚ ታሪካዊና ወቅታዊ እውንታዎች በንባብ ራሳቸውን ብቁ ያደረጉ መሪ መሆናቸውን በተለያዩ መድረኮች ካደረጓቸው ንግግሮች መረዳት ይቻላል፡፡ የአገራችንን ባህልና ወግ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆናቸውንም አቀላጥፈው ከሚናገሩት ኦሮምኛ፣ አማርኛና ትግርኛ ቋንቋዎችና ወጎች መደምደም ይቻላል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የዳበረ እውቀት፣ ልምድና መልካም የግል ባህርያት በስምንት ወራት ውስጥ ካስመዘገቡት አበረታች ለውጦች ጋር ሲደመር ዶ/ር አብይን ብቁ መሪ ያደርጓቸዋል፡፡

ዶ/ር አብይ ህዝብ ወዳጅ፣ ተግባቢና በማህበራዊ ኑሮዎች ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን በዚች አጭር ጊዜ ውስጥ አስመስክሯል፡፡ ሰኔ 23, 2018 እ.ኤ.አ በመስቀል አደባባይ ሰልፉ ሲካሄድ በፈነዳው ቦምብ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ሆስፒታል ድረስ ተመላልሰው በመጠየቅና ደማቸውን በመስጠት እንዲሁም በሟቾቹ ቤተሰቦች ለቅሶ ላይ በመድረስ ከተራው ህዝብ ጋር ያላቸውን ፍቅርና ማህበራዊ ትስስር አሳይተዋል፡፡ በቼሻየር ሆም ሂደው ችግረኞችን ምሳ በማብላት፣ ለአካለ ስንኩሎች ተሽከርካሪ ወንበር በመለገስ፣ በገጠርና በከተማ ባሉ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጋር ውይይት በማድረግና ሌሎች ማህበራዊ ስራዎችን በመስራት እታች ካለው ህዝብ ጋር ያላቸውን ከፍተኛ ቀርቤታ አሳይተዋል፡፡

ዶ/ር አብይ ኢህአዴግ በ27 አመታት ውስጥ በህዝቡ ላይ ለፈጸማቸው በደሎችና ጥፋቶች ሁሉ ሃላፊነት በመውሰድ የአመራር ብቃታቸውን አስመስክረዋል፡፡ በተለይ ከፓርላማ አባላት "አሸባሪ እስረኞችን ለምን ይፈታሉ?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ "እስረኞችን በጨለማና ቀዝቃዛ ቤት ውስጥ አስሮ በማሳቃየት፣ በመግረፍ እና አካል በማጉደል አሸባሪዎች እኛ እንጂ እስረኞቹ አይደሉም" በማለት እቅጩን ነግረው መንግስት ሃላፊነቱን እንደሚወስድ የስጡት ምላሽ ምን ያህል ብቁና ታማኝ መሪ እንደሆኑ አረጋግጧል፡፡ ስህተትን ማመንናቸውና ሃላፊነቱን መውሰዳቸው በህዝባቸው መካከል ከፍተኛ ታማኝነት አጎናጽፏቸዋል፡፡

በብቁ መሪዎች ላይ የሚታዩ ድክመቶች ምንድን ናቸው?

ከተለያዩ የስራ አመራር (Management and Leadership) ምርምር ጽሁፎች መረዳት እንደተቻለው፣ ብቁ መሪዎችን ከሚፈታተኑ ችግሮች ውስጥ የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡

1) ሁሉንም የሚያስደስት እርምጃ መውሰድ፡

አንዳንድ መሪዎች ለሁሉም ወገን፣ ህዝብ፣ደጋፊና ተፎካካሪ የሚስማማ እርምጃ በመውሰድ ተሰሚነትን፣ ተቀባይነትን ለማግኘት ይሞክራሉ፡፡ ይህ ጠቃሚ የአመራር ባህርይ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ይህን ለማድረግ ሲሞከር የስራ ውጤት ማግኘቱ ይረሳና ሰዎችን ማስደሰት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ አካሄድ በረጅም ጊዜ የታቀዱ ትልሞች ግባቸውን እንዳይመቱ ምክንያት ይሆናል፡፡

2) በተወሰኑ ሰዎች፣ ስትራቴጂዎችና ታክቲኮች ላይ ብቻ ከመጠን ያለፈ መተማመን (Over confidence)

አንዳንድ መሪዎች ከውጤታማነት ለታማኝነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙም ውጤታማ ላልሆኑ ግለሰቦች አመራር ሙሉ እምነት ሰጥተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ይዘው በተነሱት ስትራቴጂና ታክቲኮች በመተማመን ለሌሎች አማራጭ መንገዶች ቦታ አይሰጡም፡፡ ይህ አካሄድ የህዝብ ችግሮችን ውጤታማ በሆነና ጥራት ባለው መንገድ መፍታት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

3) ቁርተኛ የሆኑ ውሳኔዎች ለመውሰድ መዳዳት

አንዳንድ አመራሮች የተለያዩ ተግባራትን ለመፈጸም ያቅዳሉ፣ ይዘጋጃሉ ነገር ግን ተግባራቱን ለማስፈጸም ውሳኔ በመስጠት ላይ ድክመት ያሳያሉ፡፡ ውሳኔ በመፈጸም ሂደት በራስ የመተማመን ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ውሳኔያቸው አይሳካ ይሆን፣ ከበታች ያሉት ሃላፊዎች አይቀበሉት ይሆን፣ ህዝቡ ይቃወመው ይሆን፣ የተወሰኑ ቡድኖች ወይም ተጻራሪዎቻቸው እንደ ድክመት ወስደው ለጥቃት ይጠቀሙበት ይሆን ብለው ይፈራሉ፡፡ በዛም ምክንያት እርምጃ ለመውስድ ይወላውላሉ፡፡ ጊዜ ካለፈ በኋላ እርምጃዎቹን ቢወስዱም ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ፡፡

በኔ ግላዊ አስተያየት ከላይ የቀረቡት የመሪዎች ድክመቶች በዶ/ር አብይ ላይም እይተንጸባረቁ ናቸው ብዬ እገምታለሁ፡፡

1) ዶ/ር አብይ ሁሉንም የሚያስደስት

ወደ ገፅ 27 ዞራል



ረ/ፕሮፌሰር ዳንኤል መኮንን ይልማ
ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር
dmekonnen37@yahoo.com

# ያልተቀደሰው የኦነግና የህውሃት ጋብቻ እና የቲም ለማ ስጋት



ያሳለፍነው ሳምንት ለቀድሞዎቹ ባላንጣዎች ህውሃትና ኦነግ መልካም ያልነበረ ሳምንት ነበር፡ ፡ያልተቀደሰ ጋብቻ የፈጸሙት ሁለቱ “ነጻ አውጪዎች” (የለውጡ ጉዞ ያሰጋቸው) እንደተለመደው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ዋና መነጋገሪያ ነበሩ። ህውሃት አመራር የተቃወመችውን “የማንነትና የድንበር ኮሚሽንን የማቋቋም አጀንዳን” ጠፍጥፋ ባዋቀረችው የእንደራሴዎች ምክር ቤት የማጽደቅ ሂደትን በመቃወም ምንም እንኳን ለፓርላማው 23 ገጽ የተቃውሞ ሰነድ ብታቀርብም በታሪኳ ዝቅተኛውን ድምጽ በማግኘት ለመጀመሪያ ጊዜ አጀንዳዋ ውድቅ ተደርጎባት“እንግዲህ የእንተያያለን” ከበሮ መቀሌ ላይ እየጎሰመች ትገኛለች። ከእጇ እየበሉ ከደጇ እየጠጡ የነበሩት የህውሃት አክቲቪስቶችም የማንነትና የድንበር ኮሚሽኑ አጀንዳ በፓርላማ ከጸደቀ በኃላ ፌዴራሊዝሙ አበቃለት እያሉ የተለመደውን ጩኸታቸውን አሁንም ድረስ አላቆሙትም።

በሌላ በኩል በቦሌ ወጥቶ በቦሌ የገባው በዳውድ ኢብሳ የሚመራው የኦሮሞ ህዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦነግ) እንደ ጠገበ ጎረምሳ እኔ የምለውን ካላረክ “የእንጋጠም” ጥሪ ለመንግስት አቅርቧል። መንግስትም (ከኦዴፓ መግለጫ እንደሰማነው) ጥሪውን የተቀበለና ልክህን አሳይካለው አይነት ምላሽ ለኦነግ ሰቶታል።

እነዚህ ሁለት ክስተቶች በብስለትና በስርአቱ ካልተያዙ በቀጣይ የሀገሪቱ ፖለቲካ ላይ ትልቅ በጎ ያልሆነ አሻራቸውን ጥለው ሊያልፉና ተስፋ የተጣለበትን የለውጥ ጉዞ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊያመሩት ይችላሉ።

ንጉሳዊውን ስርአት ገርስሶ መንበረ ስልጣኑን የተቆጣጠረው የደርግ መንግስት መጀመሪያ ላይ ሲሰባሰብ መመሪያ ብሎ የያዘው “ኢትዮጵያ ትቅደም ያለ ምንም ደም” የምትልን መፈክር ነበር። ነገር ግን ሀገሪቱን በደም ለማጨማለቅ አንድ አመት እንኳን አልፈጀበትም። 60ዎቹን ለመረሸን የተተኮሰችው የመጀመሪያዋ የደርግ ጥይት ስንት ወጣቶችን የቀጠፉ ብዙ ጥይቶችን እንዳስከተለች የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን ማገላበጥ

ወደ ገፅ 28 ዞሯል

# ከአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ
## የተሰጠ መግለጫ



አርበኞች ግንቦት 7 በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመታገል ቆርጦ የተነሳ ድርጅት ነው።

ባለፉት አመታት የኢትዮጵያ ህዝብ በሃገራችን አፈና እንዲያበቃ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሏል። ውሎ አድሮ በኢህአዴግም ውስጥ ከዚህ መስዋእትነት ከፋይ ህዝብ ጋር የወገኑ የለውጥ ሃይሎች ተነስተዋል። የእነዚህ ሁለት ኩነቶች ድምር የሃገራችንንን ፖለቲካ ከነበረበት አስፈሪ ሁኔታ ወደ ተሰፋ ሰጭ ሁኔታ መርቶታል። ይህን ያጤነው ድርጅታችን አርበኞች ግንቦት 7 አመጽን ጨምሮ ሲያደርግ የነበረውን የነጻነትና የመብት ማስከበር ትግል ያለምንም ማቅማማት ወደ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ቀይሮታል።

አርበኞች ግንቦት 7 ይህን ውሳኔ ሲወስን በሃገራችን ውስጥ ሁሉ ነገር ተስተካክሏል የወደፊቱ ትግል አልጋ ባልጋ ይሆናል ከሚል እሳቤ አልነበረም። ገብተንበት የነበረውን አመጽን ያካተተ ትግል ቀድሞውኑ ተገፍተን እንጂ ወደን የገባንበት አለመሆኑና በተለይ ከገባንበት በኂላ ይህ አመጽን ያካተተ የትግል ስልት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሊያስከትል የሚችለው መዘዝ ክፉኛ ያሳስበ ስለነበር ነው።

አርበኞች ግንቦት 7 ለነጻነትና ለፍትህ መከበር የአመጽ ትግልን ያካተተ ትግል የጀመረው ለተመሳሳይ ዓላማ ተመሳሳይ ትግል በበርካታ የአረብ ሃገራት መደረግ ከመጀመሩ በፊት እንደነበር ያስታውሷል። በነጻነት ስም የተጀመረ የአመጽ ትግል ሶሪያን፣ የመንን ሊቢያንና ሌሎችንም የአረብ ሃገራት የጨመረበትን ሲኦል የመሰለ ሁኔታ ለተመለከተ የኛም ተመሳሳይ ትግል በተለይ በኢትዮጵያ የተወሳበበ ሁኔታ ምን ሊያስከትል ይችል ይሆን ብሎ መጨነቁ አይቀርም። አመጽ፣ አንድ እምነት አንድ ቋንቋ የሚናገሩ የአረብ ሃገራት ህዝቦችን ወደ ሲኦል ከወሰደ እንደኛ የቋንቋ፣ የባህልና የእምነት አይነት በበዛባት ሃገር የት ሊወስደን እንደሚችል ለመተንበይ ጠንቋይ መቀለብ የሚያስፈልግ አይሆንም።

የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ በኢትዮጵያ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ለሰላማዊና ህጋዊ ትግል የተሻለ እድል ከፍቷልና የአመጽ ትግል እናቁም የሚለው ውሳኔ የመነጨው ሃገርንና ወገንና ከሚያሰቀድም ጭንቀት እንጂ ከድርጅቱና ከአባላቱ ጠባብ ጥቅምና ፍላጎት አይደለም። በዚህ ጽኑ እምነትና ምክንያት ላይ በመመስረት ንቅናቂያችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የተኩስ አቁም አድርጎ ሃገሪቱን የሚመራው የለውጥ ሃይል ያቀረበውን የሰላም ጥሪ ተከትሎ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ በቅቷል።

ንቅናቂያችን በመሳሪያ ሃይል ይንቀሳቅሱ የነበሩ አባላቱን ከመንግስት ጋር ባደረገው ስምምነት ወደ ካምፕ ያስገባ ሲሆን፣ እስከአሁን ካምፕ ያልገቡትንም መንግስት ወደ ካምፕ እንዲያስገባ በጋራ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ንቅናቂያችን በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ሲንቀሳቀሱ ለነበሩ ታጣቂዎቹ በምንም አይነት የአመጽ እንቅስቃሴ እንዳይሳተፉ መመሪያ ከሰጠበት እለት አንስቶ እስከ አለንበት ወቅት ምንም አይነት ችግር ያልተፈጠረ ሲሆን አባላቶቻችን ለሰላም መስፈንና ለህግ የበላይነት መከበር ካላቸው ቀናዒነት የተነሳ ወደፊትም ምንም አይነት ችግር እንደማይፈጠር እርግጠኞች ነን።

አመጽ ከሃገራችን ፖለቲካ ተወግዶ ፖለቲካ በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ የሚደርግበት ሁኔታ ሲናፍቅ የኖረው ንቅናቂያችን ዛሬ በሃገራችን የተፈጠረውን ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ለማድረግ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይቀለበስ በመንግስት ውስጥ ካሉት የለውጥ ሃይሎች፣ ለሰላምና ለህግ መከበር ከቆሙ ከተለያዩ ተፎካካሪ ድርጅቶች ጋር በጋራና በጽናት እንድሚቆም ያሳውቃል።

ሁሉም ለሰላም ዘብ ይቁም ።

አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ

(በያሬድ ኃ/ማሪያም)



# ክልል ከአገር የሰፋባቸው ጎሰኞች እና ኢትዮጵያ

የጎሳ ፖለቲካ ከሚያስከትላቸው መዘዞች ውስጥ ብዙዎቹን ባለፉት አሥርት አመታት አስተናግደናል:: በቅርቡም አስከፊ በሆነ መልኩ አፍጦና አግጦ አይተነዋል:: ሕዝብ እርስ በርሱ ተጋጭቷል:: የብዙዎች ሕይወት ጠፍቷል:: በሚሊዮኖች ተፈናቅለዋል:: ቀላል ግምት የማይሰጠው የአገር ሃብት ወድሟል:: ከቡራዩ እስከ ቤኒሻንጉል፣ ከአዋሳ እስከ ኡጋዴን ብዙ አይተናል፤ ታዝበናል:: ከእነዚህ እልቂቶች ግን አልተማርንም::

ኢትዮጵያ ዛሬ በማን እጅ እንዳለች አፍ ሞልቶ መናገር ይከብዳል:: የተወሰኑ እና ወሳኝ የሆኑ የአገሪቱ ክፍሎች የአፈንጋጮች መጨፈሪያ ሆኗል:: በዶ/ር አብይ የሚመራው የፌደራል መንግስቱ የሕዝብን ቅቡልነት አግኝቶ አገሪቱን በበላይነት ያስተዳድራል ቢባልም በተወሰኑ ክልሎች ላይ አቅም አልባ ሆኗል::ከፌደራል መንግስቱ በተቃራኒ የቆሙ እና እራሳቸውን እንደመንግስት የሚቆጥሩ ሁለት የመንግሥትን አቅም እየተፈታተኑ ያሉ ትናንሽ መንግስታት ጎልተው እየታዩ ነው::

አንደኛው መቀሌ የከተመው ህውሃት ነው:: የፌደራል መንግስቱ በአሁን ሰዓት በትግራይ ክልል ላይ ያለው ሥልጣን ምን ያህል እንደሆነ ግልጽ አይደለም:: ሁለተኛው ትንሽ መንግስት ደግሞ ቀድሞ ጃዋር መሃመድ የፎከረበት እና አሁን አፍጦ የወጣው የቄሮ-ኦነግ መንግስት ነው:: እነዚህ ሁለት ኃይሎች የለውጥ ኃይሉን ክፉኛ እየተፈታተኑ ለመሆኑ አሁን በበርካታ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለው ሁኔታ በደንብ ያሳያል:: በአንዳንድ አጀንዳዎችም ሁለቱ ኃይሎች ሲደጋገፉና ሲመጋገቡ ይታያል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞም በትግራይ እና በአማራ ክልል አዋሳኝ ድንበሮች ላይ የሚታየው መፋጠጥ ሌላ አገሪቱን ወደ ቀውስ ውስጥ ሊከት የሚችል ሁኔታ ነው:: የመቀሌ እና የባህርዳር ፍጥጫ ከቃላት ምልልስ ካለፈ ቆይቷል:: ወታደራዊ ሰልፍ ማሳመር ከጀመሩ ውለው አድረዋል::

ኢትዮጵያ ሰፊ አገር ነች:: ሕዝቦቿን አጥግቦ የሚያሳድር ሰፊ መሬት ያላት አገር ነች:: ሁሉም የአገሪቱ ክፍል የየራሱ የሆነ ልዩ እና ውብ መገለጫዎች አሉት:: የዛኑ ያህልም በየአካባቢው ያለው ሕዝብ የራሱ የሆኑ ውብ ባህሎች፣ ቋንቋዎች እና እድሜ ጠገብ ትውፊቶች አሉት:: ኢትዮጵያ የእነዚህ ሁሉ ውጤት ነች:: አንዱ ቢጎድል ትጎድላለች:: አንዱ ቢታወክ ትታወካለች:: አንዱ ሲታመም ትታመማለች:: አንዱ ያለ ሁሉም፤ሁሉም ያለ አንዱ ብቻቸውን አይደምቁም::

ኢትዮጵያዊ ስትሆን ሞያሌ ላይ ሆነህ አክሱምን፣ ጋምቤላ ላይ ሆነህ ኡጋዴንን፤ ባሌ ተራሮች ላይ ሆነህ የሰሜን ተራሮችን፤ ነቀምት ላይ ሆነ ጎንደርን፣ አሳይታ ላይ ሆነህ ጂንካን፤ አርባ ምንጭ ላይ ሆነህ መቀሌን አቅርበህ ታያለህ:: ሁሉም የእኔ ነው በሚል የአገር ባለቤትነት ስሜት ትኮፈሳለህ:: ባሌጎባ ሲታመም መቀሌ ላይ ሆነህ አብረህ ትታመማለህ:: ወልዲያ ላይ ሆነህ ድሬድዋ ሲከፋት አብረህ ትከፋለህ:: አድዋ ላይ ሆነህ አንቦ ስታነባ አብረህ ታነባለህ:: ደስታም ሲሆን አብረህ ትደሰታለህ::

> ❝ እራስህን በክልል አጥረህ እና እዕምሮህንም የጎጥ ግንብ ገንብተህ የፈለከው አፋፍ ላይ ወጥተህ ብትቆም ይቺኛዋን ኢትዮጵያ አታያትም

እራስህን በክልል አጥረህ እና እዕምሮህንም የጎጥ ግንብ ገንብተህ የፈለከው አፋፍ ላይ ወጥተህ ብትቆም ይቺኛዋን ኢትዮጵያ አታያትም:: አገርህ አንድም እራስክን በከለልክበት ክልል ወይም አዕምሮህን በጠረነፍክበት ጎጥ ውስጥ ትወሰናለች:: ክልልህ አገርህ ይሆናል:: ከኢትዮጵያ ድንበር ሳትወጣ ከክልልህ በወጣህ ጊዜ ሌላ ሰው አገር የገባህ ያህል ይሰማሃል:: ሌላው ኢትዮጵያዊም ሀገሬ ሰፊ ነች ብሎ አንተ ወዳለህበት ሥፍራ ሲመጣም እንደ ባዕድ ትቆጥረዋለህ:: አንድ የሌላ ሀገር ሰው እደጃፍህ እንደመጣ ያህል ይሰማሃል::

የጎጠኝነት በሽታ ክልልህን ከኢትዮጵያ አስበልጠህና አግዝፈህ ትልቅ አገር አድርገህ እንድታይ ብቻ ሳይሆን የሚያደርግህ የሌላውንም ኢትዮጵያዊ አገር እንድታጠብ ያደርግሃል:: አገሬ ነች ብሎ ከአንድ የአገሪቱ ጫፍ አንተ ወዳለህበት ሥፍራ የሚመጣውን ሰው እያዋከብክ እና እያሳደድክ ስታባርረው አገርህ አይደለም እያልከው ነው:: ተመልሶ የሚሄደው ወደ ትውልድ ቀዮው ነው:: የራስህን አገር ያጠበብከው አልበቃ ብሎህ የሌላውንም ኢትዮጵያዊ አገር ታጠባለህ:: ጥበት ደግሞ መጨረሻው ድህነት፣ የእርስ በርስ ግጭት፣ ስደት እና እልቂት ነው::

ዛሬ ኢትዮጵያ በአራቱም ማዕዘን በጠባብ ጎጠኞች ተወጥራለች:: አገራቸውን ያጠበቡ ጠባቦች ኢትዮጵያንም እያጠበቧት ይመስላል:: ዛሬ አንድ ሰው በነጻነት ከፈለገው የአገሪቱ ክፍል ተነስቶ ወደ ወለጋ ወይም ወደ ሞያሌ ወይም ወደ መቀሌ መንቀሳቀስ አይችልም:: እነዚህ በጎጥ አጥር ተወስነው ሌላውን ኢትዮጵያዊ በማንነቱ ብቻ የሚያሳድዱ እና የሚያፈናቅሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ኢትዮጵያን እንዲያጠቡብን መፍቀድ የለብንም:: ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊታገላቸው ይገባል::

የአሃድ ዘገባ

# ‹‹አዲስ የፖለቲካ ራዕይ አንግበናል››

ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ



አርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ለሰላማዊ ትግል ወደ ሀገር ቤት ከገቡት ፓርቲዎች ዉስጥ አንዱ ሲሆን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተንቀሳቅሶ የቀጣይ የትግል መሰመሩን ለህዝብ በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል፡፡
ፓርቲዉ በአዲስ አበባ ሰሞኑን በራስ ሆቴል ፣በመብራት ሀይል፣ በኮኮብ አዳራሽ ባዘጋጃው ህዝባዊ መድረክ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ንቅናቄን ወደ ፓርቲነት የማሸጋገር ሂደት ላይ አተኩሮ እየሰራ እንደሚገኝ የፓርቲዉ ሊቀመንበር ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ እና ዋና ፀሃፊዉ አቶ አንዳርጋቸዉ ፅጌ ገልፀዋል፡፡
ፓርቲዉ የወደፊት እንቅስቃሴዉ በዜግነት ላይ የተመሰረተን የፖለቲካ ራዕይ ማንገቡን አስታዉቋል፡፡ እንደ አመራሮቹ አገላለፅ አርበኞች ግንቦት ሰባት በሁሉም ወረዳዎች ላይ በምርጫ የመወዳደር እቅድ እንዳለዉና ለዚህም ከወረዳዎች አንስቶ በህብረተሰቡ ዘንድ እምነት የሚጣልባቸዉን ሰዎች እየመለመለ ያዘጋጃል፡፡
ድርጅቱ አሁን ላይ በጊዜያዊነት እያከናወነ ያለዉን የአደረጃጀት ስራ አጠናቆ ሲጨርስ ወደ ፓርቲ ምስረታ ሂደት በፍጥነት እንደሚገባም ተጠቁሟል፡፡ በአዲስ አበባ የንቅናቄዉ አደራጅ ግብረ ሀይል የነደፈዉን የሁለት ወራት የስራ እቅድንም አቅርቦ ዉይይት ተደርጎበታል፡፡
በተለይ ባለፈዉ ቅዳሜ በአዲስ አበባ ሜክሲኮ በሚገኘዉ የመብራት ሀይል አዳራሽ በርካታ ህዝብ የተገኘ ሲሆን ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኃላ በርካታ ህዝብ በተቃዋሚ ፓርቲ መድረክ ላይ የተገኘበት ተብሎለታል፡፡ በዚህ መድረክ ላይ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ ‹‹ በኢትዮጵያ በአጭር ወራት ዉስጥ የተስተዋለዉ ለዉጥ የሚበረታታ›› መሆኑን ጠቁመዉ ‹‹ ይህን ለዉጥ አደጋ ላይ ለመጣል የሚደረገዉን እኩይ እንቅስቃሴ ለመግታት መረባረብ እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል››፡፡
‹‹እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ባህሉና ቋንቋዉ ሊከበርለት እንደሚገባ ድርጅታችን ያምናል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ማህበራዊ ፍትህን በማስፈንና በዜግነት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ የእንቅስቃሴያችን ዋነኛ ቁልፎች ናቸዉ›› ያሉት ፕ/ር ብርሃኑ ‹‹ ከምንም በላይ በጋራ ስለምንኖርባት ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን በአፅንዖት ማሰብ ያስፈልጋል›› ብለዋል፡፡ ሊቀመንበሩ ‹‹ለሀገራችን ኢትዮጵያ በቅንነት መስራት ወደፊት በአዲስ መልክ የሚደራጀዉ የድርጅታችን ዋና ግብ ነዉ ›› ሲሉም አክለዋል፡፡
በመድረኩ ላይ የፓርቲዉ ዋና ፀሃፊ አቶ አንዳርጋቸዉ ፅጌ ‹‹ድርጅታችን የስያሜና የመዋቅር ለዉጥ በማድረግ ከተለያዩ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ ተደርሷል›› ብለዋል፡፡
እንደ አቶ አንዳርጋቸዉ ገለፃ‹‹ ከተለያዩ ፓርቲዎች ጋር በመስራትና በየወረዳዎች አባላትን በማደራጀት አዲስና ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ለመፍጠር እንቅስቃሴ እየተደረገ ነዉ፡፡ አርበኞች ግንቦት ሰባት ከሰማያዊ፣ ከኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና ከአንድነት ጋር በጋራ ለመስራት በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ስምምነት ላይ መደረሱን ተናግሯል፡፡
ኢህአዴግ የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እንደሚያስቀድም መርሁ አድርጎ ለአመታት ቢንቀሳቀስም የብሔሮችን መብት በማስከበር ረገድ በተግባር የታየ ለዉጥ እንደሌለ የብዙ የፖለቲካ ሰዎች ሀሳብ ነበር፡፡ አርበኞች ግንቦት ሰባት አዲስ የፖለቲካ ራዕይ አለኝ በሚልበት በዜግነት ፖለቲካ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ባህሉና ቋንቋዉ ሊከበርለት እንደሚገባ አፅንኦት በማድረግ የእያንዳንዱን ዜጋ መብት በእኩልነት የተከበረባት ኢትዮጵያን መፍጠር የፓርቲያችን ግብ ነዉ ብሏል፡፡


መልካም ሞላ



# የህወሃት ደብተር

የህጎች ሁሉ ማሰሪያ የሆነው ህገ መንግስት ነው። ዝርዝር አዋጆች ወይም ማንኛውም ዓይነት ህግ ሲረቅ ከህገ መንግስቱ ጋር ከተጣረሰ ህጉ ተቀባይነት እንደማይኖረው ይደነግጋል።ጥቅም ላይ መዋል የጀመረው ህዳር 29 1987 ዓ.ም ነው። የኢትዮጵያ የበላይ ተጠሪ ነኝ የሚለው ህጉ ከጸደቀ 24 ዓመት ሆኖታል። በማርቀቁ ሂደት ውስጥ የውክልና ማነስ እና በውስጡ የያዛቸው አንቀጾች ውክልና ችግር ፈችነት ጉዳይ አጨቃጫቂ ነው። አይወክለኝም፣ ህገ መንግስቱ ጫና አድርጎብኛል የሚሉ አካላት የመብዛታቸውን ያህል በህገ መንግስቱ አንደራደርም የሚሉም አሉ።

ህገ መንግስቱ ይሻሻል የሚል ጥያቄ በተለያየ ጊዜ እየተነሳ ቢገኝም ህወሃት መራሹ መንግስት በተደጋጋሚ ግዜ ህገ መንግስቱ አይነካም የሚል ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል። ህገ መንግስቱ ጥቂት ቡድንተኞች ተሰብስበው ያጸደቁት ( በአንዳንዶች አጠራር የህወሃት ማኒፌስቶ) እንጅ ኢትዮጵያ እና ህዝቧን ህልውና አስጠብቆ የህዝቡን መብት በእኩልነት አስከብሮ የሚዳኝ አይደለም።




ህገ መንግስት ሲጸድቅ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች እኩል ተሳትፎ አድርገውበት መጽደቅ ሲገባው በተቃራኒው አንዱን ገዥ እና ልዩ ተጠቃሚ አንደኛውን በዝባዥ እና ጨቋኝ አድርጎ ያስቀመጠ የህወሃት እና የኦነግ ማኒፌስቶ ነው።

አንድ ህገ መንግስት ተቀባይነት የሚኖረው በህገ መንግስት ስሪት ወቅት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል፣ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ ሊሂቃን እንዲሁም ሁሉንም የፖለቲካ ሀይሎች ማሳተፍ ሲሆን ይህም አንድን ህገ መንግስት የስረ-ነገር ቅቡልነት (Original Legitimacy) ያጎናጽፋል ሲሉ የህግ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ነገር ግን በ1987 ዓ/ም የጸደቀው ህገ መንግስት፤ በሚቀረጽበት ወቅት ሁሉን የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ ሊሂቃን የተሳተፉበት፤ የሁሉም ሀሳቦችና ፍላጎቶች የተስተናገዱበትና የተንጸባረቁበት ሳይሆን ስልጣንን በቁጥጥራቸው ስር ያዋሉ ቡድኖች የራሳቸውን ሃሳብ እና በልዩ ሁኔታ የሚጠቅም ህግ የቀረጹበት ሰነድ ነው፡ ፡ ገና ከመጀመሪያው ሁሉንም ያላቀፈ ህግ ተቀባይነት አለመኖሩ ብዙም አያስደንቅም።

ህገ መንግስቱ ገና መጀመሪያው የኢትዮጵያ ብሄሮች እና ብሄረሰቦች ብሎ ሲጀምር ማን ህዝብ ፣ማን ብሄር ማን ብሄረሰብ እንደሆነ የማይግልጽ ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ተብሎ መቀመጥ ሲችል ህዝብን የሚከፋፍል እና የሚለያይ ቃል ተቀምጦበታል።

ህገ መንግስት ሲረቅ ህዝብ ባልተወከለበት እና የመረጠው ህዝብ ተወያይቶ ያልወሰነው ህግ በመግቢያው ላይ ‹ መርጠን በላክላናቸው ተወካያቸው አማካኝነት እንዲወሰን አድርገናል› የሚል ቅጥፈት ተጽፎበታል።

እስካሁን ድረስ ከሰንደቅ አላማ አኳያ በአንድ ድምጽ መግባባት ያቃተን ህገ መንግስቱ ላይ ሲቀመጥ ህዝብን አሳታፊ ባለመሆኑ ነው።

ህገ መንግስቱ የዜጎችን መብት አላስጠበቀም፡ ፡ ታች ወርዶ በስራ ላይ ሲውል ያላግባቡ ክፍሎች የሚያግባቡ ሊሆን ይችል ነበር። ነገር ግን የሰብአዊ መብትን ፣ ዜጎች በሀገራቸው የመኖር መብታቸውን፣ ከቦታ ቦታ የመዘዋር መብታቸውን ገፏል። በተለይም አሁን በስፋት የሚታየው የዜጎች መፈናቀል ህገ መንግስቱ ህጋዊ ከለላ ይሰጠዋል። አንድን የክልል ባለቤትነት ለክልሉ ነዋሪዎች ብቻ ሲሰጥ የዚያ ክልል ነዋሪዎች ውጭ ሌሎች ወደ ‹ሀገራችሁ› ሂዱልን የማለት መብትን ሰጧቸዋል።

## ህገ መንግስቱ እንዴት ረቀቀ?

ህገ መንግስት አርቃቂውም ሆነ ያጸደቀው ክፍል ምንም አይነት ህዝባዊ ቅቡልነት የሌላቸው ናቸው። ህወሃት የራሱን ጥቅም ማሳኪያ እና ማስከበሪያ ከማድረግ ባሻገር የኢትዮጵያን ህዝብ መብት ያላስከበረ፣ ዜጎች ሰብዓዊ መብታቸው ተረግጦ ያለ አግባብ ህገ መንግስቱን ‹ጥሳችኋል› ተብለው ሲታሰሩ እና እስር ቤትም እጅግ አሰቃቂ አያያዝ ሲያዙ ፣ ህይወታቸው ሲጠፋ እና አካላዊ እና የስነልቦና ችግር ሲደርስባቸው አልታደጋቸውም።

ህገ መንግስቱን ያረቀቁት አቶ መለስ ዜናዊ ፣ አቶ ሌንጮ ለታ እና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ሲሆን እኒህ ቡድኖች ጫካ በገቡበት ወቅት ጽፈውት የነበረውን ፖሊሲና እና ደንብ ኮሚሽን አቋቁመው አጸደቁት እንጂ ህዝቡ


ahadmegazine18@gmail.com

ተስማምቶ ያወጣው ህግ አይደለም፡፡ ህገ መንግሥት እንዲያረቅ ኃላፊነት የተሰጠዉ ቡድን የተመረጠዉ በሽግግር መንግሥቱ ምክር ቤት ነው:: ያ ምክር ቤት ሕዝቡን የወከለ ካልነበረ መራጩ በራሱ አካታች አልነበረም ማለት ነው::

ምክር ቤቱ 29 አባላት ያሉት ሲሆን ከተለያዩ የሙያ እና የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የፈለጉትን ሰው ብድግ ብድግ አድረገው አባል ያደረጉበት ስብስብ ነው:: አቶ ክፍሌ ወዳጆ ሊቀመንበር፣ አቶ ዳዊት ዮሐንስ ጸሐፊ ሆነው ተሾሙ:: ይህ ኮሚሲዮን የሚያረቀው ህገ መንግሥት የሽግግር መንግሥቱን ቻርተር መንፈስ የተከተለ መሆን እንዳለበትም በማቋቋሚያ አዋጁ ላይ ተገልጿል:: ያንን ቻርተር ያዘጋጁት ደግሞ ፖለቲካዊ ድርጅት ያላቸው ሦስት ሰዎች ናቸዉ:: አቶ መለስ ዜናዋ፣ አቶ ሌንጮ ለታ እና አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ:: የህገ መንግሥቱን መንፈስ እና ግብ ምን መሆን እንዳለበት የሽግግር መንግሥቱ ከመቋቋሙ በፊት እነዚህ ሦስት ሰዎች አስቀድመው ያረቀቁትን ቻርተር ማየት ነዉ:: በቻርተሩ መንፈስ ህገ መንግሥት እንዲያዘጋጁ የሽግግር መንግሥቱ ምክር ቤት መረጣቸው::

የምክር ቤቱ አፈጉባኤ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ናቸዉ:: ያው አቶ መለስ ሃያ ዘጠኝ ሰዉ መርጠዉ "ሕገመንግሥት ጻፉ" አሏቸው ማለት ነው:: ይህ ኮሚሲዮን ያረቀቀውን ለምክር ቤቱ አቀረበ:: ከዚያ ለሕዝብ ዉይይት ቀረበ ተባለ:: ሕዝቡ በበቂ ሁኔታ ስላልተወያየበትም እንዲሁም ዝርዝር የህገ መንግሥት እውቀት ሊኖረዉ ስለማይችል 'እኔ የተወያየሁበት ነው፤ የእኔ ነው' የሚልበት አጋጣሚ የመኖር ዕድሉ ጠባብ ነው:: ከዚያ አሁንም ምርጫ ተደረገና በአጽዳቂ ጉባኤ ለአርባ ቀናት ተቀምጠው ተጽፎ የተሰጣቸዉን በድምጽ ብልጫ አጸደቁ:: ሊቀመንበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ምክትሉ አቶ አዲሱ ለገሰ እና ጸሐፊዉ አቶ አባተ ኪሾ ነበሩ::

ከጉባኤያተኞቹ ውስጥ የተወሰኑ በጣት የሚቆጠሩ ከአዲስ አበባ የተመረጡ ተቃዋሚዎች ነበሩ:: እነ ሻለቃ አድማሴ፣ ዘለሌ ጸጋ ሥላሴ የመሳሰሉት:: እነሱ ይቃወማሉ ከአምስት መቶ በላይ የሆኑ ኢህአዴጎች በየተራ ይሰድቧቸዋል:: በመጨረሻም በድምጽ ብልጫ ውድቅ አድርገዉ ሰነዱን አጸደቁት" ሲሉ አቶ ውብሸት አብራተዋል::

አቶ ውብሸት እንደሚሉት የህገመንግሥቱን መንፈስ የቀረጹት እነዚህ ሦስት ሰዎች ይመሯቸው የነበሩ ድርጅቶች ነበሯቸው:: የህገ መንግሥቱ መንፈስም የእነዚህ ፓርቲዎችን ፕሮግራም የሚያንጸባርቅ ነው ማለት እንደሚቻል አረጋግጠዋል:: በሌላ አነጋገር ህገ መንግስቱ የፖለቲካ ፕሮግራምነቱ ያመዝናል እንደማለት ነው:: እዚህ ላይ ግን አንድ ልብ ማለት ያለብን ጉዳይ እንዳለ

አቶ ውብሸት ይጠቁሙናል፤ የሰብዓዊ መብትን የሚመለከቱት አብዛኛዎቹ አንቀጾች ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ሰነዶች የተወሰዱ በመሆናቸው የፖለቲካ ፕሮግራም መልክ አላቸው ብሎ ማጃመል አይቻልም በማለት ከበኩር ጋር ባደረጉት ቆይታ ገልጸዋል፡፡

ህገመንግስቱ ሲያረቁ አብዛኛው ነፍጠኛ በሚል ጸረ አማራ ትርክት ፈጥረው የአማራን ህዝብ እንደ ጨቋኝ እና በዝባዥ ይቆጥሩት በነበሩ ሰዎች ነው፡፡ ሲረቅም ሆነ ሲጸድቅ አንድም የአማራ ተወካይ በሌለበት እና አማራ ጨቁኖል በሚል ፖሊሲ ቀርጸው የተገንጣይ ቡድን ሲመሩ በነበሩት አቶ መለስ አቶ ኢሳያስ እና አቶ ሌንጮ ለታ አማኝነት ነው፡፡ እነዚህ ጸረ አማራ አስተሳሰብ ያላቸው እና በአማራ መቃብር ላይ ነጻነታችን እናውጃለን ብለው ጫካ የገቡ ሰዎች ፍትሃዊ እና የአማራንም ሆነ ሌላ ከእነሱ ጎሳ ውጭ ያሉት የሚጠቀም ፍትሃዊ የሆነ ህግ ያወጣሉ ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው፡፡ አላወጡምም፡፡ በጥቅሉ ኢትዮጵያ ጠል በሆነ አስተሳሰብ የተጠመዱ ሰዎች ተሰብስበው ያወጡት ደብተር እንጂ ህገመንግስት ሊባል አይገባው የሚሉት በርካቶች ናቸው፡፡ አይወክለንም እንደ ዜጋ አያውቀንም የሚሉት በርካቶች ናቸው፡፡

## የማንነት ጥያቄ በህገመንግስት

ህወሃት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ከሰራቸው ስራዎች አንዱ ኢትዮጵያን በክልል መከፋፈል ነው፡፡ ከዚህ ከለላ በኋላ በአማራ እና በትግራይ ክልል የማንነት ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይዋል፡፡ ወልቃይት ፣ራያ ፣ሁመራ ጨምሮ በርካታ የአማራ ታሪካዊ ቦታዎች ወደትግራይ ተካለዋል፡፡ ከመካለልም ባለፈ ባለፉት ሃያ ሰባት አመታት ሆነ ተብሎ በአካባቢው የህዝብ ስፈራ ተደርበታል፡፡ ወልቃይት እና ጠገዴ ነባር ነዋሪዎች ህዝብ ተፈናቅሎ በምትኩ ከትግራይ የመጣ ህዝብ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

አሁን ይህን ጉዳይ በህገ መንግስቱ ይዳኝ ቢባል መፍታት አይችልም፡፡ ብዙ በፖለቲካዊ ውሳኔ የተወሰኑ እንደ ቅማንት አይነት ቦታዎች በህገ መንግስቱ ይፈታ ቢባል ህገ መንግስቱ አያውቃቸውም፡፡ እንደምሳሌ በአማራ እና ትግራይ መካከል ያለውን ችግር አነሳሁ እንጅ በኦሮሚያ እና በሶማሌ ፣ በሶማሌ እና ኦሮሚያ ፣ በቤንሻንጉል እና አማራ/ ኦሮሚያ ተመሳሳይ የወሰን ወይም የማንነት ጥያቄዎች ቢኖሩም ፖለቲካዊ ውሳኔ የተሰጠባቸው ከመሆኑ አንጻር ማለት ከባድ ነው፡፡

የህግ ባለሙያው አቶ ውብሸት ሙላትም እንዲህ ያለውን ችግር ህገ መንግስቱ ሊፈታው አይችልም በሚል አጭር ቋንቋ ያስቀምጡታል:: ማንነትን በሚመለከት የሚነሱ ጥያቄዎች ነጻ፣ ፍትሐዊና ተቀባይነት ያለዉ ዳኝነት መስጠት የሚችል ተቋም እንደሌለ የሚገልጹት እርሳቸው እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን እንዲፈቱ በክልልና በፌደራሉ ሕገ መንግሥታት የተቋቋሙት ተቋማት ፍትሐዊ ዉሳኔ መስጠት እንዲችሉ ሆነው አልተቋቋሙም ብለዋል:: "በክልሎች ላይ (ከሐረርና ከደቡብ በስተቀር) በየወረዳዉ ወኪሎች ያሉበት የህገመንግሥት ኮሚሽኖች አሉ:: በእርግጥ እነዚህም በአግባቡ አልተቋቋሙም:: ይህ ማለት የወልቃይት አማራ ማንነት ጥያቄ የሚቀርበዉ ከአርባ ሦስት ገደማ ወረዳዎች የተወከሉ የትግራይ ተወካዮች ባሉበት የህገመንግሥት ኮሚሽን ነዉ:: በሌላ አገላለጽ ከብሔር አንጻር የበደለዉ ትግራይ፣ ተከሳሹም ትግራይ፣ ዳኛዉም ትግራይ ነው ማለት ነው:: ስለዚህ ራሱን በራሱ የሚያጠፋ ቡድን (Suicide Squad) እስካልሆነ ድረስ ራያንና ወልቃይትን ወደ አማራ ክልል ይመለሱ ብለው ሊወስኑ የሚችሉበት ምንም ዓይነት መዋቅራዊ አቋም የላቸውም" ብለዋል::

## በህገ መንግስቱ የተረሳች ከተማ

ህገመንግስቱ የረሳት እና አስተዳደራዊ ችግሮቿ ህግ አልባ ያደረጋት ከተማ አንዷ ድሬዳዋ ናት፡፡ በኢትዮጵያ በክልል ከተከፋፈሉት ውጭ ሁለቱ ከተሞች በአስተዳደር ተወስነዋል፡፡ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ፡፡

ድሬዳዋን ህገ መንግስቱ አያውቃም፡፡ አዲስ አበባን ደግሞ ቢያውቃትም አያውቃትም፡፡ በህገ መንግስት አንቀጽ 49 መሰረት አዲስ አበባ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አላት ሲል ይደነግጋል፡፡ መሬት ላይ ያለው እውነት አዲስ አበባ አዲስ አበቤ አያስተዳድራትም፡፡ ከዚህ በፊት ያሉትም ሆነ አሁን ያለው የአዲስ አበባ ህዝብ የመረጠው ሳይሆን ገዥው መንግስት ለህዝቡ የመረጠለት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ምርጫ መደረግ ቢኖርበትም ተዘሏል፡፡ የሚያስተዳድራትም ከኦሮሞ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ኦዴፓ) አባል የሆኑ ሰው ነው፡፡ ይህ በቀጥታ ህገ መንግስቱን ሽሯል፡፡ በባለፈው ምርጫ ከአቶ ታከለ ይልቅ ለአዲስ አበባ ቅርብ የሆነች እና መስፈርቱም በተሻለ የምታሟላው ወ/ሮ ዳግማዊት መመረጥ ሲገባ ከተመረጠች በኋላ ወደ ትራንስፖርት ሚኒስቴር እንድትዛወር መደረጓ ይታወሳል፡፡


ድሬዳዋ በጭራሽ ህገ መንግስቱ አያውቃትም፡፡ ስለ ድሬዳዋ አስተዳደር ምንም ባለመጻፉ የድሬዳዋ ህዝብ የራሱን አስተዳደር መምረጥ አይችልም፡፡ የሶማሌ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የአማራ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በጥረት ይመሯታል፡፡ በአቶ አባይ ጸሃየ ትዕዛዝ አስተዳደሯ አንዴ ከኦዴፓ አንዴ ከሶህዴፓ በፈረቃ እየተመረጡ ይመሯታል፡፡ አንደኛው የኦዴፓ ተመራጭ ተመርጦ የራሱን ጥቅም አደላድሎ ሰዎቹን ቀያይሮ ሳይጨርስ የስልጣን ዘመኑ ያልቅና ሌላኛው የኦዴፓ ተመራጭ ስልጣኑን ይይዛል፡፡ ተመሳሳይ አዙሪት ውስጥ ገብቶ ሳያበቃ የስልጣን ዘመኑ ያልቃል፡፡ የመሰረተ ልማት ጥያቄ አይታሰብም፡፡ ሰሞኑን በወጣው መረጃ መሰረት ድሬዳዋ ውስጥ ከ 2006 ዓ/ም ጀምሮ አንድም ፕሮጀክት አልተጀመረም፡፡

ህገ-መንግስቱ የኢትዮጵያን ህዝብ የማይመጥን እና ከጥቃት የማያስጥል ነው፡፡ ሊቀየርም ይገባዋል፡፡ እንዴት ከተባለ እሱም የራሱ የሆነ ህግ እና አግባብ አለው፡፡



ታምራት ታረቀኝ

# ከምርጫ በፊት




መንደርደሪያ

ከቅርብ አመታት ወዲህ ሕዝብ የሚለው የወል መጠሪያ ሁሉም እንደ አፈታቱ ወይም እንደ ወረደ እየተጠቀሙበት መስመር ስቷል ብቻ ሳይሆን ቅጥ አምባሩ ጠፍቷል። በየአዳራሽ የተገናኘ ሀምሳም መቶም ሰው፤የቀበሌ ነዋሪም የወረዳም እያለ እስከ ሀገር ድረስ ነዋሪው ህዝብ እየተባለ ነው የሚጠራው። ፖለቲከኞቹ ለዓላማቸው ነው። የጋዜጠኞችን ምን ይሉታል?

ያረጁበት ሲፋቱት አዳዲስ ወጤዎች (የወጡ ለማለት ነው) እየተጋቡት ላካሚውም ሆነ ለአስታማሚው አልመች ባለውና ትልቁ በሽታችን በሆነው ዘረኝነትም ሁሉም ነገድ በሉት ጎሳ፣ ብሄረሰብ በሉት ማህበረሰብ፣ መጠሪያው ህዝብ ሆኗል። ይህም ብቻ አይደለም ተግባር የማያውቃቸው ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች ሁሉ የራሳቸውን ፍላጎት ሕዝብ እንዲህ ብሎ፤ ህዝቡ የሚፈልገው፣ የሚጠይቀው ይህን ነው ሲሉ የቱ ህዝብ እንዲያ እንዲናገሩለት የት መቼና እንዴት እንደወከላቸው እነርሱም አይናገሩም አልተወከሉምና። ሌላውም አይጠይቅ ምን አገባኝ ባይነት በዝቷልና፡ ፡ ጠያቂ ሲገኝም አስኳላን ያሳለፉት በስድብ የሆነ ይመስል የስድብ ናዳ ያወርዳሉ፣ የፍረጃ ጅራፍ ያጮኸሉ።

ለተአማኒ ምርጫ የህዝብ ወሳኝነት።

ቀዳሚው ነገር የምርጫ ዴሞክራሲያውነት ማረጋገጫው መራጩ ሕዝብ ድምጽ መስጫ ኮሮጆ ውስጥ የዶለውን ድምጹን በትክክል ወደ ሥልጣን መቀየር መቻሉ ነው። ስለሆነም የህዝቡ ድምጽ መስጠት ዋንኛው ጉዳይ ነው። ተወዳዳሪም አወዳዳሪም ኖረው መራጩ ሕዝብ አልመዘገብም አልመርጥም ቢል ምርጫ አይታሰብም።

ሁለተኛው ነገር ሕዝቡ ይህ ምርጫ ዛሬ የእኔን ነገ የልጆቼን ህልውና የሚወስን ነው ብሎ አምኖ፤ ያለምንምና ማንም ተጽእኖ በራሱ ህሊና አስገዳጅነት የሚካፈልበት (የሚሳተፍበት ማለቱ ያስነሰዋል) መሆን መቻሉ ነው።ይህ ሲሆን ህዝቡ በአራት ዋሳኝ የምርጫ ኩነቶች ላይ ይሳታፋል።

ሀ-በተመራጭነት፡

በስማ በለው ወይንም የተጻፈ በማንበብ ሳይሆን በተግባር ሰርቼው እንደማውቀው የፓርቲዎች አንዱ ችግር ተወዳዳሪ ዕጩ ማግኘት ነው። ለዚህ ደግሞ ቀዳሚው ችግር አሁን አሁን ፓርቲዎቹ የስም እንጂ የተግባር አለመሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው ጎመን በጤና ባዩ መብዛቱ ነው። ፓርቲ ወደ ሰው ወይንስ ሰዉ ወደ ፓርቲ የሚያነጋግር ጉዳይ ስለሆነ ከአስፈለገ በሌላ ርእስ እመለስበታለሁ። በቀደሙት ተከታታይ የምርጫ ጉዳይ ጽሁፎች ለማሳየት እንደ ሞከርኩት የድምጽ ውጤት ከተገለጸ በኋላ ለአንድ ሳምንት የተለመደ ተጭበርብሯል ጩኸታቸውን አስምተው ለቀጣይ አራት አመት ተከናንበው የሚተኙ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድ የግዜ ሰሌዳውን ሲያወጣ በድንብርብር ጉዞ በሚያደርጉት የዘጥ ዘጥ ስራ ጥራቱ ቢቀር ብዛት ያለው ዕጩ ማቅረብ እንዴት ይችላሉ ?

ነገር ግን ዓላማ ተብሎ ስራ ተደርጎ ቢሰራ ከ100 ሚሊዮን ህዝብ ያውም ደግሞ ለሀገር መሪነት እውቀትም ልምድም ካለው ብዛት አንጻር እጩ ፍለጋ መባዛን ሳይሆን በማወዳደር ማቅረብ በተቻለ ነበር። እዛ ደረጃም ባይደረስ ቢያንስ የሚወዳደሩት እኔ ተሸነፍኩ ማለት ምርጫው ተጭበርብራል ማለት ነው ብለው በኪሳቸው የብጥብጥ አጀንዳ ይዘው ሳይሆን ዋና ዓላማና ግባችን የእኛ ፓርላማ መታየት ወይንም ቤተ መንግስት መግባት ሳይሆን በዚህ ምርጫ የዴሞክራሲ ሥርዓት የመሰረት ድንጋይ ማኖር መቻል ነው ብለው የሚወዳደሩ፤ በፓርቲ መሪዎች የሚነዱ ሳይሆን በራሳቸው ህሊና የሚወስኑ በሁለት እግራቸው የቆሙ እጩዎችን ለማዘጋጀት መጀመሪያ ፓርቲ ያስፈልጋል። ሲቀጥል አንድ የምርጫ ግዜም በቂ አይደለም፡ ፡ ለምንይልክ ቤተ መንግስት መታገልና ለዴሞክራሲ መታገል በጣም የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው እየታወቀ የፖለቲካ ትግል የሥልጣን ጥያቄ ነው በሚል ማጨናበሪያ ይድበሰበሳል። ፖለቲከኞቹ የሚያጨናብሩና የሚያጭበረብሩት ራሳቸውን ጭምር በመሆኑ ሁለቱንም እንደ አጡት ዘመናት ተቆጠሩ።

ለ-በመራጭነት፤

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩት መራጭ ከሌለ ምርጫ የለም። መራጭ ስንል ደግሞ እስከ ዛሬ እንደተለመደው አንድም በጥርነፋ ሁለትም በልፈፋ የሚያስወጡት ከዚህም በላይ ከተመዘገበው ይህን ያህል ፐርሰንቱ ድምጽ ሰጥቷል ብለው የሚያላግጡበት ሳይሆን፤ እድሜው ለመመርጥ ከደረሰውና ህግ ክልከላ ካልጣለበት ምን ያህሉ ተመዝግቧል? ከተመዘገበውስ ምን ያህሉ ድምጽ ሰጥቷል? ይህ በምን ያህል መቶኛ ተፈጻሚ ሲሆን ነው ህዝብ መርጧል ለማለት የሚያስችለው?

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

# ህገ መንግስቱ ይከበር




የሰሜን ወገኖቻችን ከመለስ ዜናዊ ሙት መንፈስ ካልተላቀቁ በስተቀር ነገሩ ሁሉ እየተምታታባቸዉ የሄደ ይመስላል:: ህገ መንግስቱ ይከበር ብሎ መቀሌን ያራደ ሰልፍ መዉጣት ምን የሚሉት ነዉ? ከነሱ ብሶ መገንጠላችን ነዉ ብለዉ ማስፈራራታቸዉስ ከምን የመጣ ነዉ? ይህ ነገር ከፖለቲካ ትንተና ይልቅ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ ጊዜ ካለዉ የሳይኮሎጂ ትንተና ቢሰጥበት መጠነኛ ግንዛቤ እናገኝ ነበር :: እንዴት ነዉ ሰሞኑን የሰሩትን ግፍ አይተን ትንሽ ትልቅ ሳንል እምባ በእምባ ያራጨንን ዘግናኝ ግፍ በህውሃቶች መሰራቱን በመረጃ እየቀረበለን የመቀሌ ምሁራን ወንጀሉን በመካድ ብሄር ተኮር ነዉ ብለዉ መግለጫ መስጠት ከምን የመጣ ነዉ? ለዛዉም የዩኒቨርስቲ መምህሩ አብረሀ ደስታ። አይ ትምህርት አይ ህሊና !

ህውሃቶች ሌቦቻችን በቴሌቭዥን ታዩብን ብለው ሙሾ መዉረድ በጤናማ አስተሳሰብ ሲታይ ግራ ያጋባል? እነዚህ ሰዎች ተገንጥለዉ ቢሄዱ የዘረፉት ገንዘብ ምን ያህል እንደሚያቆያቸዉ የተገነዘቡ አይመስልም። በዚህ ላይ አቦይ ስብሀት ኢፈርት የልጆቼ ነዉ ሲል ምስኪኗ አዜብም ድርሻዋን መጠየቋ አይቀርም። እነ አባይ ጸሀዬም አይናቸዉ ኢፈርት ላይ ነዉ። እዚህ ላይ የቆየ የሀራችን ብሂል አለ። ሌባ ሲካፈል እንጂ ሲሰርቅ አይጣላም የሚሉት። ለካ አርከበም አለ ብዙ ናቸዉ። ቢገነጠሉ ከማን እንደሚዋሰኑ ለደቂቃ አስበዉታል? ከደቡብ አማራ 27 አመት ቆዳዉን የገፈፉት፣ በሰሜን ጥርስ ነቅለዉ ያባረሩት ኤርትራዊ፣ በምስራቅ ሽሪያ ሱዳን፣ በምእራብ ያተራመሱት አፋር በእነዚህ ተከበዉ ምን አይነት ህይወት ሊያሳልፉ ያምራቸዋል።

ህገ መንግስት ማለት ከሁለት ቃል ተዋህዶ የተሰራ ከመሆኑም ባሻገር ቃላቱ በተራዉ ህዝብ ግንዛቤ እንኳን መንግስት ማለት የአንድን ሀገር የመሪነት ወንበሩን ይዞ የሚያሽከረክረዉ ሲሆን ስልጣንና ሃላፊነቱም ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣዉ የሀገርን አንድነት ማስጠበቅ፤ህግና ደምብን ባለዉ ተቋማት በሀገሩ ማስከበር፤ ሐገሪቱን የሚወክለዉን ባንዲራ አክብሮ መያዝ፤ሌባና ነብሰ ገዳይን ተገቢዉን ቅጣት መስጠት እያለ ይቀጥላል። በእርግጥ አብይ ለሌቦቹ ጊዜ በመስጠቱ የደረሰዉን ጥፋት እሱም ሳይገነዘበዉ አልቀረም። በጣም ሰልጥነዋል በተባሉት በምእራብ አገሮችም ሌባና ነብሰ ገዳይን ለመያዝ ቆይ ጊዜ እንስጠዉ የሚባልበት ጉዳይ አልነበረም። ወንጀለኛ ይሰወራል፣ ንብረት አገር ይለቃል፣ ስም ይዘዋወራል ሌላም ሌላም:: ለዚህም ነበር የሌቦች አለቃ ክንፈና ጓደኞቹ ለሰሩት ወንጀል እንደገና ታክስ ከፋዩ ጠበቃ ያቁምልን ብለዉ የቀለዱት...። ህውሃቶች ግን በመንግስትነት ዘመናቸዉ የሰሩት የዚህን ተቃራኒ ነበር።

ለህውሃቶች ህገ መንግስትን ማክበር ማለት የዜጋን ጥፍር እየነቀሉ ማሰቃየት፣ የሀገሪቱን ተስፋ ወጣት ዜጎችን ከጅብ ጋር አስሮ በብርድና በፍርሀት ሰቆቃ ዉስጥ መጨመር፤ የሀገሪቱን እሴቶች በህገ ወጥ መንገድ መመዝበር፤ መሸጥ፤ከባእድ ጋር ተመሳጥሮ ሀገርን መበዝበዝና ማዉደም ነበር። እነሱ አእምሮ ዉስጥ ያለዉ የህገ መንግስት ጽንሰ ሀሳብ ምን ይሆን? የሚያደንቁት ሞሶሎኒም እኛን ጎዳ እንጂ ለሀገሩ ድንቅ ስራ ነዉ የሰራዉ። የእነሱ አገዛዝ ህገ አራዊት ነዉ። አስተሳሰባቸዉና ተግባራቸዉ ሲታይ ከዛ ብዙም የራቀ አይደለም። ለምሳሌ በአንድ የአራዊት ጥበቃ አደጋ ላይ የነበረዉን ልጅ ዝንጀሮዉ ከሌሎች ዝንጀሮዎች ተከላክሎ ልጁን በህይወት ከቤተሰቡ አገናኝቷል። እንዲህ አይነት ሰባአዊነት ግን በህውሃቶች አልታየም። የነዚህ ግፍ እኮ በቀደም የታየዉ ዋናዉ ሳይሆን ቅምሻዉ ነዉ። ጎበዝ ገና ብዙ ጉድ አለ። የሀገራችን ወጣት ጋዜጠኞች ለስራችሁ እዉቅና ከፈለጋችሁ ይህንን ወንጀል ተከታትላችሁ ለህዝብ አቅርባችሁ ታሪክን ጻፉ። ይህ እድል ለጋዜጠኛ ሁል ጊዜ የሚገኝ ስላልሆነ ተጠቀሙበት። ጆናታን ድምብልብይ የወሎን ረሀብ ተከታትሎ አሳይቶ ነዉ ዛሬ እርሶ ተብሎ ተከብሮና ተደንቆ የሚኖረዉ።

”

ለህውሃቶች ህገ መንግስትን ማክበር ማለት የዜጋን ጥፍር እየነቀሉ ማሰቃየት፣ የሀገሪቱን ተስፋ ወጣት ዜጎችን ከጅብ ጋር አስሮ በብርድና በፍርሀት ሰቆቃ ዉስጥ መጨመር፤ የሀገሪቱን እሴቶች በህገ ወጥ መንገድ መመዝበር፤ መሸጥ፤ከባእድ ጋር ተመሳጥሮ ሀገርን መበዝበዝና ማዉደም ነበር

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

(በዶ/ር መሀመድ አሊ እንድሪስ)



# አጀንዳህን ኢትዮጵያዊ የሚያደርገው ኢትዮጵያዊነቱ ነው!

ስለ ሀገርህ ስታስብ በአንድነቷ ውስጥ ጨፍልቃ ስለምትይዛቸው ልዩነቶች ሳይሆን ከልዩነቷ ተቀምሮ ስለተሰራው አንድነቷ ብታስብ መልካም እንደሆነ በመናገር ልጀምር። አንተ ሙስሊም መሆንህን ሳታምን ጥሩኢትዮጵያዊ በመሆንህ ላይ በራስ የመተማመን መንፈስ ላይ ልትደርስ አትችልም። ‹‹ጥሩ ሙስሊም ሳትሆን ጥሩ ኢትዮጵያዊ ልትሆን አትችልም›› እያልኩህ ነው።

ታዲያ ጥሩ ሙስሊም ስልህ ቀኖናዊ ግንዛቤህን አምጥቀህ አምልኮ ላይ ስለሚኖርህ ትጋት እያወራሁ አይደለም። እርግጥ ነው ይህም ከፀጋዎቹ ነው። በእስልምናህ እንደማንነት መገለጫ የማትኮራባት ኢትዮጵያ ጥሩ ኢትዮጵያዊ አታደርግህም። እናም ጥሩ ሙስሊም ኢትዮጵያዊ ለመሆን በራሱ የሚተማመን ሙስሊም መሆን ቅድመ ሁኔታ ነው። ይህን ካላደረክ ይፍጠን ወይንም ይዘግይ እንጂ የእውነታዎች ተቃርኖ አፍጥጦ ይመጣል። መሰረቱን ስትጥል ተጠንቅቀህ ያላሰብክበትን ጉዳይ ቤቱን ከገነባህ በኋላ እልፍኙን ሊያስከለክልህ ይችላል።

ደግሞ ልንገርህ አይደል… አቋም ከሌለህ የትም አትፈለግም። ‹‹የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አደረጓት›› ተብላ ጭምጭምታዋ የሚሰማ አንዲት አሉባልታ ቢጤ አለች። እሷን ልንገርህማ…. በስብሰባ መሐል አንዱን ሙስሊም ሚኒስትር ወረቀት ቢጤ ወርውረውበት ‹‹እንዳንተ አቋም ከሌለው ደጋፊ ደህና አቋም ያለው ተቃዋሚ ይበልጥብኛል›› አሉት አሉ። መቼም ‹‹አሉ›› ነው… እዚያ ተገኝተን አላየንም።

‹‹እንደ ሙስሊም ኢትዮጵያዊ በራስህ ተማመን›› ስልህ ታዲያ ‹‹ከፉክክር እና ከቅደም ተከተል መንፈስም ለመራቅ ሞክር›› ስል መጨመር ይጠበቅብኛል። ሐጋይ ኤርሊች ሁለቱን ገናና እምነቶች በኢትዮጵያ ሲስላቸው ‹‹ዙፋኔን ተቀማሁ የሚል ቁጭት ያለበት›› እና ‹‹የሚገባኝን አላገኘሁም በሚል እልህ ልቡ ያቄመ›› ሲል ነበር ቂም በቀል ሊዘራ የሞከረው። አሁን ደግሞ ጊዜው ተቀይሮ ‹‹የሚገባኝን ያገኘሁበት ዘመን አሁን ነው›› ብሎ ያመነ እምነት ሶስተኛ ምድብ ይዟል። ‹‹ዙፋኔን አጣሁ›› ባዩ አስተሳሰቡ ብዙም ያልተቀየረ ሊሆን ይችላል። አካሄዱን ግን ቀይሯል። ‹‹የሚገባኝን አላገኘሁም›› የሚለው ክፍል ደግሞ የሚገባውን እስኪያገኝ አቋሙን መቀየር ባይጠበቅበትም አካሄዱን ካልቀየረ ግን ዘመኑ በራሱ እንደሚተፋው ሊያውቅ ይገባል። ለዚያም ነው ‹‹አካሄድህን ልትቀይር ግድ ይልሃል›› የምልህ።

ባለንበት ወቅት የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ፎረሞች፣ የሚዲያ ተቋማት ወዘተ… በሚያነሱት ኢትዮጵያዊ አጀንዳ እንጂ በእነማን ነው የተያዙት ከሚል መነሻ ኢትዮጵያዊነታቸው አልተፈጋገጠላቸውም

ስለሙስሊሙ ስታወራ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለኢትዮጵያ እያወራህ ነው። ሙስሊሙ በደሴት ውስጥ የሚኖር ስላልሆነ እና ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ከዚያም አልፎ አምልኮአዊ ተግባራትህን በምትፈፅምበት ወቅት በአንድ ወይንም በሌላ መልኩ ሙስሊም ካልሆነው ኢትዮጵያዊ ጋር የሚገናኙ ሂደቶች ውስጥ ማለፍህ ስለማይቀር ስለሙስሊሙ ስታወራ ከሌሎቹ ጋር ስለሚኖረው መስተጋብርም እያወራህ ነው። እናም ስለ ኢትዮጵያ እየሰራህ እንደሆነ በልበ ሙሉነት እመን።

ወዳጄ ምናልባት ይሄን ስልህ እንደ ባለፉት 10 እና 15 አመታት ሁሉም ነገር በመስጂድህ ዙሪያ፣ ሁሉንም ከእምነት አቻዎችህ ጋር ብቻ አድርግ እያልኩህ እንደሆነ እየገመትክ ይሆን እንዴ? ቆይ ላጥራልህ፤ ይበልጥ እንድትረዳኝ ይህን ነገር ሰፋ አድርጌ በርዕስ ከፋፍዬ ላቅርበው…

ታሪክን ኢትዮጵያዊ የሚያደርገው ኢትዮጵያዊነቱ ነው

በቅድሚያ ይህንን እወቅ… ስለ አንድ የተለየ ህዝብ ብትፅፍም፣ ስለ አጠቃላይ አገሪቱ ብትፅፍም ታሪኩ ኢትዮጵያዊ ነው። ‹‹ኢትዮጵያዊ ታሪክ›› እና ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ›› ግን ለየቅል ናቸው። ልክ ከዚህ ቀደም ‹‹ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነትን ለይተን እንይ›› እንደተባባልነው ነው ነገሩ። የኢትዮጵያ ታሪክ መልከ ብዙ፣ መጠኑ የሚለያይ ነው፤ አንዱን ታሪክ ብቻ ነጥለህ አጠቃላይ የአገሪቱ ታሪክ አድርገህ እስካላቀረብከው ድረስ። እናም አቅም እና ጊዜህን ታሳቢ አድርገህ ዋና ትኩረትህ ሙስሊሙ እንዲሆን ከወሰንክ በትኩረትህ ግፋበት… ምክንያቱም ትኩረትህ ኢትዮጵያዊ የትኩረት አቅጣጫ ነውና። እንደታሪክም ኢትዮጵያዊ ታሪክ ነው እየፃፍክ ያለኸው። የጎደለ አገራዊ ገፅታን ነው እያሟላህ ያለኸው። ብቻ አደራ የምልህ ነገር ቢኖር ስራህ ሙያዊ ታማኝነት እና ጨዋነትን መላበስ እንዳለበት ነው።

ምን እያልኩ መሰለህ….

በትምህርት መስክ እያለህ ሙስሊሙን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ብትሰራ፣ ብትመራመር፣ ብትፅፍ ፈፅሞ ወገንተኛ እንደሆንክ አይሰማህ። በአግባቡ ባለመጠናቱ መፍትሄ ያጣን፣ የአገር ሰላምና እድገትን አንቆ የያዘን ችግር ለመቅረፍ እየሰራህ እንደሆነ እመን። እውነቱን ነው ወዳጄ! ዘመናዊ ትምህርት ከተስፋፋ በኋላ ለውጭ

አገር ትምህርት እድል ያገኙ ኢትዮጵያዊያን የሰሯቸውን መመረቂያ ፅሁፎች አገላብጥ እስኪ። ቁጥሩ ይህ ነው በማልልህ መጠን ስለ ቤተክርስትያን ታሪክ፣ ስለገዳማትና አድባራት፣ ስለአገር እና ቤተክርስትያን፣ ቤተክርስያን ለሀገር አንድነት ስለተጫወተችው ሚና፣ በቤተክርስትያን ላይ ስለተጋረጡ አደጋዎች ወዘተ የሚተነትኑ ጥናቶች ናቸው የሚበዙት።

‹‹እናም ስለነሱ እኔን ምን አገባኝ?›› ትለኝ ይሆናል። እኔ ደግሞ ‹‹እነሱ አይባሉም›› እልሃለሁ። ‹‹እሰየው! እንኳንም እንደዚያ አጠኑልን!›› እልሃለሁ። ሃይማኖት እና አገር ሳይምታታባቸው ስለ አንዱ ሲያወሩ ስለሌላውም እያወሩ እንደሆነ ቀድመው በመረዳታቸው ስለ እነሱ እኔን ደስ እንደሚለኝ እነግርሃለሁ፤ በራስ መተማመንን የሰጣቸው አፈ-ታሪክ ሳይሆን እነዚህ ስራዎች እንደሆኑ ስለማምን። ታዲያ በራሱ የሚተማመን ዜጋ እኮ ሌላ በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሲያገኝ ተከባብሮ ይኖራል። እናም ወዳጄ… በራስህ እንድትተማመን መጀመሪያ ራስህን እመን! ባይሆን እዚህ ላይ አንድ አንገብጋቢ ጉዳይ ላንሳልህ፡-

እስካሁን በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ታሪክ ዙሪያ የተፃፉ ጥቂት መፅሐፍትን ብታይ ከርዕሳቸው ጀምሮ ስለ ትኩረት አቅጣጫቸው በግልፅ እና በታማኝነት አስፍረው ታገኛቸዋለህ፡፡ ፕሮፌሰር ሁሴን አህመድ ‹‹እስልምና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ወሎ›› ብሎ ሲፅፍ ስለ ወሎ እየፃፈ ስለሆነ ሌላውን የኢትዮጵያ ታሪክ አልነካም። ካነሳው ርዕስ ጋር ሊገናኝ የሚችለውን ተጠቅሞ ይሆናል እንጂ የወሎን ታሪክ በኢትዮጵያ ታሪክ ወክሎ አልፃፈም። ፕሮፌሰር ላጲሶ ‹‹የኢትዮጵያ የመከራ ስርዓት›› ብለው ሲፅፉ፣አህመዲን ጀበል ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የጭቆናና የትግል ታሪክ›› ብሎ ሲፅፍ ታሪኩን ኢትዮጵያዊ አድርገው፣ ከርእሳቸው ጀምሮም ታማኝ ሆነው ነው። ‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ›› ብለው ስለጭቆና ብቻ አላወሩም። ‹‹የሙስሊሞች የጭቆና ታሪክ›› ብለው ጀምረው ስለሌሎች ሃይማኖቶች መጨቆን አለመፃፋቸው ሊያስወቅሳቸውም አይችልም፤ ርእሳቸው ግድብ ነውና። በብዙ ታሪክ ፀሀፊያን እንደሚታየው ‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ›› ብለው የአንድን ህዝብ እና ባህል ታሪክ በመፃፍ በታሪክ ላይ አልዋሹም፡፡ ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ታሪክ›› ብለውም ስለጭቆና ብቻ አልጻፉም።

በተቃራኒው እነ ይልማ ደሬሳ እና አለቃ ታዬ የፃፏቸውን መፅሐፍት ስታይ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚያወሩ ይነግሩሃል፡፡ ውስጣዊ ይዘታቸው ግን አንድ ብሄር፣ አንድ እምነት ሆኖ ታገኘዋለህ። ተክለፃዲቅ መኩሪያም ቢሆኑ ብርቱ ሰውነታቸውን ከማድነቄ ጋር የነገስታቱን ታሪክ ሲፅፉልን የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የነገስታቱ ታሪክ ማለት ነው በሚል አጭቀው ነው። እንግዲህ በቀና መልኩ እንረዳው ካልንም ምክንያታቸው ‹‹ታሪኩን ከኢትዮጵያ ታሪክ ልንነጥለው አንችልም፤ በጥብቅ የተቆራኘ ነውና›› ከማለት ላይዘል ይችላል።

በታሪክ ጥናት እና በአጠቃላይ በሳይንሱ ዓለም አንድ ውጤት ከአንድ ሰበብ ጋር የሆነ ግንኙነት ስላለው ብቻ ውጤቱን በሙሉ ወክሎ የመቅረብ ቅቡልነት የለውም። የኢትዮጵያ ታሪክ እና ፖለቲካ ትልቁ ችግር ግን ይህንን ያላገናዘበ ‹‹ዲተርሚኒስቲክ›› አካሄድ መከተሉ ነው፤ ለአንድ ፖለቲካዊ ሁነት በርካታ መነሻዎች ኖረውት ሳለ አንዱን ብቻ መዞ ሁነቱን አንድ ቀለም በመቀባት የመጠቅለል አካሄድ። ይህም ማለት የዚያን ህዝብ አልያም እምነት ታሪክ ኢትዮጵያዊ ማድረጉ በቂ ሆኖ ሳለ ከኢትዮጵያ ጋር የሚተሳሰርባቸው ጉዳዮች ስላሉ ብቻ ‹‹የራሷ የኢትዮጵያ ታሪክ›› እንደሆነ አድርጎ የመጠቅለል አካሄድ እንደማለት ነው።

የፖለቲካ አጀንዳህን ኢትዮጵያዊ የሚያሰኘው ኢትዮጵያዊነቱ ነው

ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ፖለቲካ ለማውራት ኢትዮጵያዊ መሆን አይጠይቅም። ሲጀመር የኢትዮጵያ ታሪክ እና ፖለቲካ ሲፃፍና ሲዘወር የኖረው በኢትዮጵያውያን አይደለም፡፡ ነገር ግን ምሁራንም ይሁኑ ፖለቲከኞች ሀሳቡ ላይ እየተወያዩ፣ ፖሊሲውን እየተገበሩ ምንጩን አይመረምሩም። ‹‹Ethiopian Studies›› በመባል የሚታወቀው ስለ ኢትዮጵያ ጥናት እና ምክክር የሚካሄድበት ተቋም በ1959 ሲቋቋም ኢትዮጵያውያን ሚናቸው ለምንም የቀረበ ነበር። እስካሁን ከተካሄዱ 19 ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችም 13 የሚሆኑት በውጭ አገር ነው የተካሄዱት። በሚቀርቡት ጥናቶችም የውጭ አገር ዜጎች ጉልህ ድርሻ አላቸው።

ስለዚህ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ለማውራት ኢትዮጵያዊ መሆን ራሱ መስፈርት አይደለም፡፡ አንተ በሙስሊም ኢትዮጵያዊነትህ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ለማውራት፣ ለፖለቲካችን ችግሮች መፍትሄ ለመሻት ትልቅ ኃላፊነት አለብህ። የፖለቲካ አጀንዳህን ኢትዮጵያዊ የሚያደርገው ኢትዮጵያዊ ቀለም መያዙ ነው፡፡ አንተ ስላነሳኸው ብቻ ፖለቲካው እስላማዊ አይሆንም። አንተ ስላደራጀህ እና ስለመራኸው ብቻ የፖለቲካ ተቋሙ እስላማዊ ተቋም አይሆንም።

በኢትዮጵያ ታሪክ ወደላይኛው የመንግስት መዋቅር ሙስሊም እንዲያልፍ በህግ የታገደበት ወይም በሌላ መልኩ እንዳይሳተፍበት በተደረገባቸው የሚኒልክ እና የአፄ ኃይለ ስላሴ አገዛዝ ወቅት ‹‹ስርዓቱ ኢትዮጵያዊ አይደለም›› የሚል ትችት ሲቀርብ ሰምተህ ታውቃለህ? ሌላው ቢቀር በደርግ ጊዜ ደርግ የሚከተለው ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ለሃይማኖት ምንም የተለየ ትኩረት ካለመስጠቱ ጋር በካቢኔው አንድም ሙስሊም ተወካይ አልነበረም። ሙስሊም ስላልተሳተፈበት ግን የደርግን ስርዓት ‹‹ኢትዮጵያዊ አልነበረም›› አላስባለውም፡፡ ባለንበት ወቅት የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ፎረሞች፣ የሚዲያ ተቋማት ወዘተ… በሚያነሱት ኢትዮጵያዊ አጀንዳ እንጂ በእነማን ነው የተያዙት ከሚል መነሻ ኢትዮጵያዊነታቸው አልተረጋገጠላቸውም፡፡ ሌላው ይቅርና ‹‹ህዝባዊ ኑሮ እድገት››ን የመሳሰሉ ግልፅ ሀይማኖታዊ ተልዕኮ የነበራቸውን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሳይቀር ኢትዮጵያዊ አድርገን መቀበል የቻልን ሰዎች ነን።

ወደ ሙስሊሙ ሲመጣ አጀንዳው ኢትዮጵያዊ ለመባል ተጨማሪ ግለ ምርመራ (Self Censorship) እንዲያደርግ የሚጠይቀውን አስተሳሰብ ከምንጩ ማድረቅ የምትችለው በራስህ በመተማመን እንጂ ራስህን የመመርመር ግዴታነትን በመቀበል አይደለም። መድኃኒቱ በቀላል የማሸማቀቂያ ዘዴ እጅ ከመስጠትና በራስ ካለመተማመን ደዌ በፍጥነት መፈወስ ነው። ጥሩ ኢትጵያዊ የፖለቲካ ባለ ድርሻ ለመሆን ጥሩ ሙስሊም መሆንህ ቢረዳህ እንጂ አይጎዳህም። ስለምታነሳው ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ተጠንቀቅ እንጂ ያነሳኸው አንተ ሙስሊም መሆንህ ሊያሳስብህ አይገባም።

ታዲያ የሚቻል ነገር ሁሉ ትክክል ነው ማለት እንዳልሆነም አትዘንጋ። ከእምነት አቻዎችህ ጋር ብቻ ሆነህ ስለ ኢትዮጵያ ብትደክም በርግጥም ስለ ኢትዮጵያ ነው እየለፋህ ያለኸው። ግን ኢትዮጵያህ ብዙ ቀለም አላት፣ ከሌሎች ጋር ህብር ፈጥረህ ማየትን ትሻለች። እናም ሁሉንም በየመልኩ ስራ። መስጂድህን ለመገንባት ቋሚ እና ማገር ከሌላ እምነት ተከታይ ጎረቤትህ መዋስ ላይጠበቅብህ ይችላል፡፡ አገራዊ ተቋማትን ግን በጋራ እና በጋራ ብቻ ስትገነባቸው ነው አገራዊ የሚሆኑት።

ጥሩ የሃይማኖት መምህር ለጥሩ ኢትዮጵያዊነት መሰረት ነው!

ስለ እምነትህ ስታወራ እና ስትሰብክ የአንድ ትልቅ እምነት ተከታዮችን እየቀረፅክ እንደሆነ ታውቃለህ ብዬ አምናለሁ። ትውልድ መቅረፅ ከኃላፊነቶች ሁሉ የገዘፈው ኃላፊነት ነው፡፡ አንተ የምትቀርፀው ትውልድ ጥሩ ዜጋ፣ እምነቱ ውስጥ ያሉ መልካም ተግባራት ላይ የሚተጋ፣ የራሱ እምነት እንዲከበርለት የሌሎችንም የሚያከብር፣ በምድራዊ ህይወቱ እና በሰማይ ቤቱ መካከል ግርዶሽ አበጅቶ የማይሰቃይ አድርገህ እየቀረፅከው ነው። ታዲያ ከዚህ በላይ ምን ትልቅ ስራ አለ?

እንደውም ግልጽ ግልጹን ልንገርህ? አንድ የኦርቶዶክስ አማኝ ተነስቶ ‹‹ክርስትና ለኢትዮጵያ መፍትሄ አላት›› ቢለኝ ‹‹መፍትሄውን አምጣውና ከሀገራችን እና ከህዝባችን ጥቅም አንፃር እንየው›› እለዋለሁ… እንኳን በኢትዮጵያ ትልቅ አሻራ ያላትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስን ቀርቶ የስንቱን ሚሽነሪ የመፍትሄ ሐሳብ ፖሊሲ ብለን ተቀብለን እደምንኖር ስለማውቅ። ነገር ግን ይኸው ሰውዬ ‹‹ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሄ ከቤተክርስያን ብቻ ይምጣ›› ሲለኝ ግን ‹‹አንተ እና ቤትህ አምላክህን ለግላችሁ ያዙ›› እለዋለሁ።

ምን እያልኩህ መሰለህ…. እንደ ሃይማኖት ሰባኪነትህ ከእምነትህ የሚመነጩ ሀገራዊ የመፍትሄ ሀሳቦች ስታገኝ በቅንነት ወደፊት አውጣቸው። ለሀገርህ እድገት፣ ስለ ስራ ባህል፣ ህዝብን በቅንነት ስለ ማገልገል፣ ስለ ሙስና አስከፊነት፣ ለህዝቦች አብሮነት

ወደ ገፅ 31 ዞሯል

# ‹‹ደብረፂዮንም ሆነ ሌሎቹም ባለስልጣናት የትግራይን ህዝብ አይወክሉም››

## ...ከባለፈው ሳምንት የቀጠለ

ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም




**አሃድ፡- የአሜሪካ መንግስት የደህንነት ሹሙ ጌታቸዉ አሰፋን እንዲያዝ የሚል ትዕዛዝ አውጥቷል፡ ፡ የኢትዮጵያ መንግስት ጌታቸዉን ለመያዝ ብዙ ሙከራ አድርጓል፡፡ ይሁንና ህወሃት ሰዉዬዉን አሳልፎ የመስጠት ፍላጎት ያለዉ አይመስልም...**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ሰዉዬዉ በወንጀል ‹‹Crime Againset Humanity›› ወይም ከአለም ሰብዓዊ የጥፋት ወንጀሎች ከሚባሉት ከፍተኛዉን እንደፈፀመ በገሃድ የታወቀ ነዉ፡፡ እሱም ብቻ ሳይሆን በአካባቢዉ ያሉት ሰዎች ማስረጃዉን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በእሱ ስር ሆነዉ የሰሩትም ሰዎች ይሄንን ያጋልጣሉ፡፡ እንግዲህ አሜሪካ ባወጣችዉ ትዕዛዝ ላይ በመጀመሪያ እሱ እዚህ ሀገር ይመጣል ብዬ አላስብም፡፡ እዚህ ሀገር ቢደርስ በግለሰብ ደረጃም በህግም እንደሚጠየቅ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ እሱም ይሄን የሚያዉቅ ይመስለኛል፡፡

ሰዉዬዉ በጣም ተንኮለኛና ክፉ ሰዉ መሆኑ የታወቀ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ለመጠቆም ያህል እሱም ካነበበዉ እንዲያዉቀዉም ጭምር እዚህ ሀገር የሚመጠራዉ በራሱ ስም አይደለም፡፡ እያንዳንዱን ነገር የሚጠቀመዉ በሰዉ ስም ነዉ፡፡ መኪና እንኳን ሲከራይ በሰዉ ስም ነዉ፡፡ እሱ ያለበት ፌስ እንዳይደረግ ማለት ነዉ፡፡ ይሄንን ሁሉ የሚያደርገዉ ማንነቱ እንዳይታወቅ ነዉ፡፡ ለዚህ እኛ በቂ የሆነ ማስረጃ አለን፡፡ ምን እንደሚሰራም ጭምር እናዉቃለን፡፡ እራሴን አድናለሁ ብሎ ቢያስብ ከንቱ ሀሳብ ነዉ፡፡ እንደኔ ሀሳብ እዚህ ሀገር የሚመጣ አይመስለኝም፡፡ ከመጣም ተዘጋጅተን እንጠብቀዋለን ወደ ፍርድ ለማቅረብ፡ ፡ ሁሉም አሁን መቀሌ ዉስጥ ተሸሽገዋል፡ ፡ ማምለጫቸዉ እዛ ነዉ፡፡ የትግራይን ህዝብ ዘወር ብለዉ ሳያዩት በየቀኑ እያሰቃዩ አሁን ከዛ አምልጠዉ መተዉ ሌሎቹ ሊገሉን ነዉ፣ የትግራይን ህዝብ ሊያጠፉ ነዉ እያሉ እራሳቸዉን ለመደበቅ የሚሞክሩበት ብዙ መንገድ አለ፡፡

ለ 27 ዓመታት ኢትዮጵያ ላይ እንዳደረጉት ሁሉ የሚጫወቱት ጨዋታ ነዉ፡፡ እንግዲህ ይሄንን ሰዉዬ አንሰጥም ካሉ ሰዉዬዉ የት ይሄዳል? እንደ እኔ ሰዉዬዉ ከሀገር የመዉጣት እድሉ በጣም የመነመነ ነዉ፡፡ ቢወጣም የትም አለም ቢሆን ተፈልጎ መያዙ አይቀርለትም፡፡ እሱም እራሱ በነፃነት እኖራለሁ ብሎ እምነት አለዉ ብዬ አልገምትም፡፡ እሱም በዚህ ሁኔታ ከኖረ እራሱን እንዳሰረ ነዉ የሚቆጠረዉ፡፡ ህግ ይፈልገዋል፡፡ ከሀገርም ከወጣ በኢንተርፖል ይፈለጋል፡፡ ሀገር ዉስጥ የፈፀመዉ ወንጀል ስለሆነ የትም ሀገር ሄዶ መኖር አይችልም፡፡

**አሃድ፡- አንዳንዶች ደግሞ ሰዉዬዉ እስከ መኖሩም የሚጠራጠሩ አሉ፡፡ ምክንያቱም በፎቶም ምንም የሚታወቅ ነገር የለም ይባላል ይሄ ነገርስ እንዴት ነዉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ያዉ እንግዲህ ለዉጭ ተመልካች ላይታይ ይችላል፡፡ የፌደራል መንግስቱ ግን ያውቀዋል፡፡ ስለ ሰዉዬዉም ሰፋ ያለ መረጃ አላቸዉ ብዬ እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ እኛ ፎቶግራፉን ስላላየን ቢያነጋግረንም እነሱ ግን በሚገባ ያዉቁታል፡፡ ሆነም ቀረ

ወደ ገፅ 25 ዞሯል

# የሚራዘመዉ...

ከገፅ 24 የዞረ

ካልኩ ምርጫዉ ይራዘም አይራዘም በሚል ከሰሞኑ እየሰማን ያለዉን ዉዝግብ እናንሳ፤ በመሰረታዊነት በዚሁ አዋጅ በግልጽ ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት አመቱ ሊካሄድ እንደሚገባ ተቀምጦ ይገኛል፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ አዋጅ የተቀመጡ የምርጫ አይነቶች ጠቅላላ ምርጫን ጨምሮ አምስት አይነት ናቸዉ፡ ፡ የአካባቢ ምርጫ፣ማሙያ ምርጫ ፣ህዝበ ዉሣኔ፣ ድጋሚ ምርጫ ተብለዉ በአንቀጽ 27 ላይ ተቀምጠዋል፡፡

ጠቅላላ ምርጫን ስንመለከት የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤት አባላት ለመምረጥ በየ አምስት አመቱ በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ የሚካሄድ ምርጫ ቦርድ ሲያምንበት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ዉሳኔ ሲያገኝ ምርጫዉ በተለያየ ጊዜ መካሄድ እንደሚችል የሚያትት የምርጫ ስርአት እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነዉ፡፡ ታዲያ ይህ በየአምስት አመቱ የሚደረገዉ ምርጫ እየደረሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት ዉዝግቡ የትየለሌ ሆኖ እየተመለከትን እንገኛለን፡፡ ግማሹ የፖለቲካ ፓርቲ ምርጫዉ መራዘም የለበትም በሚል በርካታ መከራከሪያዎችን ያነሳል፡፡ ሌላዉም እንዲሁ መራዘም አለበት በሚል ሲከራከር ይስተዋላል፡፡

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ለማጣጣም ጥረት ማድረጉ ተገቢ ይመስላል፡፡ አንዱ የምርጫ ህጋችን ሲሆን፣ ሌላዉ ደግሞ የሀገሪቷ ነባራዊ ሁኔታ የምርጫ ህጉ አንቀጽ 28(ሀ) ላይ በተመሳሳይ ወቅት ይካሄዳል ካለ በኃላ (ለ) ላይ ምርጫ ቦርዱ ሲያምንበት ተወካዮች ምክር ቤትም ሲቀበለዉ በተለያየ ጊዜ ሊሆን እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡ ይህ ደግሞ አሁን ላይ ሰላም የሌለባቸዉ እና የተፈናቀሉ ወገኖች ያሉባቸዉን ስፍራዎች ይህን አንቀጽ መሰረት አድረጎ በማስተናገድ ለሌሎች የሀገራችን ክፍሎች ደግሞ ሌላ ለምርጫ አስፈላጊ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ከተገኙ በተወሰነለት ወቅት ምርጫ ማድረግ ማስቻል፣ ህጉን መንግስት ጣሰ ከሚል እና መንግስት ታማኝ አይደለም ከሚል ትችት የሚያድን ይመስላል፡፡ ይህም ግን በተወካዮች ምክር ቤት ተቀባይነትን መሰረት አድርጎ ነዉ፡፡

ከሀገሪቷ ነባራዊ ሁኔታ ስንነሳ በተለይ በአሁኑ ወቅት ጠንካራ የሆነ ለምርጫ የበቃ የፖለቲካ ፓርቲ አለን ወይ? ይህን መመለስ ይገባል፡ ፡ ሁላችንም እንደምናዉቀዉ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ታሪክ ምንም እንኳን እረጅም ታሪክ ያላቸዉ ቢሆኑም በአብዛኛዉ በተለያየ ምክንያት በእስር የቆዩ ፤ ከሀገር ወጥተዉ ከሰላማዊ ትግል በዘለለ ሌላ እንቅስቃሴ ያደርጉ የነበሩ ሲሆኑ ሀገር ዉስጥ ያሉትም ቢሆኑ በተለያየ ምክንያት አቋማቸዉ የተዳከመ ይመስላሉ፡፡ ታዲያ በዚህ በ ስድስት እና በስምንት ወር ባሳዩት የፖለቲካ አቋም ህዝቡ ከስሜት በዘለለ ይመርጣል ወይ? እዉነት የፖለቲካን አቋም ገምቶስ ይመርጣል ወይ? ይህን ያልኩት አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ የፖለቲካ ድርጅት በሰብአዊ መብት ጥሰት እየተወቀሰና አፋኝ እንደነበር እየተነገረ ነዉ፡ ፡ ህዘቡም ለዉጥ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ለዉጥ በመፈለግ ብቻ ገና በድንበር ፣በብሄር ፣በማንነት በዘር፣በፖለቲካ አስተሳሰብ እየተናቆርን ባለንበት በአሁኑ ሰአት ጠንካራ ያልሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ወደ ስልጣን ቢመጣ ለሀገራችን መፍትሄ ይዞ ይመጣል ወይ የሚለዉ አጠራጣሪ ነዉ ብየ እገምታለሁ፡፡

ሌላዉ አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ ፓርቲ ምርጫዉን በተለያዩ ምክንያቶች አራዝማለሁ ቢል ምርጫ እንዲካሄድ የሚፈልጉ እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ተቀባይነት እንዳላቸዉ የሚያምኑ ፤እንዲሁም በግርግር ተቀባይነት እናገኛለን ብለዉ የሚያስቡ አካላት ወይም ፓርቲዎች ለሀገራችን ሰላም ይሰጣሉ ብሎ ማሰብም አይቻልም፡፡ መንግስት በአዋጅ የተደነገገዉን ህግ ጥሶአል በማለት ለዘለፋ ምላሰቸዉን የሚያረዝሙም አይታጡም፡ ፡ ከዛም አልፎ ወደ አላስፈላጊ ግጭት የሚያመሩበት መንገድ ሰፊ ይሆናል፡፡ ይህንን ለማለት ያስቻለኝ ደግሞ መግለጫ በመስጠት ምርጫዉ ቢራዘም ያልታዩ ችግሮች ይፈጠራሉ በማለት በእርግጠኝነት እስከ መናገር የደረሱትን ፓርቲዎች በሰማሁ ጊዜ ነዉ፡፡ ቀድመዉም ስለ ወደፊታችን እየተነበዩልን ይገኛሉ፡፡

ምርጫ በመሰረታዊነት ለህዝብ በማሰብ የሚደረግ፣ ህዝብ መንግስቱን የሚመርጥበት ስርአት ነዉ፡፡ ለህዝብ ተብሎ የተዘረጋን ስርአት እንዴት ህዘቡ ባልተረጋጋበት ሁኔታ ህዝብ በየቀኑ ከየክልሉ እየተፈናቀለ ባለበት በአሁኑ ሰአት ለምርጫ መሟላት ያለባቸዉ ሁኔታች ተሟልተዉ ምርጫዉ ይካሄዳል ለማለት ይከብዳል የሚል መከራከሪያ የሚያነሱ ፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን መከራከሪያ የሚጠቀሙ ፓርቲዎች ለመወዳደር ዝግጁ ያልሆኑ ፓርቲዎች እንጂ አሁን መንግስት እንደ መንግስት ለምርጫ መሟላት ያለባቸዉን ነገሮች የማሟላት አቅም አለዉ፡፡ በመሆኑም በአንድ አመት ዉስጥ ምርጫ ለማካሄድ እንቅፋት እንደማይሆን ያስረዳሉ፡፡

ሌላዉ ምርጫን ለማካሄድ የህዝብ ቆጠራ መሰረታዊ ነዉ፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ ምርጫዉ ለህዝብ ሲባል የሚደረግ ነዉ፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ፓርቲዎች ለራሳቸዉ የስልጣን ፍላጎት ቢሮጡም! የሀገራችን ህዝቦች ተፈናቅለዉ በተቀመጡበት ሁኔታ ምርጫን ማካሄድ አንዳንድ እናሸንፋለን ብለዉ በህዝብ ላይ አመኔታ የጣሉ ፓርቲዎች ካልሆኑ በቀር ህዝቡን ተደራሽ አድርጎ ምርጫ ቀስቅሶ ህዝብ ተረጋግቶ መምረጡ ላይ አጠያያቂ ይመስላል፡፡

ሌላዉ የምርጫ አዋጁን በመከለስ ላይ ነዉ የሚል ጭምጭምታም አለ፡፡ ለምርጫዉ የቀረዉ አንድ ድፍን አመት እና የተወሰኑ ወራቶች ናቸዉ፡፡ ታዲያ ህጉ ተከልሶ ለሁሉም መሰረት የሆነዉ ሰላም ተመልሶ በተገቢዉ መንገድ ምርጫ ተቀስቅሶ የታሰበዉ እቅድ እዉን መሆኑ ላይ አከራካሪ መስሎ ይታያል፡ ፡ ያም ብቻ ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 552/2007 አንቀጽ 63 ላይ ስለ ምርጫ ጣቢያ ደህንነት ሲያብራራ የምርጫ ጣቢያዎች ከምርጫ በፊት እንዲሁም በምርጫ ሰአት እና ከተጠናቀቀ በኃላ እዚህ ላይ ከቆጠራ በኃላ ለማለት ነዉ፤ የምርጫ ጣቢያዉ ደህንነት መጠበቅ ይኖርበታል ፡፡

ደህንነት መጠበቅ ሲባል በአንድ ወቅት ምርጫ ሲካሄድ የምርጫ ኮሮጆ ለመስረቅ እስከ መሞከር የተደረሰበት ሁኔታ ነበር፡፡ በዚህም የሰዉ ህይወት ጠፍቷል፡፡ በመሆኑም ህዝብ ሊያስተዳደረኝ ይችላል የሚለዉን አካል ለመመምረጥ በወጣበት ህይወቱን ሊያጣ እንደማይገባ ይሰማኛል፡፡ ከምርጫ በፊት ቀድሞ የሚነሳዉ የምርጫ ቅስቀሳስ? አሁን ባለዉ ነባራዊ ሁኔታ ማካሄድ ይቻላል ወይ? የሚለዉ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነዉ፡ ፡ አንዳንድ ክልሎች ላይ ፓርቲዎች ሄደዉ እንደፈለጉ መቀስቀስ መቻላቸዉ ያጠያይቃል፡ ፡ ምክንያቱም በሚያሳዩት እንቅስቃሴ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ዳር የያዙ፣ በራሳቸዉ ዛቢያ የሚዞሩ ስላሉ ታዲያ በራሱ ዛቢያ የሚዞር አጠገቡ ማንም እንዲዞር አይፈቅድም፣ አይፈልግምም፡፡ ልዙር ካልክም መዞሪያህን ሊበጥሰዉ ይችላል፡፡

በተቃራኒዉ መራዘም የለበትም ብለዉ መከራከሪያ የሚያደርጉት ህጉን ነዉ፤ ይህ ምርጫ በ አምስት አመት አንድ ጊዜ መደረግ እንዳለበት ከተቀመጠ ህጉን አለማክበር እና ምርጫዉን አለማካሄድ ህግ መጣስ ነዉ፡ ፡ በተለይ መንግስት እንደ መንግስት ህግ ማክበር ስላለበት የህዝብ ተአማኒነትን ለማግኘት ምርጫዉ መካሄዱ ግድ እንደሆነ የሚያምኑም አሉ፡፡

እኔ ግን እላለሁ፤ ምርጫ መራዘሙ፣ አለመራዘሙ መከራከሪያ ሊሆን አይገባም፡ ፡ ይልቁንም በሀገራችን ላይ እንዴት አይነት ፍሃዊ የምርጫ ስርአት መገንባት እንችላለን? የሚለዉን ጉዳይ መመለስ እንዳለብን አስባለሁ፡፡ መሟላት ያለባቸዉ ጉዳዮች እየተሰሩ የምርጫዉ ሁኔታ ራሱ መልስ እያበጀ እንደሚሄድ እምነቴ ነዉ፡፡ እሱም ብቻ ሳይሆን ከምንም በላይ ሰላም ወሳኝነቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ አንድ ክልል ላይ የጦር ቀጠና ሆኖ ምርጫ ላካሂድ ማለት ለህዝብ ሳይሆን ለወንበር እንደመወዳደር ይቆጠራል፡ ፡ ምክንያቱም ህዝቡ ሰላም ሳይኖረዉ ምረጥ ማለት እርስ በእርስ ተጫረስ ማለት ነዉ፡፡ ስለሆነም ከምንም በላይ ስለ ሰላም መፍትሄ ፈልጎ በመቀጠል ምርጫዉን ማካሄዱ ተገቢነቱ የጎላ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡

በተደጋጋሚ የምርጫ ኮሮጆ እየተሰረቀ እና ህዝብ ያልፈለገዉን እንዲመርጥ እየተገደደ እንኳን ሲመርጥ እና ባልፈለኩት ፓርቲ ተመራሁ እያለ ቁጭቱን ችሎ የኖረን ማህበረሰብ በተለይ በቅርቡ ሃሳቡን እንዲገልጽ፣ ንጹህ አየር እንዲተነፍስ እየተደረገ ባለበት ሁኔታ ሀገር ሙሉ ለሙሉ እስኪረጋጋ ተጠብቆ ሌሎች የህግ ማእቀፎችን ተጠቅሞ ከስር ከስር መሟላት ያለበቸዉን ሂደቶች የምርጫ ቦርድ እየሰራ መንግስት ደግሞ በሰላም ግንባታዉ ላይ እየተረባረበ ከሁለት መጥፎ ዉጤት የሚያስከትሉ እዉነታዎች የተሻለዉን መጥፎ በመምረጥ ለሀገር ሚች እንጂ ለወንበር ሚች እንዳናይ፣ እንዳንሰማ ተመኘቼ አንባቢዎችም የራሳችሁን ሃሳብ ትይዙ ዘንድ ዉሳኔዉን ለእናንተ በመተዉ አበቃሁ፡፡

በሰልማን ኮከብ



# ‹‹የዝቅተኛነት ስሜት›

የሙስሊሙ ኡማ ትልቁ ችግሩ የዝቅተኛነት ስሜቱ ነው። በእኛ አካባቢ ብቻ አይደለም በሁሉም ቀጠናዎች የበላይነት ስነ-ልቦናው ከስሞ የተጎጅነት ስሜት ብቻ ነው ያለው። በዚህ የዝቅተኛነት ስነ-ልቦና ደግሞ መቼም ድል አናገኝም። ለዚህ ትልቁ ምሳሌ የሚሆነን የሙሳ (ዐሰ) ህዝቦች ታሪክ ነው።

አላህ በቁርአኑ እንደተረከልን የሙሳ (ዐሰ) ህዝቦች በፊራዑን ባርነት ለዘመናት ሲማቅቁ የኖሩ ነበሩ። እናም አላህ ከመካከላቸው ሙሳን (ዐሰ) አስነሳና ነፃ አውጥቷቸው በኋላ ወደ ሻም እንዲገቡ አደረጋቸው። ነገር ግን ሻም ድንበር ላይ ሲደርሱ ቅዱሷን (ኢየሩሳሌምን) ሌሎች ሙሽሪኮች ይኖሩባት ነበርና ‹‹ሕዝቦቼ ሆይ! ያችን አላህ ለእናንተ ያደረጋትን የተቀደሰችውን መሬት ግቡ። ወደ ኋላችሁም አትመለሱ። ከሳሪዎች ሆናችሁ ትመለሳላችሁና።›› ተባሉ። ነገር ግን ደፍሮ የሚዋጋ ጠፋ። አላህ እረዳችኋለሁ! ታሸንፋላችሁ! ቢላቸውም ፍርሃታቸው አሸነፋቸው። እናም ለሙሳ ‹‹ሙሳ ሆይ! በርስዋ ውስጥ ሀያላን ሕዝቦች አሉ። ከርስዋም እስከሚወጡ ድረስ እኛ ፈጽሞ አንገባትም። ከርስዋም ቢወጡ እኛ ገቢዎች ነን አሉት።››

በዚህ ጊዜ አላህ ፍርሃታቸውን አይቶ ‹‹ከእነዚያ አላህን ከሚፈሩትና አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሰላቸው የሆኑ ሁለት ሰዎች በእነርሱ (በሀያሎቹ) ላይ በሩን ግቡ። በገባችሁትም ጊዜ እናንተ አሸናፊዎች ናችሁ። ምእመናንም እንደ ሆናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ››አላቸው። ነገር ግን አላህ በሁለት ሰዎች ምክንያት ድል እንደሚያገኙ ነግሮ ፈተናውን ቢያቀልላቸውም እንኳን ህዝቦቹ ‹‹ሙሳ ሆይ! በውስጧ እስካሉ ድረስ እኛ ፈጽሞ ምንጊዜም አንገባትም። ስለዚህ ሂድ አንተና ጌታህ ተጋደሉም እኛ እዚህ ተቀማጮች ነን አሉት።››

ሙሳም (ዐሰ) እንደማይዋጉ ተስፋ ሲቆርጥ ‹‹ጌታዬ ሆይ! እኔ ራሴንና ወንድሜን በቀር ላስገድድ አልችልም። በእኛና በአመጸኞቹም ሕዝቦች መካከል ለይ አለ።›› አላህም የመጨረሻውን የቁጣ ውሳኔውን አሳለፈ። እንዲህም አለው፡- ‹‹እርስዋም (የተቀደሰችው መሬት) በእነርሱ ላይ አርባ ዓመት እርም ናት። በምድረ በዳ ይንከራተታሉ። በአመጸኞችም ሕዝቦች ላይ አትዘን።›› (ማዒዳህ 21-25)

እናም የእስራኤል ልጆች በፍርሃታቸው ምክንያት አርባ ዓመታት በበረሃ ተንከራተቱ። አርባ ዓመቱ ከተፈፀመ በኋላ የሹዕ መጣ። በእሱ መሪነትም እንደገና ተዋጉና ድል አደረጉ።ከተማዋንም ቁዱስን ከፈቱ።

ኡለማዎች ስለዚህ አንቀፅ ሲናገሩ አርባ አመት የአንድ ትውልድ እድሜ ነው ይላሉ። እናም አላህ በምድረ በዳ አርባ አመታት እንዲቆዩ ያደረጋቸው ያ ትውልድ እስኪያልፍ

> ”
>
> **ድል የሚፈልግ ሰው ካለ ቅድሚያ ‹‹አንችልም›› ከሚለው የዝቅተኛነት ስሜት መውጣት አለበት። የሙሽሪኮችን ሰራዊት የቱን ያህል ቢበዛም የተውሂድን ሃይል መቋቋም እንደማይችል እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። እኛ ከዚህ የዝቅተኛነት ባርነት ወጥተን ነስር እናገኝ ይሆን ወይስ እንደ ሙሳ (ዐሰ) ህዝቦች ከነፍርሃታችን ተቀብረን እንጠፋ ይሆን የሚለው ከሁላችንም መልስ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው።**

ነበር ይላሉ።ምክንያቱም በፊራዑን ባርነት ስነ-ልቦናው የተጎዳ የዝቅተኛነት ስሜት ያሸነፈው ደካማ ስለነበረ።ስለዚህ በበረሃ አዲስ ትውልድ አመጣ። ይሄ ትውልድ ባርነት ምን እንደሆነ የማያውቅ፣መገዛት የሚባል ስሜት ያልፈጠረበት ዘላን ስለነበረ በሹዓይብ መሪነት በቀጥታ ነበር ቁዱስ የገባው።

የእኛ ትውልድም ታዲያ ከሙሳ ህዝብ ጋር ተመሳሳይ ነው። የሚያውቀው የተውሂድን የበላይነት ሳይሆን የአሜሪካንን ሃያልነት ነው። ሮማዊያን በፊልማቸው፣በሚዲያቸው፣የማንበገር ሃያል ነን ሲሉ ጭንቅላቱን ሞልተውታል። አላህ ከጎናቸው ከሆነላቸው ህዝቦች ይልቅ አሜሪካና አውሮፓዊያን የደገፏቸው ህዝቦች እንደሚያሸንፉ አምኖ ተቀብሏል። ስለዚህ ከእነሱ ጋር መጋፈጥን ለማሰብም ይከብደዋል። እናም ዜናውን ሁሉ ብታዩት ሙስሊሙ ከመጠቃት ውጭ ጠላቶቹን ድል ነስቶ የበላይ የመሆን አቅም እንደሌለው እስኪታሰብ ድረስ ለቅሶ ብቻ ነው። ይህ የተጎጅነት ስሜት ደግሞ አንችልም ለሚል የሞራል ውድቀት ስለዳረገን ጠላቶቻችንን ማጥቃት ቀርቶ ሴቶቻችንን መጠበቅ እንኳን አቅቶናል።

ታዲያ አላህ ለዚህ ህዝብ እንዴት ድልን ሊሰጠው ይችላል? እንዴት በዚህ ሁኔታ የአላህን ቃል የበላይ ማድረግ እንችላለን? በፍፁም ሊሆን አይችልም። በዚህ ሁኔታ ነስር እናገኛለን የሚል ሙስሊም ካለ አላህ ድልን ለማን እንደሚሰጥ ያላወቀ ብቻ ነው።

ምናልባት ጠንካራ መሪ መጥቶ ነፃ ያወጣናል ብሎ የሚያስብ ሞኝ ካለም ይሄው የሙሳ (ዐሰ) ታሪክ እኮ በቂ ማሳያ ነው። ሙሳ (ዐሰ) በጠንካራነት ከየሹዕ ይበልጣሉ። ነገር ግን የሙሳ (ዐሰ) ህዝብ ሲጠፋ የሹዓይብ ግን አሸንፏል። ምክንያቱም አላህ ኡማው የማሸነፍን እርግጠኛነት ካልያዘ በጠንካራ መሪ ብቻ ድልን ስለማይሰጥ ነው።

ድል የሚፈልግ ሰው ካለ ቅድሚያ ‹‹አንችልም›› ከሚለው የዝቅተኛነት ስሜት መውጣት አለበት። የሙሽሪኮችን ሰራዊት የቱን ያህል ቢበዛም የተውሂድን ሃይል መቋቋም እንደማይችል እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። እኛ ከዚህ የዝቅተኛነት ባርነት ወጥተን ነስር እናገኝ ይሆን ወይስ እንደ ሙሳ (ዐሰ) ህዝቦች ከነፍርሃታችን ተቀብረን እንጠፋ ይሆን የሚለው ከሁላችንም መልስ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው።

"አላህንና መልክተኛውን እነዚያንም ያመኑትን የሚወዳጅ ሰው (ከአላህ ጭፍሮች ይኾናል)። የአላህም ጭፍሮች እነርሱ አሸናፊዎች ናቸው፡
፡"

(ማዒዳህ 56)

## ማስታወሻ

# መሪራስ አማን በላይ

በፈንታሁን ጥሩነህ



አቶ አማን በላይን የማውቀው ከ20 ዓመት ገደማ ጀምሮ ነው። እስከዚያ ድረስ የጻፏቸውንመጻሕፍትን ሆነ እርሱን እራሱን በወሬ እንኳን አላውቅም ነበር።

ዶ/ር ወሰን እንቁባህሪ ረዘም ላለ ጊዜ "መጽሐፈ ሱባዔ" የተሰኘ መጽሐፍ አውቅ እንደሆነ ወይም በምሰራበት በኮንግሬስ መጻሕፍት ቤት (Library of Congress) ይገኝ እንደሆነ በደወለልኝ ቁጥር አዘውትሮ ይጠይቀኝ ነበር። እኔም በብራና መጻሕፍት ክምችትም ሆነ በታተሙ መጻሕፍት ዘንድ እንዲህ ዓይነት ርዕስ ያለው መጽሐፍ ከስብስቡ እንደሌለ በተደጋጋሚ ስገልጽለት ቆየን። ከዕለታት አንድ ቀን በኮንግሬስ ቤተ መጻሕፍት ሕንፃ ውስጥ ባለ አንድ ምግብ ቤት ምሳ ለመብላት በቀጠሮ ተገናኝተን አንድ የግልባጭ ግልባጭ የሆነ ጽሑፍ በማጎደር የታቀፈ ሰጠኝና ቤት ስገባ ብቻ እንዳነበው ነገረኝ። እንዳለውም ከሥራ መልስ ራት በልቼ ማህደሩን ከፍቼ ማንበብ ስጀምር "የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ" በሚል ርዕስ ያላሰብኩት ከዚህ ቀደምም ሰምቼው የማላውቅ የጥንት የኢትዮጵያ ታሪክ ማንበብ ጀመርኩ።

ሥጋዬ፣ አጥንቴ፣ ደሜ፣ ነፍሴ የሚመኘው ወይም የምናፍቀው የነበረ ታሪክ በዚያ ብጥቅጥቁ በወጣ መዝገብ ውስጥ ነበረ። በወረቀቱ ዳርና ዳር ያሉት ፊደሎች ከኩረጃ ብዛት የሉም፤ ሌሉትን በሙላ እያሟላሁ ሳነብ ምሽቱ ነጋ። እንዲህ የሳበኝና የማረከኝ መጽሐፍ አጋጥሞኝ አያውቅም — ለረጅም ጊዜ። ሁለመናዬ ሳቀ፤ ተደሰትኩ። "ይህ ነው የጠፋብን ታሪካችን!" እያልኩ መገረም ጀመርኩ።

ስለ ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜ የሚረብሸኝ አንድ ምናባዊ ሥዕል አብሮኝ ይኖር ነበር። እውነተኛ ታሪኩን ባለማወቁ እውነተኛ ማንነቱ ጠፍቶበት በየሄደበት ታሪኩን ለማግኘት የሚናውዝ፤ በአጥንቱ፣ በነፍሱ፣ በጊንሱ፣ የማንነቱ ገናናነት እየታወቀው ዓለም ሳያውቀው በመቅረቱ ሲያሳንሰው ሲደቁሰው የሚኖር፤ እንደ ግማሽ እብድ እንደ አውቆ-አበድ የሚያደርገውና ስለታሪኩ ገናናነት ሊገልጽ ሲሞክር በውስጡ ያለውን አውጥቶ መናገር መግለጽ ስለሚሳነው ዓይኖቹን በማፍጠጥ በቁጣ መንፈስ ከሰው ጋር የሚጋጭ፣ የሚደባደብ፣ እርስ በርሱም አንገት ላንገት የሚተናነቅ፤ የኢትዮጵያ ስም ሲነሳ በማያውቀው ሥነ ልቦና ውስጥ ተዘፍቆ እንደ ዛር የሚያንቀጠቅጠው፤ የቁጣ ማዕበል ልገንፍልብህ፣ ልፈንዳብህ እያለ የሚያቅበጠብጠው፤ የገዛ ወንድሙን ኢትዮጵያዊውን አገሬን እንደኔ አታውቃትም፣ አትወዳትም ብሎ የሚደነፋ •••

ግን ደግሞ በተቀበረው ማንነቱ በየሄደበት፣ በየተሰደደበት ስለእውነት የሚሞት፤ በትሕትናው ራሱን ዝቅ በማድረግ በአገልግሎቱ የሚያስከብር ሥራ በመሥራት፣ በሐቀኝነቱ የተከበረ፤ ፍቅረ-ንዋይ የማይደልለው፣ አድርባይነት የማይጠጋው •••

ጋሽ ጸጋዬ ገብረመድህን ነፍሱን ይማረውና የዋሽንግተንን ከተማ በጎበኘበት በአንድ ወቅት ለእኔና ለጥቂት ሰዎች እንደገለጸልን፣

"በምዕራብ ከተሞች ሁለት እጁን በሁለት ኪሱ ከትቶ፣ ደረቱን ነፍቶ፣ በአስፋልቱ ላይ በሁለት እግሩ በእርግጠኝነት የሚራመድ፤ አሮጊት ነጮች በመስኮት ሰርቀው እያዩ 'ይህ የማነው ጥቁር በኩራት በቀያችን የሚንጎራደደው' ብለው የሚደነቁበት ያ የኛው አሎሎ ራስ ኢትዮጵያዊ ነው!"።

አማን በላይ ማለትም ከነርሱ አንዱ ነበር።

ግን አማን በላይ ደግሞ ከነዚህ ዓይነት ኢትዮጵያውያን ለየት የሚያደርገው ባህሪ አለው። የትምህርት ጥማት ስለነበረው በወጣትነቱ ከቤተሰቡ ተለይቶ ለረጅም ዓመታት ከደብር ደብር እየተዘዋወረ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ልቅም አድርጎ ተምሯል። ቤተሰቦቹ ለዘመናት ስለጠፋባቸው ጫካ ለጫካ ሲሄድ አውሬ በልቶት ይሆናል ብለው እርግጠኛ በመሆን እርማቸውን በለቅሶ ካወጡ ከሰላሳ ዓመት በኋላ በሕይወት እንዳለ እንዲያውቁ አድርጓል።

ይህን ያህል ዘመን ለዕውቀት ከጠቅላይ ግዛት ወደጠቅላይ ግዛት በተዘዋወረበት ረጅም ዘመን ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጋርም ተገናኝቷል። በቤተክርስቲያኗ የተለያዩ ቦታዎች ያሉትንም ብርቅ መጻሕፍት ለማወቅ ዕድል አግኝቷል። ከነዚህም ብርቅ መጻሕፍት አንዱ "መጽሐፈ ሱባዔ" የተሰኘው ይገኝበታል። ይህን መጽሐፍ በዓይኔ ባላየውም ከጥንታዊ

ወደ ገፅ 29 ዞሯል

ገብርኤል ዳንኤል

# ጤናን የሚያውኩ የእድገት ሂደቶች

ክፍል 2



ኢትዮጵያ አሁን የተያያዘችው ራሷን ከድኅነት በማላቀቅ ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ስትቆርጥ ዋንኛው አቅጣጫ ኢንዱስትሪና ዘመናዊ ግብርና መሆኑ ተጠቅሷል። እነዚህ የእድገት እርምጃዎች፣ ግዙፍና መካከለኛ ማምረቻዎችን ማቋቋም፣ ግድቦችን መገንባት፣ መስኖን ማስፋፋት፣ ማዳበርያንና ፀረ ህዋስ ንጥረ ነገሮችን መጠቀም ወዘተ… ላይ ያተኮረ ነው። ከጤና አንፃር እነዚህን በመተግበር ጊዜ የሚወጡ አላስፈላጊ ውጤቶች አካባቢን ብሎም ህብረተሰቡን የመበከል ጎጂ ጎን ሊኖራቸው ይችላል። ከዚህ በፊት በተለያዩ ሀገራት ከነዚህ ዓይነት ክስተቶች የተነሣ የበሽታ መስፋፋት (እንደ ቢላሀርዚያ እና ወባ)፣ የአየር፣ የውሃ፣ የአፈር፣ የከርሰ ምድር ህይወት ጉዳት ታይተዋል። በኢትዮጵያ የአበባ እርሻ በተስፋፋበት ወቅት የተከሰተውና የቆዳ ፋብሪካ ፍሳሾች ያስከተሉት የአካባቢና የወንዞች ብክለት የቅርብ ጊዜ ትዝታዎቻችን ናቸው። መንግሥት ለእንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮች ጥንቃቄ፣ጥናት፣ ሕግና፣ ቁጥጥር ላይ ትኩረት ካልሰጠ በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማስከተሉና እስካሁን የተገኙ ውጤቶችን የሚጎዳ መሆኑ አይቀርም።

> ”
>
> **በድኅነት፣ በሥራ እጥነትና በቤት እቅራቦት ችግር ምክንያት በአንድ ቤት ውስጥ ተጣበውና ተፋፍነው የሚኖሩ በርካታ ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ሲሆን፣ ከዚህ የተነሳ የተለያዩ የጤና ችግሮች ይከሰታሉ። ዋንኛ የበሽታ መተላለፊያ መንገድም ነው። በነዚህ ዙርያ ሰፊ ጥናት፣ የህብረተሰብ ግንዛቤና የመንግሥት ሚና ከፍ ሲል ይገባዋል።**

ሌላው ጤና ላይ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተፅእኖ የሚያሳይ ሁኔታ ቁጥጥር የጎደላቸው፣ ዕድሜያቸው ያበቃ፣ ጥራታቸው ያልተረጋገጠ፣ በሙስና የሀገር ድንበር ጥሰው የሚገቡ መድኃኒቶች፣ የጤና መገልገያዎች፣ ምግቦች፣ መጠጦች ወዘተ… መኖራቸው ነው። እነዚህ ጥቅም አልባ ከመሆናቸው በስተቀር፣መጠኑና ዓይነቱ የማይታወቅ የጤና መታወክ ያስከትላሉ። ጥራት የጎደላቸው ወይም የአገልግሎት ዕድሜያቸው ያበቃ መድኃኒት፣ ምግብ ወዘተ… ጠቃሚነታቸው አጠያያቂ፣ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ መርዛማነት የሚያሳዩ መሆን ይችላሉ። ከዚህም አልፎ ብቃታቸው ያልተረጋገጡት መድኃኒቶች ሲወሰዱ ጀርሞቹ መድኃኒቶቹን በመላመድ የፀረ ህዋስ አለመበገር (አንቲ ማይክሮብያል ሬዚስታንስ) ይፈጠራሉ። ይህ ደግሞ ብዙ ሚሊዮኖች ዶላር ወጥቶባቸው የተመረቱ መድኃኒቶች ጥቅም አልባ ይሆናሉ ማለት ነው። በኢትዮጵያ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በምን ደረጃ ላይ እንዳለና ምን መፍትሔ እየተሰጠው እንዳለ በቂ ጥናት ያለ አይመስልም።

ሌላው ተግዳሮት ተብሎ የሚጠቀሰው ጥቅም ላይ የማይውሉትን ነገሮች የማስወገድ ወይም መልሶ ሥራ ላይ ማዋል (ሪሳይክል) የማድረግ ጉዳይ ነው። እነዚህን ጥቅም አልባ ነገሮች ሳይንሱ በሚፈቅደው መንገድ ለማስወገድ በኢትዮጵያ መመሪያው ቢኖርም ተግባራዊነቱ ደካማ ነው። በብዛት የሚታየው ክስተት ቁጥጥር በጎደለው መንገድ በተቆፈሩ ጉድጓዶች ማቃጠል፣ ያለአግባብ በየቦታው መጣል ወይም በየወንዙ መድፋት ነው። በተገቢው መንገድ ያልተወገዱ ጥቅም አልባ ነገሮች የአየር፣ የከርሰ ምድር ውሃና የአካባቢ ጤናን በመበከል ተጨማሪ ጉዳት ያስከትላሉ። በኢትዮጵያ እነዚህን በተገቢው መንገድ ማስወገድ አቅሙ በጣም የተወሰነ ነው። በተጨማሪም አሳሳቢነቱ ስለጉዳዩ ያለው ግንዛቤ በህብረተሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ መሆኑ ነው። የተለያዩ ንጥር ነገሮች የተለያዩ የማስወገድ ዘይቤ ይጠይቃሉ። አንዳንዶቹ ንጥረ ነገሮች ልዩ የማስወገጃ ዘዴዎች ስለሚጠይቁ ወደ ሌላ አቅም ያላቸው ሀገራት ተልከው መወገድ ያለባቸውም ይገኛሉ። መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሥራት በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ የሚያደርገው ቁጥጥር፣ የማስወገድና መልሶ መጠቀም እርምጃ በከፍተኛ መጠን መጨመር

ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌም በአዲስ አበባና በክልሎች እንዲሁም ተጠቃሚ ድርጅቶች በርካታ ጥቅም የማይሰጡ ነገሮችን ማስወገድ እንደሚቻል ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት ተመክሮዎችን መመልከቱ ጥቅም አለው፡፡

ኢትዮጵያ ከምታደርገው የከተሞች ዕድገት፣ የከተማ ኗሪዎች መብዛት የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ እንዲሁም የተለያዩ የማምረቻ ተቋሞች አንፃር፣ የፍሳሽ፣ የፅዳት፣ የውሃ፣ የመብራት፣የቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎቶች ማሟላት ተቀዳሚ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይህን ለማሟላት የተወሰደው ወይም እየተወሰደ ያለው እርምጃ ምን ያህል እንደሆነና ስኬቱስ ምን ያህል እንደሆነ ጥሩ ጥናት ይጠይቃል፡፡ በቅርብ የሚታዩትም ሆኑ የሚሰሙት ብሶቶች እንደሚያሳዩት ብዙ መሠራት እንዳለበት ነው፡፡

በቅርቡ በአዲስ አበባ ረጲ አካባቢ በዘልማድ ቆሼ በሚባለው የቆሻሻ መጣያ ቦታ ላይ የደረሰው ያለመጠን የተከመረው ቆሻሻ መደርመስና መናድ ከስሩ ተጠግተው በሚኖሩ 114 ግለሰቦች ህይወት መጥፋቱን መንግሥት አስታውቋል፡፡ በዚህ ስፍራ በርካታ የቆሻሻው ተቋዳሽ የሆኑ ችግረኞች ቆሻሻ ውስጥ የሚያገኙትን ምግብና ሌላ የወደቁ ነገሮችን ለመጠቀም ሲሰበስቡ ማየት እጅግ የሚያሳዝንና የሀገሪቱን ሌላ ገፅታ የሚጠቁም ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ የደረሰው የህይወትና የንብረት መጥፋት የአስተዳደር ጉድለትና በጊዜው ተገቢውን እርምጃ ያለመውሰድ ውጤት መሆኑ ይገመታል፡፡

በአዲስ አበባ የመንገድ ቆሻሻን በመጥረግ፣ ከየቤቱ በመሰብሰብና ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ በመውሰድ፣ አሮጌ ዕቃዎችን ከየሰፈሩ በመግዛትና በመሸጥ (ቁራሌ ወይም ቆርቆሮ ያለው! በመባል የሚታወቁ)፣ ምናለሽ ተራ መርካቶ የተለያዩ አሮጌ ዕቃዎችን በመሸጥ ኑሮአቸውን የሚገፉ በርካታ ናቸው፡፡ ይህን ግን በሚያደርጉበት ወቅት ያለምንም የአደጋ መከላከያና ጥንቃቄ ስለሆነ ለተለያዩ በሽታዎችና አደጋዎች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ከመሆኑ በተጨማሪ እራሳቸው የበሽታ አስተላላፊዎችም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህን በሚመለከት በተለያዩ ግንባታና ፣ ፋብሪካ የሚሠሩ ሁሉ ጤናቸውን ለመጠብቅ ይህ ዓይነቱ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልጋቸው የተሟላ ግብአት ሊስተካከልላቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በፊት እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሠራተኞች ለመርዳት ተቋቁሞ የሚሠራ በጎ አድራጎት ድርጅት ዘርፈ ብዙና ጥሩ ውጤቶች እንዳሳየ ቢታወቅም ከዚህ የተገኘው ተመክሮ ምን ያህል በሀገሪቱ እንደተዛመተ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

ከከተማዎች መስፋፋትና ኗሪዎች መብዛት ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ቤቶች የውሃ፣ የመፀዳጃና የቆሻሻ ማስወገጃ አቅርቦት ችግር እንዳለ በሰፊው ይሰማል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ቀንደኛዋ የፅዳት ጉድለት የሚታይባት ሀገር ናት፡፡ ይህ የአፍሪካ አንድነትና የብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ ለሆነችው ኢትዮጵያ ጥሩ መገለጫ አይደለም፡፡ የምእተ ዓመቱን ልማት የውሃ አቅራቦት 57% ግብ አሟልታለች ቢባልም የተቀረው 50 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ አሁንም የንፁህ ውሃ ተጠቃሚ አይደለም፡፡ መፀዳጃን በሚመለከት 28% የሚሆነው ሕዝብ ብቻ ነው መሠረታዊ በሚባል ደረጃ መፀዳጃ የሚገለገለው፡፡ ሌላው ለጤና አደገኛ በሆነ መንገድ ይፀዳዳል ማለት ነው፡፡ይህ ደግሞ ቀጥተኛ የሆኑ ውሃ አዘል የጤና ችግሮች (እንደ ኮሌራ ወይም አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት፣ አተት)፣ በዓለም ቀዳሚ የዐይን መታወር የሚያስከትለው ትራኮማ ወዘተ… ላሉ በሽታዎች ሕዝቡን ሰለባ ያደርጋሉ፡፡ ቤቶች ሲሠሩ ግንባታው ብቻ ሳይሆን ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት አገልግሎቶች የግንባታ ፈቃድ ከመሰጠት ጋር የተቆራኙ ግዴታዎች መሆን ይገባቸዋል፡፡

በቅርቡ የተጀመረው የደረቅ ቆሻሻን ለኃይል ማመንጫ መጠቀም ጥሩ ጅምር ሲሆን፣ ይህን ተመክሮ በመላው ሀገሪቱ ማስፋፍት ለጤና ጎጂ የሆነን ቆሻሻ ከበካይነት አውጥቶ ወደ ጠቃሚ ኃይል መቀየር ወይም የገቢ ምንጭ ማድረግ እሰይ የሚያሰኝ ጅማሬ ነው፡፡ ሌላው መስፋፋት ያለበት ተመክሮ በአዲስ አበባ በየአካባቢው የተጀመረው የህብረተሰቡ የቆሻሻ ማስወገድ ቀን መወሰኑ ነው፡፡ በርከት ያሉት ውሳኔዎችና ሙከራዎች በተፋጠነ ሁኔታና በስፋት በየአካባቢው ካልተዛመተና በድርጊት ካልተደገፈ ከይስሙላነት አያልፍም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ያለበት የሕዝቡን ስነ ልቡና መቀየርና በትምህርት ማነፅ ነው፡፡ ሕዝቡ የቆሻሻን የጤና ጎጂነትና ፀረ ቆሻሻነትን ባህሉ ማድረግ ላይ ብዙ ካልተሠራ ጊዜያዊና ቁንፅል ድርጊቶች ብዙም አያስኬዱም፡፡

ሌላው ከእድገት ጋር ተያይዞ የሚታየው ተግዳሮት፣ የተሽከርካሪዎች መብዛት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ተሽከርካሪ ብዛት ባጠቃላይ እጅግ ዝቅተኛም ቢሆን ካሁኑ ተገቢው ቁጥጥርና ሕግ ካልታሰበበት ለወደፊት ብዛቱ ሲጨምር ችግሩ ቀላል አይሆንም፡፡ እንደ ቀልድ ተደርጎ የተነገረ ነገር አለ፤ የጂቡቲው ፕሬዜዳንት ጉሌድ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስን ሲጠይቁ፥ “እንዴት ነው ይሄ ሁሉ መኪና በየጊዜው በጂቡቲ ኢትዮጵያ የሚገባው? ሕዝቡ መኪና ነው የሚበላው?” ብለው ጠየቁ ይባላል፡፡

ይህ ቁም ነገር አዘል ቀልድ የጉዳዩን ትኩረት ይጠቁማል፡፡ በሀገሪቱ 900,000 ገደማ ተሽከርካሪዎች ብቻ ሲኖሩ፣ በዓመት እስከ 8,000 መኪናዎች ሀገር ውስጥ እንደሚሠሩ፥ እንደሚገጣጠሙ ይሰማል፡፡ በብዛት ከውጭ የሚገቡት ደግሞ አዲስ ሳይሆኑ ጥቅም ላይ የነበሩ ናቸው፡፡ የተሽከርካሪ ታክስ አንዳንዴ ከመኪናው ዋጋ ጋር እኩል ስለሚሆን ሕዝቡ የረከሱትን መግዛት ይመርጣል፡፡ በኢትዮጵያ እስከ አርባ ዓመታት ያስቆጠሩ ዕድሜ ጠገብ መኪናዎች አሁንም አገልግሎት የሚሰጡ አሉ፡፡ ባለፉት ዓመታት ደግሞ ባጃጅ የሚባሉ ባለሦስት ጎማ በህንድ የተሠሩ ተሽከርካሪዎች ሀገሪቱን አጥለቅልቀዋታል፡፡ በቅርቡ ወደ ሀገር በየወሩ የሚገቡት ባጃጆች ቁጥር እስከ 8,000 ነው ይባላል፡፡ ከነዚህ ተሽከርካሪዎች የሚወጡ ጭሶች አደገኛ ጋዞችና ጥቃቅን ብረታማ ነገሮች ከፍተኛ የአየር ብክለትና የጤና መታወክ ያስከትላሉ፡፡ እንደ ብሮንካይተስና አስም ያሉ በሽታዎች መንስኤና ማባባሻም ናቸው፡፡ የካንሰርም ምክንያት የመሆን አደጋ አላቸው፡፡ ከኤታኖል አልኮል ጋር የተደባለቀ ነዳጅ በሀገሪቱ ጥቅም ላይ መዋሉና ብክለትን ይቀንሳል ቢባልም ጥቅሙ ውስን ከመሆኑ ሌላ የተሽከርካሪዎቹ ዕድሜና ዓይነትም ጥቅሙ ላይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ብዙ ሰዎችን የሚጭኑ የከተማና ሀገር አቋራጭ፣ እንደ አውቶቢሶች፣ ባቡር ወዘተ ያሉ ማጓጓዣዎችን ማስፋፋትና መንገዶችን በሰፊው መገንባት እንዲሁም የአነዳድ ስነ ሥርዓትን ማስተማርና ማስከበር አዎንታዊ የጤና ውጤቶች ከሚያመጡ እርምጃዎች ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡ በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነው “ላይት ሬል” የከተማ ባቡር ጥሩ ጅምር ሲሆን ከናሙናዊነቱ መዝለል ይጠበቅበታል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በርካታ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡ ጥቅም ላይ የማይውሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በተገቢው መንገድ ማስወገድ ችሎታ በሀገሪቱ ያልዳበረ በመሆኑ በአልባሌ መንገድ ስለሚወገዱ ሊያስከትሉ የሚችሉት የጤና አደጋ በዓይነትና ውጤት ሊገመት አይችልም፡፡ በዚህ ላይ ጥናትና ቁጥጥር መደረግ ያለበት አስቸኳይ ጉዳይ ነው፡፡

በድኃነት፣ በሥራ አጥነትና በቤት አቅራቦት ችግር ምክንያት በአንድ ቤት ውስጥ ተጣበውና ተፋፍነው የሚኖሩ በርካታ ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ሲሆን፣ ከዚህ የተነሳ የተለያዩ የጤና ችግሮች ይከሰታሉ፡፡ ዋንኛ የበሽታ መተላለፊያ መንገድም ነው፡፡ በነዚህ ዙርያ ሰፊ ጥናት፣ የህብረተሰብ ግንዛቤና የመንግሥት ሚና ከፍ ሊል ይገባዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን የምትገኝበት ፈጣን የእድገት ሁኔታ በዓለም ካሉ ሀገራት ጭራነት መውጣት ሲሆን፣ የመንግሥት ትኩረት፣ የምሁራኑና የህብረተሰቡ ተሳትፎ ጤናን በመንከባከብ፣ በሽታን በመከላከል፣ ግለሰብን ያማከለ፣ ውጤት ተኮር፣ ጥራት የተሞላበት፣ ቀጣይነቱ የተረጋገጠ እርምጃ መሆን ጊዜ የማይጠብቅ ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በርካታና ሰፊ ከመሆናቸውም በስተቀር ብዙ ወጪ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ የአንድ ሀገር ሃብቱ ሕዝቡ ስለሆነ ሁለንተናዊ ጤንነቱን ማረጋገጥ ደግሞ የመንግሥት ዋንኛ ግዴታው ነው፡፡

# ሀበሻ የገና ኤክስፖ በበርካታ ህዝብ እየተጎበኘ ነዉ



በወጣቶች የሚመራዉ ሀበሻ ዊክሊ ፕሮሞሽን በሀገራችን ታላላቅ ስራዎችን በመስራት ወደፊት እየገሰገሰ ያለ ድርጅት ነዉ። ይህ ድርጅት በዚህ አመት የገና እና የፋሲካ ኤክስፖ ጨረታን አሸንፏል። ከታህሳስ 6 አንስቶም ሀበሻ ገና ኤክስፖን በኢግዚብሽን ማእከል እያካሄደ ነዉ።

በዚህ ኤክስፖ ዙሪያ የድርጅቱን የስራ ሀላፊዎች ለማነጋገር ወደ ኢግዚብሽን ማእከል ባቀናንበት ጊዜ ብዙ አስደማሚ ነገሮችን ተመልክተናል። የኢግዚብሽን ማእከሉ አዳራሾችና ግቢዉ ሙሉ በሙሉ አገልግሎታቸዉን በሚያስተዋውቁና በሚሸጡ ድርጅቶች ተሞልቷል።

በጣም በርካታ ሰዎች ለግብይት ፣ለሽመታ ወደ ማእከሉ ሲያቀኑ ተመልክተናል። በዓሉ የተወሰኑ ቀናት ቢቀሩትም በእግዚብሽን ማዕከሉ ዉስጥ የሚስተዋለዉ ነገር ግን በዓል ነገ ወይንም ከነገ ወዲያ የሆነ ነዉ የሚመስለዉ፡ ፡ የሀበሻ ዊክሊ የአስተዳደር ሀላፊ ናትናኤል ኢቲቻ ለአሃድ መፅሔት እንደገለፀዉ ሀበሻ ዊክሊ የገናንና የፋሲካን ኤክስፖ ጨረታ ያሸነፈዉ በሀምሳ ሚሊዮን ብር ነዉ።

አሁን እየተካሄደ ባለዉ ሀበሻ ገና ኤክስፖ ላይ ከሀገር ዉስጥ ከአምስት መቶ በላይ፣ ከዉጭ ደግሞ ከሁለት መቶ በላይ ድርጅቶች መሳተፋቸዉን ናትናኤል ኢቲቻ ተናግሯል፡ ፡ ‹‹ኤክስፖው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሞቅ ደመቅ ባለ መንፈስ እየተከናወነ እንደሆነ የሚገልፀዉ ናትናኤል በየቀኑ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ሰዉ ወደ ኤክስፖው እየመጣ ነዉ›› ብሏል።

አሁን አሁን በዓላት ሲመጡ ኢግዚብሽንና ባዛሮች የማዘጋጀት ልምድ እየጨመረ ሲሆን ሰዎችም ለግብይት እነዚህን ቦታዎች ሲመርጡ ይስተዋላል። ‹‹በኢግዚብሽንና ባዛሮች ላይ ግብይት የማድረጉ ጥቅም አንድ የተለያዩ እቃዎች በአንድ ቦታ ላይ ተሰብስበዉ መገኘታቸዉ፣በሌላ በኩል ደግሞ በቅናሽ ዋጋ የሚፈልጉትን እቃዎች ሰዎች እንዲያገኙ እንደሚያስችል›› ናትናኤል ይገልፃል።

በዚህ በሀበሻ የገና ኤክስፖ ከግብይቱ፣ ከድርጅት ትውውቁ ባሻገር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ቦታ ተሰጥቷቸዉ ስለ ስራቸዉ ሲያስተዋውቁ አስተዉለናል። ናትናኤል ኢቲቻም እንደገለፀዉ ሀበሻ ዊክሊ ስምንት መቶ ሺ ብር የሚተመን ቦታን ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሰጥተናል። ከዚህ ባሻገር ማህበራዊ ሀላፊነታችንን ለመወጣት ለተለያዩ አካላት ድጋፍ አድርገናል›› ብሏል።

ሀበሻ ዊክሊ በሚያዘጋጀዉ ኢግዚቢሽኖች ላይ ለየት ለየት ያሉ ነገሮች ይዞ በመቅረብ ይታወቃል። በዚህ በገና ኤክስፖም ‹‹ ጀርስክ ፓርክ›› የተሰኘ ፓርክን በኢግዚቢሽን ማዕከል ዉስጥ በመገንባት በፓርኩ ዉስጥ የዳይኖሰር ትዕይንት እንደሚታይ፣ ለህፃናትም ልዩ የመጫወቻ ስፍራዎች መዘጋጀታቸዉን ናትናኤል ኢቲቻ አስታዉቋል።

በኤክስፖው የመግቢያ ትኬት ላይ በየቀኑ የተለያዩ እጣዎች እየወጡ እድለኞች ሽልማቶቻቸዉን እየወሰዱ እንደሚገኙ ናትናኤል ለአሃድ መፅሔት ገልፃዋል።

በሀበሻ ዊክሊ ገና ኤክስፖዉ ላይ በመዝናኛ በኩል ለ23 ቀናት የሙዚቃ ኮንሰርት እንደሚካሄድ ፣ በዚህ ኮንሰርት ላይ አንጋፋና ወጣት ድምፃዊያን እንደሚሳተፉ ፣የዘጠኝ ዲ ሲኒማ ፣ነፃ የዋይፋይ አገልግሎትት ፣ የሰርከስ ዝግጅቶች እየቀረቡ መሆናቸዉን የገለፀዉ ደግሞ የሀበሸ ዊክሊ የህዝብ ግንኙነትና የፕሮሞሽን ክፍል ሀላፊ ሳምሶን ሺፈራዉ ነዉ።



ahadmegazine18@gmail.com

አሃዱ
ሳምንታዊ መፅሔት
ቅፅ. 1 - ቁ.13 ታህሳስ 2011

# ባህልና ሕዝብ

(ደርጋ መንግሥቱ እስጢፋኖስ)



የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከ81 (ሰማንያ አንድ) በላይ የሆኑ የብሔር፣ የብሔረሰብና የማህረሰብ ቅንብር ያላት መሆኑ ግልጽ ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ አባላት ብቻ ካላቸው ባህላቸውና የዘርያቸው ሐረግ ሊዋጥና — ጨርሶም ሊጠፉ ጥቂት ከቀራቸው ማህበረሰቦች አንስቶ፣ ብዙ ሚሊዮን አባላት እስከ ላሏቸው ሀያልና ሠፋፊ መሬት እስከ ያዙት የኦሮሞና የአማራ ብሔሮች ባህሏን የሚያበለጽጉና ሕብረሰባዊነቷን የሚያጠናክሩ፣ ሕብሯን የሚያሞሽሩ ህዝቦች የሚኖሩባት አገር ነች።

ምልዓተ ፀጋዋና ባህላዊ ብልጽግናዋ በመላ አፍሪካ ተወዳዳሪ የሌላት ኢትዮጵያ፣ እንደ ዛሬው አይበለውና በቀድሞው የዓለም የታሪክ ማኅደሮች ተደጋግማ ስትወሳ የኖረች ነች። መወሳትም ሳይሆን፣ በማይለቅ ቀለም ተከትባ ትገኛለች። ፍፁምና ዘለዓለማዊ ታሪክ ካላቸው ጥቂቶች የቀድሞው የጥንታዊው ዓለም አገሮች መካከል ተጋና የተተረከች አገር ነች።

የሰው ልጆች ታሪክ መተረክ፣ ሥዕል መጫጫርና፣ ጽሑፍ መጻፍ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የእነዚህ ጥንታዊ ጥበቦች አፍ መፍቻና ጣት ማንቀሳቀሻ የሆነችው ኢትዮጵያ ነች። ከግሪክ የአምልኮ ትረካ (ሚቶሎጂ) እስከ ሮማይስጣዊ ሥልጣኔ፣ ከዚያም መካከል በዘመን ወርድ በተረባረቡት ክፍላተ ዘመን በጽርዕ (ጥንታዊ ግሪክ)፣ በእብራይስጥና በላቲን፣ ከዚያም በዓረብኛና በሌሎች የዕድገት ለጣቂ ቋንቋዎች የተጻፉ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የባሕል፣ የጦርነትና የሌሎች ጽሑፎች አዛይ መጻሕፍት ውስጥ ኢትዮጵያ ያልተጠቀሰችባቸው የጥንት መጻሕፍት የሉም። ይህች ምኑም የማይሻር ታሪካዊ ዝናና ምሩጽ ስም፣ ማንም ሆነ ምን ዝቅ ሊያደርገው የማይችል ትልቅነት ያላት አገር በእነዚሁ ዘመናት ውስጥ የሕዝቧን ባህል ስታበለጽግ ኖራለች። ከማሕበረሰቡ እስከ ብሔር ስፋት ያለው ሕዝብ በፍቅር ግዛቱን አስከብሮ፣ ባህሉን አበልጽጎ፣ ሁሉም አካሏ በዘመናት ርዝመት በፈፀማቸው የተከበሩ ተግባሮች ተኩራርቶ ኖሯል።

ኢትዮጵያ ከዕውቅና ሥራዓታዊ ሃይማኖት እስከ- ባህላዊ ዕምነት ያለው ሕዝብ ሲኖራት፣ ከዓላማውያን እስከ ክርስቲያን- በአንፃሩም፣ እስከ ቤተ እሥራኤላዊ ሃይማኖት የሚከተሉ ሕዝቦቿ በየበኩላቸው ለባህሏ ይህ ነው የማይባል አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል። በረከታቸውም አላቋረጠም።

በዘመኑ የሚገኙት በየክፍላተ ዘመን የተሠሩ በዕድሜ የገፉ ቤተ ክርስቲያናትን ግድግዳዎችና አኅበሮች የበለጸጉ ጥንታዊ ሥዕሎች፣ የዋሻ ምስሎች፣ ከአለት ተወቅረው፣ ከቋጥኝ ተፈልፍለው የቆሙ ሓውልቶች፣ በልዩ መልክ ታንጸው የተሰሩ መንበረ ዕምነቶች፣ በብራና ላይ የተከተቡ ጽሑፎች፣ ልዩ ቅርጾች ከዚያ ታላቅና ጥንታዊ ሕብረተሰብ ልጆች ተሠርተውና ተጠብቀው የተገኙ እና የኖሩ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማንኛውም የዓለም ሕብረተሰብ ይልቅ — ለብዙ ሺህ ዘመናት የራሱ የሆነ፣ በዓይነቱ የበዛና የተለያየ የቤት ውስጥ፣ የማዕድ ቤት ፣ የአዳራሽ፣ የእልፍኝና የመስክ መጠቀሚያ ቁሳቁስ የነበረውና ያለው፣ ለብዙ ሺህ ዘመናት የእርሻ፣ በአደን፣ የደንበኛ ጦር፣ የወግና የማዕረግ፣ የአዘቦት መሣሪያና ትጥቅ የነበረውና ያለው ነው።

የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የራሱ የሆነ የአለባበስ፣ የአጋጌጥ፣ ከወንድ፣ ከሴት፣ ከሕጻናት እስከ ጎልማሳ የፀጉር አሠራር ደንብና ፈሊጥ (ፋሽን) የአደባባይና የመስክ አለባበስ ወግና ሥርዓት ያለው፣ ከሌላው ዓለም ሕዝብ ተለይቶ ሲታወቅ የኖረ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ልማድና የአኗኗር ሥርዓት ለራቀው ለሚያስቀና ለቀረበውም ባለቤት ለሆነው ወገን የሚያኮራ፣ መታፈሪያ፣ መታደጊያ የሚሆን ነው። የሕዝቡ ልዩ ልዩ ባህላዊ ቅርስ ብሩህ ታሪካዊ መነሻና ፈለግ ያለው፣ ሲወርድ

ወደ ገፅ 26 ዞሯል



ድንቃየሁ መኮንን

# የሚራዘመዉ ምርጫ እና ጦሱ

election

2012

በአንድ ወቅት ንብ እኮ እዚህ ወረዳ ላይ ያለ አንድ ተቃዋሚ አሸነፈ እየተባለ ሲወራ የሰሙ አንድ ግለሰብ በወሬ ብቻማ አላምንም ብለዉ ድምጽ የሰጡበት የምርጫ ጣቢያ በመሄድ ካረጋገጡ በኃላ ቤታቸዉ እየተመለሱ ‹‹ዉይይይ እኔ መች ንብን መርጬ ነዉ በሙሉ ድምጽ አሸነፈ የተባለዉ? እኔ የመረጥኩት ሌላ›› እያሉ ብቻቸዉን እያጉተመተሙ ተመለሱ ፡፡ እኚህ ግለሰብ በወቅቱ ሌሎች ጥያቄዎችን ቢያነሱ የሚደርስባቸዉ እንግልት የዋዛ አለመሆኑን በማሰብ ይመስላል ዉይይይ በምትል አስተዛዛቢ እና የቁጭት መልክ ያላት ቃል በመሰንዘር ብቻ ያለፉት፡፡

የምርጫ ስርአት በኢትዮጵያ ደስ የማይል ታሪክ ካላቸዉ ጉዳዮች ዉስጥ የሚመደብ እንደሆነ ብዙዎችን ያስማማል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በሀገር ዉስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጨምሮ ምርጫን ለመታዘብ ከዉጭ የመጡ የተለያዩ ድርጅቶችም በሀገራችን ይካሄድ የነበረዉ ምርጫ ፍትሀዊነት እና ግልጽነት የጎደለዉ ከመሆንም በላይ መጭበርበር የበዛዉ ነዉ በሚል ሳያስደስታቸዉ ማለፉን ከምናያቸዉ እና ከምናነባቸዉ ሪፖርቶች ለመረዳት አይከብድም፡፡

ህዝብ የፈለገዉን መርጦ ለማስቀመጥ ያልታደለባት፣ ልምረጥ ወይም አልመረጥ ቢሉ እንኳዋን የተለያዩ ፓርቲዎች እና ግለሰቦች እንዲሽመደመዱ በተለያየ መንገድ ተሸብበዉ እየኖሩ በተቃራኒዉ ደግሞ የህዝብ የሆነን ወንበር ፣ሀገር እንዲሁም ስልጣን የሙጥኝ ብለዉ ከዘራ እስኪይዙ መቆየትን የሚሹ በርካታዎች ተሰብስበዉባት ዛሬን በተለይ ለአሁኑ ትዉልድ አስቸጋሪ አድርገዉት እንመለከታለን፡፡

ከ1983 ጀምሮ ሲቃወም የነበረ ተፎካካሪ ፓርቲ ዛሬም ፉክክር ላይ ነዉ፡፡ ጥያቄዉ ፉክክሩ ላይ አይደለም፣ መፎካከሩ መልካም ሆኖ ለወጣቱ የመልቀቅ ፍላጎት ቢኖር መልካም ነዉ፡፡ ወጣቱ ለዉጥ ፈላጊ እንደሆነ ማናችንም የምንስማማበት ነዉ፡፡ አሁን ለሚታየዉ ጭላንጭል እንኳዋን የወጣቱ ድርሻ ቀላል አይደለም፡፡ ለዉጥ መንግስት ላይ ብቻ ሳይሆን ተፎካካሪዎች ላይም መታየት እንዳለበት የአብዛኛዉ እምነት እንደሆነ አስባለሁ፡፡

በአለም ላይ ብዙ አይነት የምርጫ ስርአቶች እንዳሉ እሙን ነዉ፡፡ በየሀገሩ ያላቸዉ ቅቡልነት ግን እንደየ ሀገሩ ስርአት ይለያል፡፡ አንዳንዶቹን ለግንዛቤ ያክል ለመጥቀስ፣ የአብላጫ ድምጽ ያለዉ ተፎካካሪ መንግስት የሚመሰርትበት አንዱ ስርአት ሲሆን፣ በዚህ ስርአት ዉስጥ ደግሞ ሌሎች በዝርዝር ሊቀመጡ የሚችሉ የምርጫ ስርአቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም ከ58 ሀገራት በላይ የሚሆኑ በቀድሞ የአሜሪካ እና የእንግሊዝ ግዛት ዉስጥ በነበሩ ሀገራት ዘንድ የሚተገበሩ እና ተቀባይነት ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ የአብላጫ ስርአት በጥቅሉ ስንመለከተዉ አንድ መንግስት ለመመስረት በምርጫ አብላጫ ድምጽ ያገኘ ፓርቲ መንግስት የመመስረት ሀላፊነት የዚህ ፓርቲ ይሆናል፡፡

ሌላ ስርአት በፓፓዋ ኒዉ ጊኒ እና አዉስትራሊያ የሚታወቁበት ሲሆን በሀምሳ ሲደመር አንድ ድምጽ መንግስት ምስረታ ላይ ያተኩራል ፡፡ ይኸዉም ከግማሽ በላይ የሚሆነዉ ድምጽ ሰጪ ለአንድ ተፎካካሪ ፓርቲ ድምጽ ሊሰጥ ግድ ነዉ፡፡ የተሰጠዉ ድምጽ ከሀምሳ በላይ ካልሆነ እንደገና ምርጫዉ እንዲካሄድ የሚደረግበት መንገድም አለ፡፡ እነዚህን እንደ አብነት አነሳሁ እንጅ ሌሎች እንደተመጣጣኝ (proportional) የምርጫ ስርአት እንዲሁም ቅይጥ (mixed) የተባሉ የምርጫ ስርአቶችም አሉ፡፡

ምርጫን ሁሉን አቀፍ እና ቀጥተኛ በሚል መርህ ያስቀመጠዉ የአዋጅ ቁጥር 532/2007 በአንቀጽ 25 ላይ በአንድ የምርጫ ክልል ዉስጥ ከሚወዳደሩ እጩዎች ዉስጥ አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ እንደሆነ ገልጾታል፡፡ ይህም ሀገራችን ከምትከተለዉ ስርአት የአብላጫ ድምጽ ስርአትን ነዉ ብሎ ለማለት ያስደፍራል፡፡

ይህን ያክል ስለ ሀገራችን የምርጫ ስርአት

ወደ ገፅ 17 ዞሯል

# ደብረፂዮንም…

## ከገፅ 16 የዞረ

የትም ቦታ በሰላም እኖራለሁ ብሎ ማሰቡ ከንቱ ምኞት ነዉ። በተጨማሪም ሰፋ ያለ ክስም እንደሚዘጋጅበት ላረጋግጥልሽ እችላለሁ።

**አሃድ፡- ትግራይ አሁን ላይ ከፌደራሉ መንግስት ያፈነገጠች ትመስላለች በዚህ ላይ ምን አስተያየት አልዎት?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እነዚህ ሰዎች እራሰቸዉን እዛ ስለወሸቁ ትግራይ ከኢትዮጵያ አካልነት ተለይታለች የሚለዉ እነርሱ እራሳቸዉን ከፍከፍ አድርገዉ ለማሳየት ነዉ። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል ናት። በምንም አይነት ልትገነጠል አትችልም። እንኳን የእነሱ አይነት ወሮበሎች ጣልያንም ሊገነጥላት አልቻለም፡፡ ይሄም የተረጋገጠ ነዉ። በጣልያንም ጊዜ እንደሚባለዉ ጣልያን ያስወራ ነበር፡፡ ሌሎች ኢትዮጵያዊያኖች እንደዚህ ያደርጓችኋል፣ተከላከሏቸዉ እያለ ያስወራ ነበር። ያንን ነዉ የህወሃት መሪ ነን የሚሉት አሁን እያደረጉ ያሉት። የትግራይ ህዝብ ለእነዚህ ሴረኞች አይንበረከክም። ደብረፂዮንም ሆነ ሌሎቹም ባለስልጣናት የትግራይን ህዝብ ድምፅ ይወክላሉ ብዬ አላምንም። የሚወክሉት እራሳቸዉን ነዉ። እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ሰዎች ናቸዉ። ህወሃት ከክልሉ ቢወገድ የትግራይ ህዝብ በነፃነት ይኖራል፡፡ በእኔ አስተያየት ግን አብዛኛዉ የትግራይ ህዝብ ህወሃትን ይደግፋል ብዬ አላምንም፡፡ እዚያ አካባቢ ሄደዉ የነገሩኝም ሰዎች ይሄንኑ ነዉ ያረጋገጡልኝ። ህወሃት አሁን የሚነዛዉን ፕሮፓጋንዳ ቁምነገር ብለን መመልከት የለብንም። የትግራይ ህዝብ በእኔ አስተያየት ተጨቋኝ እንጂ የነፃነት መብት ያለዉ አይመስለኝም።

**አሃድ፡- ህወሃት ለትግራይ ህዝብ ብዙ ነገር እንዳበረከተ ይናገራል። ይሄ ገለፃዉ አሳማኝ ነዉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ የህወሃት ሰዎችን የማያቸዉ በተለየ መነፅር ነዉ። ከጫካ ጊዜ ጀምሮ ስትመለከቺ ለራሳቸዉ ጥቅም ያደሩ ናቸዉ። እራሱ ጌታቸዉ ረዳም እኮ ተናግሯል፡፡ የሚቆጨኝ ነገር ቢኖር ለትግራይ ህዝብ ምንም ነገር አላደረግንለትም ብሎ በአንደበቱ ተናግሯል። ለምንድን ነዉ የቆጨዉ? የራሳቸዉን ጥቅም ብቻ ሲያስፈፅሙ ስለቆዩ ብቻ ነዉ። ለትግራይ ህዝብ የሆነ ነገር አድርገዉለት ቢሆን ኖሮ ዛሬ አፉን ሞልቶ መናገር ይችል ነበር። አቦይ ፀሃዬም እንዲህ ብሎ ተናግሯል። ስለዚህ እነሱ የራሳቸዉን ህንፃ ሲገነቡና ሲያከማቹ እንጂ ለትግራይ ህዝብ ምንም ያደረጉለት ነገር የለም። ለምሳሌ ኤፈርት የተባለዉ ድርጅት ሲመሰረት እንደተባለዉ ለትግራይ ህዝብ መረዳጃ ተብሎ ነበር። አቦይ ስብሃትም እንደተናገረዉ ገንዘቡ የኔ ነዉ ለልጆቼ አስተላልፌ እሰጣለሁ ብሏል። ስለዚህ ይህን ስታይ እነዚህ ሰዎች ለሌብነትና ለዝርፊያ የተነሱ ሰዎች እንጂ ለትግራይ ህዝብ ብለዉ የቆሙ አይደሉም። ወደ ትግራይ ህዝብ ጉያ መደበቅ የሚፈደልጉት ተጠያቂነት ስለሚሰማቸዉ ነዉ። ለሌላ ነገር አይደለም፡፡ የሰረቁት ስለታወቀ እና በዛ ነገር ተጠያቂ ስለሚሆኑ ወደ ትግራይ ህዝብ ተመልሰዉ መጥተዉ ሊጨፈጭፉን ነዉ፣ ሊገድሉን ነዉ እያሉ ህዝቡን ለማወናበድ የሚያደርጉት ነገር ነዉ። የትግራይ ህዝብ በነዚህ ሰዎች ተጠቃሚ ነዉ ወይ ለሚለዉ ነገር የትግራይ ህዝብ የሚጠጣዉ ዉሃ እንኳን የለዉም። ትግራይ ሄደዉ የመጡ ሰዎች ለእኔ ነግረዉኛል፡፡ በትግራይ ዉስጥ ያሉት ችግሮች ከሌላዉ ማህበረሰብ ካሉት ችግሮች ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ከትግራይ ህዝብ ጋር መኖራቸዉ ተገቢ አይደለም ብዬ ነዉ የማስበዉ። ስለዚህ ሌላዉ ህብረተሰብ የትግራይ ህዝብ በህወሃት ተጠቃሚ ነዉ ብሎ ማሰቡ ለእኔ ትክክል አይደለም። ህዝቡ ህወሃትን ሙሉ በሙሉ ይደግፋል ብዬም አላስብም።

**አሃድ፡- በኢህአዴግ ዉስጥ ብዙዎቹ በሙስና በዝርፊያ ተሰማርተዋል። ስለዚህ መጠየቅ ያለባቸዉ ጥቂቶች ብቻ ናቸዉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ዘረፋዉ ላይ የትግራይ ባለስልጣናት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም የተካተቱበት ነዉ። ሜቴክ ዉስጥ የነበሩት መሪዎች እንደሆኑ ለምሳሌ ክንፈ ዳኘዉ የትግራይ ሰዉ ነዉ። ከሱ ጋር የተገናኙ ሌሎች የትግራይ ባለስልጣናት አሉ። እነሱም መጠየቅ አለባቸዉ። ከትግራይ ሹማምንት ዉጭ የሌላ ብሔር ባለስልጣናትን በሙስናና በዝርፊያዉ እጃቸዉን አስገብተዋል። ስለዚህ መጠየቅ ካለበት የየትኛዉም ብሔር ሙሰኛና ዘራፊ ነዉ። በመሰረቱ ላለፉት 27 ዓመታት በብዙ ቦታዎች ላይ በሀላፊነት የተቀመጡት የትግራይ ሹማምንት ናቸዉ፡፡ ይሄ ምንም ጥያቄ የለዉም። አሁን ላይ አብዛኛዎቹ የሚታሰሩት የትግራይ ሹማምንት መሆናቸዉን ብዙ ሊያስገርመን አይገባም፡፡ ግን የየትኛዉም ብሔር ዘራፊና ሙሰኛ ከተጠያቂነት ሊያመልጥ አይገባም።

እኔ ጠበቃ እንደመሆኔ መጠን በሜቴክ ጉዳይ ላይ ሙሉ ለሙሉ መናገር አልችልም፡፡ ምክንያቱም ገና ማስረጃዎች ተሰባስበዉ አላለቀም። የክሱን ሂደት ወደፊት የምናየዉ ይሆናል። የሆነዉ ሆኖ እነዚህ ሰዎች ተጠያቂነታቸዉ በዘራቸዉ አይደለም። ተጠያቂነታቸዉ ባደረጉትና ባላደረጉት ነገር ላይ ብቻ ነዉ። ግድቡን እንሰራለን ብለዉ አልሰሩም። ይህም ያስጠይቃል። የግድቡን ገንዘብ ተቀብለዉ አጠፉት። ያስመጡትም እቃ የተበላሸ ነዉ። እነዚህ ሁሉ የሚያስጠይቁ ናቸዉ። ቀደም ብዬም እንደተናገርኩት የሰረቀ ሰዉ መጠየቅ አለበት። ግን የአብዛኛዎቹ ሰዎች ጉዳይ ገና ለፍርድ አልቀረበም።

ስለዚህ ትልቁ ነገር ምንድን ነዉ? ማስረጃ አለ ወይ? ማስረጃ ካለ ደግሞ እነዚህን ሰዎች መከራከር እና ማስቀጣት እንጂ ወሬ ማዉራት አያስፈልግም። የነርሱ ሙግት አልሰረቅንም ከሆነ በፍርድ ቤት ተከራክረዉ በመርታት አለመስረቃቸዉን ማሳየት ነዉ። ዘርን የሚያስገባዉ ነገር የለም።

**አሃድ፡- የህወሃት ሰዎች የሚሉት በቴሌቪዥን ፕሮፓጋንዳ ተሰርቶብናል የሚል ነዉ። ከዚህ በፊት እነርሱ እራሳቸዉ እንደ ‹ጀሃዳዊ ሀራካት፣ አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ›… የሚባሉ ዶክመንተሪዎችን ባልተፈረደባቸዉ ሰዎች ላይ ሰርተዋል። ከዚህ አንፃር አሁን በዶክመንተሪ ፕሮፓጋንዳ እየተሰራብን ነዉ ቢሉ ያሳምናል?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ በጀሃዳዊ ሀራካት ላይ ከፍተኛ ትግል እና ተቃዉሞ አድርጌያለሁ፡፡ ፅሁፍም በብዛት አቅርቤያለሁ። ከነሱም ጋር ተሟግቼ ነበር። እነርሱ እንግዲህ ያንን ያደረጉት በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ የወንጀል ቀለም ለመቀባት ነዉ። በአሜሪካንም ሆነ በየትም ሀገር አንድ ወንጀል ተሰራ ሲባል የወንጀሉ አይነት ይቀርባል። በተለይ በአሜሪካን ሀገር አንድ ክስ ሲቀርብ (ክስ ሲከፈት) አቃቢ ህጉ መጠቆም አለበት፡፡ አለበለዚያ የሚደበቅ ነገር አለ ብሎ ነዉ የሚገምተዉ። ምንድን ነዉ የተደረገዉ፣ የተደረጉትን ነገሮች ነዉ ሪፖርት የሚደረገዉ፡፡ አሜሪካን ሀገር ጁር የሚባል ነገር አለ። ጁር ማለት ከህዝቡ ከኮሚቴ የተዉጣጡ ሰዎች መሆኑንና አለመሆኑን የሚያረጋግጡ ሰዎች ናቸዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን ያሉት ዳኞች ናቸዉ። ፕሮፌሽናል የሆኑ ዳኞች ናቸዉ። ተናገረ አልተናገረ እነሱ የሚመለከቱት ፍርድ ቤት ዉስጥ የቀረበዉን መረጃ ብቻ ነዉ።

ስለዚህ Du process low ህጋዊ የሆነ ነገር የምንለዉ ነዉ። ፍርድ ቤት በምንገባበት ጊዜ እነዚህ ፍርድ የሚሰጡ ሰዎች ቴሌቪዥንን አይተዉ አይደለም።

**አሃድ፡- ስለዚህ መደረጉ ትክክል ነዉ ብለዉ ያምናሉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ህዝቡ ማወቅ አለበት። ይሄ አብዛኛዉን ህዝብ የሚነካ ነገር ነዉ። የቀረበዉ በጋዜጠኝነት ደረጃ ነዉ። አቃቤ ህጉ ያደረገዉ ደግሞ የእሱን ዝርዝር ነዉ ያመጣዉ። ስለዚህ አንፌር ነዉ ከተባለ አቃቤ ህጉ የዛን ጊዜ መቶ ስለ ክሱ የተናገረዉ ነገር ላይ ምንድነዉ ጉድለቱ የሚለዉ ነገር ላይ ነዉ። አቃቤ ህጉ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ተናገሩ? እኔ አስታዉሳለሁ ከአሁን በፊት የዉጭ ሀገር ጋዜጠኞች በተከሰሱበት ጊዜ መለስ ዜናዊ መቶ ‹‹እነዚህ አሸባሪዎች ናቸዉ›› ብሎ ተናግሮ ነበር። መለስ በመንግስት ደረጃ ነዉ የተናገረዉ፡፡ ስለዚህ አሁን ዶክመንተሪ ተሰራብን ብለዉ መጮሃቸዉ ብዙም የሚያስደንቅ አይደለም፡፡ እነርሱስ ይሄንን ሲያደርጉ አይደል እንዴ የኖሩት? አሁን ህግ ይከበር እያሉ እምቧ ከረዮ ቢሉ ሰሚ የላቸዉም።

# ባህልና...

## ከገፅ 23 የዞረ

ሲዋረድ ከኖረው ታሪካዊ ሐረጉ በተዋረድ ሲበለጽግና ሲጐነጐን የመጣ፣ አንዱ ከአንዱ ሲወራረስና እትብቱ ዕድገቱን ሲቋጥር እና ሲሸርብ ፣ ሲደርብ የመጣ ነው።

የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ በአብዛኛው ጥንታዊ መልኩን ያልተወ ቢሆንም ጥንታዊ ሥርዓት ደረጃ ላይ ይገኛሉ ከሚባሉ የሶስተኛው ዓለም ሕዝብ የተለየ ነው። በስብዕና፣ በሥነ ምግባር፣ በአኗኗር ሥርዓት፣ በታሪክ አቀራረጽና አሠራር፣ በባሕል ማበልጸግ፣ በሥልጣኔ ፈለግ ጉዞ ላይ የተለየ ይዘት ያለው ነው። ሥልጣኔ ማለት፣ በአሁኑ ዘመን በሠለጠነው ዓለም የምግባር ብልሹነት፣ ነፍስ ግድያ፣ አሳፋሪ ባህሎች ወግ ማጥበቅ እንደ ሥልጣኔ ባለመቁጠርና- በዘመናዊ አኗኗር አለባበስ ኋላ ቀር ደረጃ ላይ የሚታየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብሉይ እስከ ክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች የያዟቸውን ሕግጋት እያከበረ በመኖሩ የሥልጣኔ የበላይነቱን ለመግለጽ ነው።

ከማናቸውም የዓለም ሕብረተሰብ የበዛና የተለያየ የምግብና የምግብ ቅመም፣ የባሕላዊ መድኀኒት፣ የባህላዊ መጠጥ ዓይነትና ብዛት ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአለባበስም ከተለያዩ የቆዳ (የለምድ) አልባሳት እስከ ጥበብና ካባ፣ እስከ ካባና ሸልም መንጠልያ ለዓይነት የሚያስቆጥር ነው።

በመላው አፍሪካ ከአለው የሴቶችና የወንድ የፀጉር አሠራር ፈሊጥ አጠቃልሎ የሚበልጥ አይነት ይመዘግባል። በአኳኋል፣ አነቃቀልና በንቅሳት፣ በአተላተል፣ የሰውነት አጋጌጥ ዓይነትና ባህላዊ ትርጉም ወግ የተራቀቀና የተደነቀ ለመሆኑ አስተባባይ የለውም። የሰብል መሰብሰቢያ መኸር እስከ አደን፣ ከሠርግ እስከ ኃዘን ወቅቱ ያሉ፣ ከሙሾ እስከ ድለቃ፣ ከሽለላ እስከ በገና ድርደራ ያሉ የግጥም አደራደር፣ የአዛዜምና የጭፈራ ባህሉ በዓለም ሕብረተሰብ የሚያህለውም የሚመስለውም ፣ አቻዬ ነው የሚለውም የሌለው ነው። የቤተክርስቲያን ሥርዓቱ የተለየ፣ የራሱ የሆነ ጽሑፍ ያለው ራሱን ልዩና ተደናቂ አድርጎ የኖረና ያስመዘገበ ሕዝብ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ የበለፀገ ጥሩ ባህል ያለው መሆኑን ሳንረሳ፣ ጎጂና ሊታረሙ ወይም ሊቀሩ የሚገባቸው ባህሎችም አብረው እንዳሉ ሳልጠቅስ ማለፍ የለብኝም። ይሁን እንጂ፣ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ምልዕተ ባህል ድንቅና ብልፁግ፣ ልዩ እንደሆነ የኖረ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየብሔራዊ፣ ብሔረሰባዊ፣ ጎሳዊ፣ ነገዳዊ፣ ማህበረሰባዊ፣ እንዲሁም ማህበራዊ ኑሮ የተለያዩ እያንዳንዱ ክፍል የእኔ አንጡራ ባህል ነው የሚለው ባህላዊ ፀጋ ቢኖረውም አንዱ ባህል የሌላው ቅራፊ፣ አንዱ የሌላው አበልፃጊና ተደጋጋፊ ሆኖ ይገኛል። የባህል ተመሳሳይነቱም አንድነትን አጽንቶ የኖረ ኃይሉ መሆኑን በዚህ እንረዳለን። የባህላዊ ቅርሶቹ ገጽታዎች መለያዎችና አቀራራቢ መረጃዎች የሚታዩት በዕምነቶቹ፣ በዕደ ጥበብና በሌላው ውጤቶች፣ በእርሻ፣ በወግ፣ በልዩ ልዩ ሞያ መሣሪያዎቹ፣ በጋብቻ፣ በኃዘን፣ በውጊያ በአደባባይ፣ በሃይማኖታዊ በዓላትና በሌላው ሥርዓቱ የተለያዩትን ባህላዊ መልኮቹን ያሳያል።

ዋሻዎችን ምሰውና ፈልፍለው ሥዕሎችን እየሳሉ፣ ልዩ ልዩ ነገሮችን ሲቀርጹ፣ አለቶችን፣ ግንዶችን ወቅረው ሀውልቶችን ሲያቆሙ፣ ጣዖቶችን ሲሠሩ፣ መሠውያዎችን ሲተክሉ፣ በሸክላ፣ በዕምነ በረድ፣ በዕብን (ደንጊያ) በጭቃ ሃውልቶችን ሠርተው አቁመው የመስዋዕት መፈፀሚያቸውና መሰባሰቢያቸውን ሲያዘጋጁ ባህላቸውን እያሰፉ፣ የወግ፣ የስፖርት፣ የእርሻ መሳሪያዎች በየዘመኑ እያሻሻሉ የመጡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሥራ ሳይፈቱ ኖረዋል። ከዘመናዊ ሥልጣኔ ኋላ መቅረት ሌላ ያጡት ነገር የለም።

ብሔረሰቦች፣ ነገዶች፣ ጎሳዎች፣ ጐጦች፣ ማህበረሰቦች ሁሉ አንዱ ከሌላው ለየት ያለ፣ የሴትና የወንድ ሞያና ተግባር፣ የመስክና የቤት ውስጥ ሥራ ክፍፍል፣ የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ ያለባበስና ያጋጌጥ የማጀትና ያደባባይ፣ ሌላም ባህል አላቸው። በአብዛኛው የተለያየ፣ ከመጠኑም የመወራረስ ባህል በአንዳንድ አካባቢ መተዳደሪያ ሕግ ነው። ዕምነትንም በውስጡ ያቅፋል። በግርዘት፣ በገላ መብጣት፣ በንቅሳት፣ በትልተላ እና በመሰል ጠቃሚም ሆነ ጐጂ አድራጎቶች ላይ ባህልን ግልጽ እና ልዩ አድርጎ እናያለን። ጉግሥ፣ የገና ጫወታ፣ የልጆች የእርግጫ፣ የጭቃ፣ የውኃ አረጫጨት፣ የኩበት ጦርነት፣ የሴቶች የበዓላት የባህላዊ ዘፈኖችና ድለቃዎች ዝግጅት የባህልን ሌላው መልክ ያሳያሉ።

ሙሾ፣ ቅዳሴ፣ የእስላሞች መንዙማ፣ ለቦረንቲቻ፣ ለገዳ፣ ለግርዘት፣ ለሰብል አጨዳና አሰባሰብ በአውድማ ላይ፣ በመኸር፣ በእርሻና በጉልጓሎ፣ በዓረምና በቃርሚያ ወቅት የሚደረጉ ልዩ ልዩ ነገሮች ባህሎችን እየቀረጹና እያበለፀጉ ሄደዋል። በአንዳንድ አካባቢ ምልዓተ ገበያ መሃል ጋያ በማህበር ማጨስ፣ ቦርዴና ኰረፌ በበርበሬ፣ ጠላና ጠጅ መጠጣት፣ ደጀን ለይቶ ትግል መታገልና በበትር መዋቃት፣ መዝፈን፣ መደለቅ፣ ሙሽራን አጅቦ ገበያ መግባት፣ ቅርጫ አርዶ መከፋፈል የተዘወተሩ ነገሮች ሲሆኑ፣ በአንዳንድ አካባቢ ሴት ዘወትር ወደ ማጀት ገበያና መስክ — ወንድ ወደ አደባባይ፣ ወደ ቤተክርስቲያንና መስጊድ ሄዶ መዋል የተከበረ ባህል ነው። በአንዳንድ አካባቢ — አብዛኛውም በገጠር ነዋሪው መተዳደሪያ ሥራ ሴት ስትከታተል ወንዱ ጠላትን መጠበቅ፣ ጥርስ መፋጫውን አፉ ውስጥ ዶሎ፣ ጦሩን ሰብቆ፣ ጋሻውን አንግቦ መንገላወድ፣ የወንድነት ማሳያ ወጉ ነው።

የግንቦት ልደታ ማርያምን — በየመንደሩ ማክበር፣ በሌላ በኩል ለተለያዩ ጠንቋዮች ስጦታ ማቅረብ፣ በዛር በአል አክብሮ በዛር ዘፈን መዝፈን የየአካባቢው ሕዝብ ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ሲዳሩ ማልቀስ፣ ሲዳሩ መዝፈን በየልዩ ልዩ ባህላዊ ክፍል አሉ። በእስላሞች መጅሊስ፣ በክርስቲያኖች ሰንበቴ፣ ማህበር፣ የተለያዩ ጠበሎችን መጠጣት- ተመሳሳይ ዕምነትና ባህል ያላቸው ማህበራዊ ኀይሎች አብረው እንዲኖሩ የሚያደርግ ባህል ነው። በዓለማውያን በኩል ለተለያዩ ርኩሳን መናፍስት መስዋዕት ማቅረብ በጣዖት አምልኮ ሥፍራዎች ላይ መፀለይ፣ መጨፈር፣ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ማዘጋጀት የአካባቢው ሕዝብ ባህላዊ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ በክርስቲያንና በእስላም፣ በቤተ እሥራኤላዊ አካባቢ — የሃይማኖት — በዓላትን አስታክኮ ደግሶ መደሰትን፣ ምህላ ማድረግንና ሌሎችም ዕምነታዊ ጉዳዮች ተመሳሳይ ባህል ያላቸውን ሰዎች የሚያሰባስብ ነገር ነው።

የመኖሪያ ቤቶች አሰራር፣ የመኝታና የሥራ አልባሳት ዝግጅት አንዱን ሕዝብ ከሌላው ለይቶ ለማየት የሚያስችል ነገር ነው። አገራችን ውስጥ ከላይ እንደጠቀስኩት የምግብ፣ የመጠጥ፣ የቤት ቁሳቁስ፣ የመስክ መሳሪያዎች አዘገጃጀት አንዱን ብሔረሰብ ከሌላው፣ አንዱን ማሕበረሰብ ከጎሳው ለየት ያደርገዋል። የሁሉም ባህላዊ ፀጋ፣ ውበት ለማበላለጥ ማነፃፀሪያዎችን የሚያስፋፋ ጉዳይ ይሆናል። ሁሉም ልምዶች፣ ወጎች፣ የአሰራርና የአኗኗር የማህበራዊ ኑሮ ምሥረታ ዘይቤዎች በተለያዩ መልካቸው የራሳቸውን ልዩ ፀጋ ያንፀባርቃሉ። በሥራና በዕረፍት በበዓላት፣ በጨዋታ፣ በአደባባይ መሰብሰቢያ ጊዜ ሁሉም ማህበራዊ ክፍሎች ውበታቸውንና ብልጽግናቸውን ያንጸባርቃሉ።

ባህል ይበከላል፣ ይወራረሳል ፣ ያድጋል፣ ይደክማል። የአንድ ሕዝብ ባህል ሲጠበቅ የመበልፀግ አዝማሚያው የበለጠ ነው። የሠንጠረዥ፣ የገበጣ፣ ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ ጨዋታዎች በአንዳንድ አካባቢ ሲዘወተሩ፣ በአንዳንዱ አካባቢ የጥበብ፣ የሞያ መስፋፋት የታገደ ነገር ነው። ባህሉ አግዶታል፣ አውግዞታል። ባህልም ጠብቦ ይታያል። መልካም ሥራ የሚሠሩትን ካይላ፣ ፋቂ ደበናንስ፣ ቡዳ፣ ሰላቢ፣ ባለ እጅ እያሉ በሌላው ወግ እያፌዙና እያወጉ መኖር፣ ተኮፍሶ ውሎ ትችት ማብዛት የተከበረ የወንዶች ተግባር ነው። በአገራችን፣ ደቦ — ወንፈል — ጅጌ ብንላቸውም ሁሉም በአንድነት ማህበራዊ ኑሮን ያሰፋሉ ፣ ሰዎችን ያቀራርባሉ። የየአካባቢው መጠሪያዎች ቢሆኑም ባህላዊ ተፈጥሮአቸው፣ ድርጅታቸው አንድ ነው።

ዘፈን የሚያዘወትሩ ብሔረሰቦች አሉ። ሁሉም የየአካባቢያቸው የጭፈራ፣ የዝማሬ፣ ሥልት አላቸው። ክራር፣ መሰንቆ፣ በገና፣ እምቢልታ፣ ዋሽንት፣ ከበሮ አታሞ ሁሉ በየአካባቢው ባህላዊ ደጀን የባህላዊ ጨዋታ ስሜት መግለጫዎች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህል ብዙና ብልፁግ ነው። የክራር ቅኝት፣ የበገና ድርደራ፣ ቅኔ፣ ድጓ- ፆመ ድጓ፣ ዝማሬ የፀሎት፣ የጭፈራ፣ የኀዘን፣ የሠርግ የሌላም ባህል ብዛት ብልጽግና አለን። ባልትና፣ ዕደ ጥበብ፣ የወግ ማውጋት፣ የተረት — የሌላውም ባህል በየሕዝብ ማህበራዊ ክፍል የተለየ ትኩረት ያላቸው ባህላዊ ፀጋዎች ሆነው ሲበለጽጉ ኖረዋል። ስለዚህ፣ የአንዳንዶቹን የሁለት የሶስቱን ማህበረሰብ ያጠረ፣ አነስ ተደርጎ የቀረበ ባህላዊ ነገር የሚያሳዩ ጽሑፎችን ከዚህ ጋር አባሪ አድርጌ በመጭው ሳምንት አቅርባለሁ።

# የሰር አሌክስ...

ከገፅ 32 የዞረ



ሜሲ ሌሎቹ ተጫዋቾች የሚያከብሯቸው እና የሚታዘዟቸው ተጫዋቾች ሆኑለት፡፡

በ2012 ፈርጉሰን በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የአሰለጣጠን ዘይቤያቸውን ለማብራራት ከሃርቫርድ ምሁራኖች ጋር ተገናኝተው ነበር፡፡ የእርሳቸው ስነ ልቦና እና ፍልስፍና ለሁሉም ግልጽ ነበር፡፡ ሃሳባቸው በተጫዋቾቻቸው ላይ ለማስረጽ የማይቸገሩት ለዚያ ነበር፡፡

ኤሪክ ካንቶና ፣ ጋሪ ኔቪል እና ሪዮ ፈርዲናንድን የመሳሰሉ ተጫዋቾች ዛሬም ድረስ ያወሩለታል፡ ፡ ዛሬ ላይ ሁሉም የተከበሩ እና ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ሰዎች ሆነዋል፡፡ የታላቁ አሰልጣኝ ውጤት መሆናቸው ግን አይካድም፡፡ ዛሬም ድረስ ሲያወሩ በተለይም ስለ ማንቸስተር ዩናይትድ ሲናገሩ ፈርጉሰን አንድ ጥግ ቁጭ ብለው የሚመለከቷቸው ይመስል ተጠንቅቀው ነው፡፡

በሃርቫርድ በተደረገው ኮንፈረንስ ፈርጉሰን የተለያዩ የስነ ልቦና ቴክኒኮችን በልምምዶች ላይ ተግባራዊ የሚያደርጉባቸውን መንገዶች በዝርዝር ተናግረዋል፡፡ የዘረዘሯቸውን ነገሮች የሚያመሳስላቸው እና መሰረት የሚያደርጉት የጋራ ነጥቦች አሏቸው፡፡ ቀላል ፍልስፍና ነው፡ ፡ የቡድን ስሜት መፍጠር፡፡ ‹‹ከእኛ ጋር ካልሆንክ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ የሚል››፡ ፡ በእርሳቸው ዘመን ደግሞ ማንም ማፈንገጥ የሚፈልግ አልነበረም፡፡

ሞውሪንሆ በቅርቡ ባደረጉት አንድ ቃለ ምልልስ ‹‹በዲጂታል ዓለም የምኖር አናሎግ አሰልጣ ነኝ›› ማለታቸው ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ ጆዜ ዝግመተ ለውጥ ለማድረግ ዝግጁ አልነበሩም፡ ፡ ፈርጉሰን ግን በግልጽ በሚታይ መልኩ ብልሃት በታከለበት መንገድ በአቀራረባቸው ላይ ዝግመተ ለውጥን ተግብረዋል፡፡ ሌላኛው ወሳኝ ነጥብ አሰልጣኝ ተጫዋቾች እንዲያደምጧቸው ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ማወቃቸው ነው፡ ፡ አሰልጣኞች በየትኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ቢሆኑ ተጫዋቾቻቸውን ሊያናግሯቸው የሚገባው በእነርሱ ደረጃ ዝቅ ብለው ሊሆን እንደሚገባ ተገንዝበዋል፡፡

አሰልጣኞች አቅጣጫ ጠቋሚ እንጂ የሁሉም ነገር መሰረት እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ማየት እንደሌለባቸው ተረድተዋል፡፡ አሰልጣኞች ስለ ራሳቸው ከማውራታቸው በፊት ስለክለቡ ታሪክ ሊያወሩ ይገባል የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ የፈርጉሰን ሌላኛው መሳሪያ የጭንቅላት ጨዋታ የሚጀምሩት ገና ወደ ሜዳ ከመግባታቸው በፊት ነው፡፡ የማህበራዊ ስነልቦና ቁልፉ ስልጣንን ማሳየት መሆኑ ገብቷቸዋል፡፡ ሁልጊዜ እርሳቸው የበላይ መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ ተጫዋቾቻቸው ከመልበሻ ክፍል ሲወጡ መሹለኪያ ላይ ጠብቀው እያንዳንዳቸውን ይጨብጧቸዋል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ለተጫዋቾቻቸው አይደለም፡፡ ለሚመለከቷቸው ሰዎች ነው፡፡ ተጫዋቾቻቸውን ሲጨብጡ የዕለቱ ዳኞች እና የተጋጣሚ ቡድን አባላት እንዲመለከቱ ይፈልጋሉ፡፡ ያንን የሚያደርጉት በተጫዋቾቻቸው ላይ ስልጣን እንዳላቸው ለማሳየት ነው፡፡

የትኛውም ስነስርዓት የሚያከብር ቡድን ለተጋጣሚው አስፈሪ መሆኑን ያውቃሉ፡ ፡ ተጋጣሚያቸው ይሄ ስሜት እንዲያርፍበት ይፈልጋሉ፡፡ የሚከበር ቡድን ካርዶችን የመመልከት ዕድሉ ይጠባል፡፡ ስለሆነም ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ዩናይትድ መሪነቱን ይጨብጣል፡፡ ድግግሞሽ አስልቺ መሆኑንም ተረድተዋል፡፡ ድግግሞሽ የሚመከረው በልምምድ ሜዳ ላይ እንጂ በቡድን ወሬ ላይ አለመሆኑን ከተገነዘቡ ሰነባብተዋል፡፡ ፈርጉሰን በአንድ ወቅት የሰሙትን የአንድ አሰልጣኝ ታሪክ ሁልጊዜ ያስታውሳሉ፡፡ በተጫዋቾች እንዴት መቀለጃ እንደሆኑም በልባቸው አኑረዋል፡፡

ሰውዬው "ከዚህ በፊት አንድ ሺህ ጊዜ ሰምታችሁት ይሆናል" ብሎ ንግግራቸውን ይጀምራሉ፡፡ አንድ ቀን ከተጫዋቾቻቸው አንዱ ቀበል አድርጎ በግማሽ ያህሉ ጊዜ እንቅልፍ ወስዶኝ ነበር ብሎ እንደመለሰላቸው ያስታውሳሉ፡፡ የሚሰማቸው ከሌለ ደግሞ የአሰልጣኙ ተጽዕኖ ይቀንሳል፡፡

የሰው ልጅ አእምሮ የሚያነቃቃው ነገር ስለሚያስፈልግ ፈርጉሰን ንግግራቸውን ቀልብ የሚገዛ እንዲሆን ይጨነቁ ነበር ፡፡ ስለሆነም ስለ ጦርነት ፣ ስለ ታላላቅ መሪዎች ፣ስለ ታላላቅ ስፖርተኞች ፣ ስለዓለም መሪዎች ሌላው ቀርቶ ስለ አንድሪያ ቦቼሊ ኮንሰርት ለተጫዋቾቻቸው ያወሩ ነበር ፡፡

ፈርጉሰን ካደረጓቸው እጅግ ተጽዕኖ ፈጣሪ የመልበሻ ቤት ንግግሮች መካከል አንዱ በ1999ኙ የቻምፒየንስ ሊግ ፍጻሜ የተናገሩት ነው፡፡ ‹‹ከዚህ ጨዋታ ፍጻሜ በኋላ የቻምፒየንስ ሊግ ዋንጫ ከእናንተ በሁለት ሜትር ርቀት ብቻ ይቀመጣል፡፡ ከተሸነፍን ሌላው ቀርቶ መንካት እንኳን አትችሉም፡፡ ለአብዛኞቻችሁ ደግሞ ከዚህ በኋላ ወደ ዋንጫው የምትቀርቡበት ዕድል የለም፡ ፡ አቅማችሁን ሁሉ አሟጣችሁ ሳትጠቀሙ ወደዚህ ለመመለስ እንዳታስቡ›› የሚል ነበር፡፡

ፈርጉሰን ሁሉን ነገር ልምምድ ሜዳ ላይ መስራታቸውን ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን ዋንጫውን ለማንሳት የአልሸነፍ ባይነት መንፈስ እና ታታሪነት ወሳኝ መሆኑን በማወቃቸው ያንን አደረጉ፡፡ ሽንፈት የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳዩዋቸው ሞከሩ፡፡ በህይወት ዘመናቸው በሙሉ ሲቆጫቸው እንደሚኖር ሊያስታውሷቸው ሞከሩ፡፡ የጨዋታውን መጠናቀቅ የሚያበስረው ፊሽካ እስኪሰማ ድረስ ዩናይትድ ያልተሸነፈው ለዚያ ነበር፡፡

ፈርጉሰን ተጫዋቾቻቸውን የሚያነሳሱባቸው የተለያዩ መንገዶች ነበሯቸው፡፡ ዛሬ ላይ በተለያ የስነልቦና መጽሃፍት እንደ ምሳሌ ከሚጠቀሱ መንገዶቻቸው አንዱን ማንሳት ተገቢ ነው፤ ማንችስተር ዩናይትድ ከ26 ዓመታት በኋላ በ1993 የመጀመሪያ ዋንጫውን ካነሳ በኋላ የሆነ ነው፡፡

ፈርጉሰን ተጫዋቾቻቸው በአሸናፊነት ስሜት እንዲቀጥሉ ፈልገዋል፡፡ ስኬት የሚፈጥረውን መታበይ ማስወገድ ከባድ መሆኑን ተገንዝበዋል፡ ፡ ስለሆነም አንድ መላ ቀየሱ፡፡ ተጫዋቾቻቸውን "ሰብስበው ዘንድሮ እንደምንም ዋንጫውን አንስተናል፡፡ ነገር ግን በሚቀጥለው የውድድር ዘመን ደግመን ማሳካት መቻላችንን እጠራጠራለሁ፡ ፡ በተለይ ደግሞ በሶስት ተጫዋቾች ላይ ጥርጣሬ አለኝ፡፡ በሚቀጥለው የውድድር ዘመን ቡድኑ ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት ይሆናሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ነገር ግን ስማቸውን በግልጽ ልጠራ አልፈልግም፡፡ በግል እሰጣቸዋለሁ፡ ፡ ነገር ግን ግን በልምምድ ሜዳ ላይ የተሸሉ ተጫዋቾች እንደሆኑ ካሳዩኝ ሃሳቤን ልቀይር እችላለሁ" ብለው ስብሰባውን በተኑት ፡፡ ይህን ጊዜ እያንዳንዱ የቡድኑ ተጫዋች ያ የተባለው ተጫዋች እኔ እሆንን እያለ የበለጠ መትጋት ጀመረ፡፡ ውጤታማነቱም ጨመረ፡፡ ፈርጉሰን ሃላፊነታቸውን ከለቀቁ በኋላ ይፋ እንዳደረጉት ግን ምንም ዓይነት ፖስታ አልነበረም፡፡ ያንን ያደረጉት ተጫዋቾች በትጋታቸው እንዲቀጥሉ በማሰብ ነበር፡፡

ስኬት በቀላሉ አይመጣም፡፡ እንዲህ ያለውን ቴክኒክ መጠቀም ወደ ማኪያቬሊያዊ አስተምህሮ ይወስድ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከመሸነፍ ይሻላል የሚል እምነት አላቸው፡፡ እውነት ነበራቸው፡፡ ማንቸስተር ዩናይድ ሽንፈት አልተለማመደም፡ ፡ በሰር ማት በስቢ ዘመን ዩናይትድ አሸናፊ ነበር፡፡ ሰር አሌክስ ፈርጉሰንም በአሸናፊነቱ አስቀጥለውታል፡፡ ቀጥሎ የሚመጡትም አሰልጣኞች በዚያ መንገድ እንዲጓዙ ይጠበቅ ነበር፡፡ በስኮትላንዳዊው የተመረጡት እና ብዙ የተባለላቸው ዴቪድ ሞዬስ ያንን ማድረግ አልቻሉም፡፡ በተለያዩ ታላላቅ ክለቦች ውጤታማነታቸውን ያስመሰከሩት ልዊስ ቫን ሃልም አልተሳካላቸውም፡፡ ጆዜ ሞውሪንሆ ደግሞ የባሰ አዘቅት ውስጥ ጨምረውት ተሰናበቱ፡፡ አሁን መርከቧን የሚቀዝፈው ካፒቴን ኦሌ ጉናር ሶልሻዬር ነው፡፡ ኖርዌያዊው የዓለቃውን መንፈስ ወደ ኦልድ ትራፎርድ ይመልስ ይሆን? ጊዜ

# ያልተቀደሰው...

ከገፅ 6 የዞረ

በቂ ነው፡፡ በእኛም ሆነ በሌሎች ሀገራት ታሪክ እንዳየነው በለውጥ ሂደት በማንኛውም ሁኔታ የጥይት ተኩስ ከተጀመረ ማቆሙ ከባድ ነው፡፡ ይልቁንስ አንዱን ለማስቆም ሌላ ሲተኮስ ድጋሚ ሌላ ሲተኮስ በመጨረሻ ወደ አናርኪ ውስጥ ልንገባ እንችላለን፡፡ ይህንንም እጅጉን አጥብቀው የሚፈልጉት እንዳሉ እሙን ነው፡፡

### በፖለቲካ አለም ቋሚ ፍላጎት እንጂ ቋሚ ጠላት የለም

በጥንቱ የሪያሊስት አስተሳሰብ (Classical Realism paradigm) እሳቤ መሰረት በፖለቲካ አለም ቋሚ ጠላት ወይም ቋሚ ወዳጅ የሚባል ነገር የለም፡፡ ይልቁንስ ቋሚ ፍላጎት (Interest) ነው ያለው፡፡ ይህ ማለት የዛሬ ወዳጅ የነገ ጠላት ሊሆን ወይም የዛሬ ጠላት የነገ ወዳጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሁሉ መሃል ግን ቋሚ የፖለቲካ ፍላጎት (Interest) (ስልጣን የመያዝ ወይም የማሸነፍ ፍላጎት) አለ፡፡ ለዚህ አመለካከት ጥሩ ሀገራዊ ተምሳሌቶች ህውሃትና ኦነግ ናቸው፡፡

ባለፉት አመታት በተለያየ መልኩ የኦሮሞን ህዝብ መብትና ክብር ለማስጠበቅ በብዙ መንገዶች የኦሮሞ መብትና ክብር ያገባናል የሚሉ ሃይሎች የተለያዩ ጥረቶች አድርገዋል፡፡ ከእነዚህ ሃይሎች መካከል በመጀመሪያው ረድፍ የሚቀመጠው ኦነግ (የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር) ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ኦነግና ህውሃት በወቅቱ ተማሳሳይ ፍላጎት ስለነበራቸው (ሀገርን የመቆጣጠር) በጋራ አብረው ሰርተዋል (በሚኒስተር ደረጃ እንኳን ሳይቀር)፡፡ ነገር ግን የኦነግ አካሄድና አስተሳሰብ ያልተመቻቸውና የበላይነቴን ይቀናቀንብኛል የሚል ስጋት ያደረበት ህወሃት ኦህዴድን በመፍጠርና ለኦሮሞ ህዝብ ተወካይ ድርጅት እንደሰራለትና ኦነግንም አዋክቦ ከሃገር እንዳስወጣው በወቅቱ የነበሩ እማኞች ይናገራሉ፡፡

ህውሃት ጠፍጥፎ በሰራው ኦህዴድ አማካኝነት በኦሮሚያና በሀገሪቱ ያሻውን ሲያደርግና ኦህዴድን ለ27 ዓመታት ለፍላጎቶቹ መጠቀሚያነት ሲያውለው ነበር፡፡ ነገር ግን ከ2008 ዓ.ም ወዲህ (በተለይ ከኦቦ ለማ ወደ ስልጣን መምጣት ወዲህ) ኦህዴድ/ኦዴፓ እንደበፊቱ የፍላጎት ማስፈጸሚያ ከመሆን እየተላቀቀ መጥቶ እስከነጭራሹ ህውሃትን ከመሃል ሀገር አባሮ የፖለቲካ ምህዳሩን ለመቆጣጠር ችሏል፡፡ ምንም እንኳን በራሱ ፍላጎትም ይሁን በሌላ ገፊ ሃይል ኦነግ ከሃገር ቢወጣም መንፈሱና ስሙ ለህወሃት የኦሮሞን ወጣት ለማሸማቀቂያ መሳሪያነት መዋሉ ግን አልቀረለትም፡፡

ከለውጡ በኃላ ወደ ሀገር የገባው ኦነግ ግን ከ27 ዓመታት በፊት ከሀገር ካባረረውና በእርሱ ስም (በኦነግ ስም) በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ወጣቶችን ከገደለው፣ ካኮላሸውና ከሀገር ካባረረው ህውሃት ጋር ግንኙነትን ዳግም ለማደስ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ሁለቱ ነጻ አውጪዎች (የኦሮሞና የትግራይ) ለ27 ዓመታት ያሳለፉትን የግፍ ስራ ረስተው ወዳጅነትን የጀመሩት የሁለቱም ተመሳሳይ ስጋት (ኦዴፓ) መጠናከርና የሁለቱም ፍላጎት ተመሳሳይ ስለሆነ ነው (የበላይ የመሆን ፍላጎት)፡፡

### በቲም ለማ የከሸፈው የበላይ የመሆን ምኞት

ጠባብ ብሔርተኝነትን መሰረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ ወይም ከዚህ በፊት ተጎድተናልና አሁን ከሌላው በበለጠ መጠቀም አለብን ብለው የሚያምኑ ቡድኖች (ልክ እንደ ኦነግና ህውሃት) በቀላሉ ከሌሎች ጋር በእኩል የመታየትን እርምጃ ለመቀበል ከባድ ይሆንባቸዋል፡፡ ታዋቂው አሜሪካዊ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁር ፍራንሲስ ፉኩያማ በዚህ አመት (2018) “Identity the demand for dignity and the politics of resentment” በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሀፉ እንደሚለው እንዲህ አይነት ቡድኖችን ከሁሉም በላይ ሆኖ የመታየት ነፍሳዊ ፍላጎት (megalothymia) ስላላቸው ከእነርሱ ጋር መስራት እጅጉን ከባድ ነው፡፡

ገና ከጅምሩ ህውሃትም (የትግራይ ህዝብ ተበድሏል) ኦነግም (የኦሮሞ ህዝብ ባለፉት አመታት ተበድሏል) በሚል አስተሳሰብ የተደራጁ ድርጅቶች ናቸው፡፡ የደርግን መንግስት ለመጣል ከፍተኛ ትግል ውስጥ ያለፈው ህዉሃት በመጀመሪያው ማንፌስቶ የትግራይ ሪፐብሊክን መመስረት ዋና አላማው እንደነበር የድርጅቱ ሰነድ በግልጽ ያስረዳል፡፡ በተመሳሳይ ኦነግም እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ ኦሮሞን የመገንጠልና የኦሮሞን ሪፐብሊክ መመስረት አላማው ነበር፡፡ ከዚያ በኃላ ባሉት አመታት ግን ሁለቱም ባለፈው የተደረገውን ትክክል ያልሆነ አሰራር ለማስተካከል ከሌላው በተለየ መልኩ መታየትን እንደ መፍትሔ ያቀርባሉ (ህውሃት ባለፉት አመታት ይህንን አስተሳሰቡን ሲተገብረው ነበር፡፡ ኦነግ ግን ይህንን እድል አላገኘም አጋጣሚውን ካገኘ ግን አያደርገውም ማለት ይከብዳል)፡፡

የቲም ለማ በፖለቲካው አለም ወደ ፊት መምጣት የሁለቱንም ነጻ አውጪዎች አጀንዳ ገደል የከተተው ይመስላል፡፡ ህውሃት ላለፉት 27 አመታት ለህውሃትና ለቅርብ ወዳጆቿ ያደላውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነቷን በመጠቀም በከፍተኛ ሁኔታ የራሷን ኢኮኖሚ አደራጅታለች፡፡ የቲም ለማ ግን ይህንን የበላይነት በመገዳደሩና እስከነጭራሹም ለማጥፋት እንቅስቃሴ ውስጥ በመግባቱ በህውሃት ቤት ጨኸቱ በርትቷል፡፡

ኦነግ ለዘመናት የኦሮሞ ብሔርተኝነት (በመጀመሪያ ኦሮሞ) ምልክት የነበረ ሲሆን ባለፉት ሁለት አመታት የቲም ለማ ስራና እንቅስቃሴ የኦነግን አጀንዳ በመንጠቅ የኦሮሞን ብሔርተኝነት ወደ አዲስ እሳቤ አሻግሮታል፡፡ (በኢትዮጵያዊነት የታጀበ ኦሮሚዊነት) ይህም ለዘመናት በኦሮሞ ሲጠየቅ የነበረውን (ኦሮሞን አባ ቢያ) ጥያቄ ምላሽ ያስገኘ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ለኦነግ (በተለይ በኦቦ ዳውድ ኢብሳ ለሚመራው) ትልቅ የፖለቲካ ስጋት ነው፡፡

ባለፈው ሳምንት የኦነግ መሪ ዳውድ ኢብሳ እንዳሉት አሁን ለታየው ለዉጥ ዋና ተዋናዩ ኦነግና ደጋፊዎቹ እንዲሁም ቄሮ ነዉ እንጂ የቲም ለማ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ ኦነግ ለሚያነሳቸው በእኩል ወንበር ቁጭ ብለን እንደራደር እንጂ ማን የበላይ ማን የበታች (ማን ፊቺ ማን አስፈቺ ነው) ለሚለው ጥያቄዎች መሰረት ይመስላል፡፡ ህውሃትም ብትሆን የጠላቱ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው ብሂል መሰረት ለታሪካዊ ጠላቷ ኦነግ ወዳጅ ሆና ብትታይ አያስገርምም፡፡

ሁለቱም የጥንት ወዳጆች ይህንን ተመሳሳይ ስጋት ለማስወገድ የራሳቸውን መንገድ ተያይዘውታል፡፡ ዋናው ነገር የሁለቱ ነጻ አውጪዎች ህብረት ሳይሆን የቲም ለማ በምን አይነት መንገድ ያልተቀደሰውን ጥምረትና ከፊቱ የተጋረጡትን ፈተናዎች ያልፋል የሚለው ነው፡፡

## ጥንቃቄ

ኦነግም ሆነ ህውሃት የሚፈልጉት አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ሁለቱም ከዛሬ 40 አመት በፊት የተመኙትን ምኞት ማሳካት (በብሔራቸው ስም የራሳቸውን ጠባብ ፍላጎት ማስፈጸም)፡፡ ይህንን ምኞት ኦነግ ሲያገኘው አልቻለም፡፡ ህውሃት ግን ተጠቅማበት አሁን እዳውን እየከፈለች ትገኛለች፡፡ አሁን የታሪክ አጋጣሚ ሁለቱን በነፍስ የሚፈላለጉትን ጨካኝ ባለጋራዎች በአንድ ጀልባ ለጉዞ አጋጥሟቸዋለች፡፡ ኦዴፓና የቲም ለማ የለውጥ ጉዞ ትልቁ ስጋቱ አሁንም ከእነዚህ ሁለት ኃላ ቀርና ቆሞ ቀር ነጻ አውጪዎች ነው፡፡

በዚህ ወቅት በኦሮሞያ ክልል የሚፈጠር ማንኛውም ችግር ሀገሪቱን ወዳልተፈለገ አዘቅት ውስጥ ሊከታት ይችላል፡፡ ኦዴፓ አሁን ከሃይል ይልቅ በያዘው እንቅስቃሴው ኦነግን ከኦሮሞ ህዝብና ምሁራን የመለየት (እጅግ ከባድ ቢሆንም) የፕሮፖጋንዳ ስራውን ገፍቶበት በመሄድ የኦነግን ተቀባይነት መቀነስ ላይ መስራት ይኖርበታል፡፡ አሁንም ቢሆን የኦሮሞ ህዝብ የዘመናት ጥያቄ የነበሩና ያልተመለሱ ጥያቄዎች (የአዲስ አበባ ጉዳይ፣ የቋንቋ ጉዳይ...) አሉት፡፡ ኦነግ እነዚህን ጥያቄዎች እንደ አጀንዳ ይዞ ሊነሳና በኦዴፓ ላይ የአጥንት ቅንቅን ሊሆንበት ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኦነግ ከህውሃት ጋር የሚያድርጋቸውን ግንኙነቶች የራሱን ግብአተ መሬት ስለሚያፋጥንለት በአንክሮ መከታተልና የህዝብ ግንኙነት ስራ ላይ ማተኮሩ የሚሻል ይመስለኛል፡፡

በዚህ ሁሉ መሃል ግን የጃዋር እርምጃና ለየትኛው ወገን ይደግፋል ወይስ እንዳለው ሽማግሌ ሆኖ ሁለቱን ያስታርቃል የሚለው በሁለቱ ፓርቲዎች ቀጣይ ግኙነትና በኦሮሞ ፖለቲካ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ስላለው የጃዋርን ፖዝሺን እንጠብቅ፡፡

# ዶ/ር አብይ...

ከገፅ 5 የዞረ

እርምጃ እየወዱ ነው፣

ዶ/ር አብይ ባለፉት 27 ዓመታት በህዝቡ ላይ የደረሰውን ጭቆና፣ ሰባዊ መብት ገፈፋና የሃብት ዝርፊያ ለማስቆም እና ለማስወገድ እየሰሩ ይገኛሉ። በዚህ ህዝቡ ተደስቷል። ነገር ግን የበደሉ ፈጻሚዎችና ዘራፊዎችም ችግሩን በማስወገድ ሂደት ውስጥ ዋና ተዋናይ አድርገው አስቀምጠዋቸዋል። በዚህ ችግሩና መፍትሄው በተጠላለፉበት አኳኋን ውጤት ይመጣል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይመስላል። ለዚህም ነው ራሳቸውን ጠቅላይ ሚኒትሩን ለመግደል ከሁለት ጊዜ በላይ የተሞከረው። ለዚህም ነው በባንኮች፣ በአየር መንገድ፣ በመከላከያ፣ በድህንነት ቀድሞ የነበሩ ባለስልጣናት ለውጡ ውጤታማ እንዳይሆን አሻጥር እየሰሩ ያሉት።

ህዝቡንም የህዝብ ጠላት የነበሩትንም ባንድ ላይ ማስደሰት አይቻልም።

ለውጡን ውጤታማ ለማድረግ ቀድሞ በደል ሲፈጽሙ የነበሩ ግለሰቦችም ይሁኑ አመራሮች ከስልጣናቸው ባፋጣኝ የማንሳት ጠንካራ እርምጃ መወሰድ አለበት። አዲስ የተሾሙትም ይሁን ጥፋት ያልተገኘባቸው አመራሮችም ስራቸውን ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለበት መልኩ እንዲያከናውኑ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና ማስፈጸም ያስፈልጋል።

2) ዶ/ር አብይ በተወሰኑ ስትራቴጂዎችና ታክቲኮች ላይ ብቻ ከመጠን ያለፈ መተማመን ያሳያሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአብዮታዊ ዴሞክራሲና ልማታዊ መንግስት ፍልስፍና እንዲሁም ኢህአዴግ ኢትዮጵያን በኢኮኖሚም ይሁን በዴሞክራሲ ጎዳና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሳታል ብለው ነው እስካሁን የሚያምኑት። የኢህሃዴግ ፓርቲን በመጠገን አብዮታዊ ዲሞክራሲን እና ልማታዊ መንግስትን እንዲሰራ አደርጋለሁ ብለው በመነሳታቸው የለውጥ እርምጃዎችን የሚወስዱት በዘገምተኛነትና ለስላሳ በመሆን መልኩ ነው። ለውጡ እታች ሳይደርስ ከላይ ካለው እርከን ላይ ነው የቀረው።እታች ባለው እርከን ላይ ያሉት የወያኔ አመራሮችና ካድሬዎች እንዳሉ ነው ያሉት። አሰራራቸውም፣ አስተዳደራቸውም የቀድሞውን ስትራቴጂና ስልቶች ነው የሚከተለው። ለዚህም ነው የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች በመውሰድና ፖሊሲዎችን መቀየር ላይ መንቀራፈፍ የሚታየው።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሲያስቃይ፣ ሲያስር፣ ሲገድልና ሲዘርፍ ከነበር የህወሃት ድርጅት ጋር አብሮ እየሰሩ በምንም ተአምር የሰብአዊ መብት የተረጋገጠባት፣ ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ያለባት ሃገር መመስረት አይቻልም።

የቀድሞ ኢሃአዴጋዊ ታማኝነት፣ ጓዳዊነትና ድርጅታዊ አንድነትን ወደ ጎን ትቶ ከህወሃት ተላቆ ነጻ ኢኮኖሚና ሊብራል ዲሞክራሲ ወይም ሶሻል ዲሞክራሲን ከሚከተሉ ሃይሎች፣ ፓርቲዎችና ታዋቂ መሪዎች ጋር በመተባበር ለውጡን ከግቡ ማድረስ ነው የሚያዋጣቸው፣ ዶ/ር አብይን።

3) ዶ/ር አብይ ቁርተኛ የሆኑ ውሳኔዎች ለመውሰድ መዳዳት ያሳያሉ።

ዶ/ር አብይ ፍትህ ባጓደሉና አገሪቱን በዘረፉ የኢሃዴግ አመራሮች ላይ እርምጃ ለመውሰድ አቅደዋል፣ ሳፈጸሙም ዝግጅት አድርገዋል። ነገር ግን ተግባራቱን ለማስፈጸም ውሳኔ በመስጠት ላይ ድክመት እያሳዩ ነው። በተለይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችና አገር ወዳድ ግለሰቦችን ሲገርፍ፣ ሲያኮላሽ፣ የጅምላ ወሲብ ጥቃት ሲያስፈጽም፣ ግብረ ሰዶማዊ ጥቅት ሲያካሂድ፣ በአውሬ ሲያስበላ፣ እግርና እጅ ሲሳስቀርጥና ሌላም አሰቃቂ ወንጀል ሲፈጽም የነበረውን ጌታቸው አሰፋን ለህግ እንዲቀርብ ቁርጠኛ ውሳኔ አልሰጡም፣ ወይም ደግሞ ውሳኔው በማስፈጸም ሂደት ሌሎች ወገኖችን ላለማስከፋት ሲሉ ማፈግፈግ አሳይተዋል።

የኦነግ አመራሮች በሰላማዊ መንገድ አገር ገብተው በፖለቲካ ሂደት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋጸኦ ለማድረግ መንቀሳቀስ ቢጀምሩም ከጥቂት ወራቶች ወዲህ የያዝነውን የጦር መሳሪያ አንፈታም ሲሉ፣ በወለጋ፣ አሶሳ፣ ሞያሌ አካባቢዎች በሰላማዊው ህዝብ ላይ የሚያደርጉትን ግድያ እና ማሳደድ በዘላቂነት ለማስቆም ቁርጠኛ እርምጃ አልወሰዱም። ሁኔታዎችን ለማስታገስ አንዳንድ ውስኔዎችን አስተላልፈዋል ነገር ግን በኦነግ በኩል እየተፈጠረ ያለውን አሳሳቢ ሁኔታ ላንዴና ለማጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ሲዳዱ ይታሉ።

ዶ/ር አብይ የህወሃትና በኦነግ አመራሮች በለውጡ ሂደት ላይ እያደረጉት ያሉትን አሻጥሮችና አፍራሽ ተግባራትን ለማስቆም አፋጣኝ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ገራገር፣ ዳተኛና የተለሳለሱ ይመስላል።

ከላይ ለማስጠንቀቅ እንደተሞከረው የህወሃትና የኦነግ ቁንጮዎች በፖለቲካ ለውጡ፣ ፍትህንና የኢኮኖሚ ብልጽግና ለማምጣት በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ እየፈጠሩ ያሉትን ስጋቶች ለመቅረፍ አፋጣኝ እርምጃዎች መውሰድ ምንም አማራጭ የለውም።

ዶ/ር አብይ ይህንን እርምጃ በመውሰድ ረገድ ገራገርነትና መሳሳለስ እያሳዩ ከቀጠሉ ህዝቡ እስካሁን የመሰከረላቸውን የአመራር ብቃታቸው ላይ ጥርጣሬ እየገባው ይሄዳል። በአመራር ብቃታቸው ላይ ጥርጣሬው እየጎላ ከሄደም ለሻጥረኞቹ የቀድሞ ህወሃቶች አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል።

እርግጠኛ ነኝ ያ ከመሆኑ በፊት ዶ/ር አብይ በፈጣንና ቁርጠኛ አመራርና እርምጃዎች እንደሚቀድም እተማመናለሁ።

ለሳምንት በቸር ይግጠመን።

zelalemtek@yahoo.com

# መሪራስ...

ከገፅ 19 የዞረ

መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። በ1997 ዓ.ም ገደማ ከአማን በላይ ጋር መተዋወቅ እንደጀመርን በየጊዜው እየተደዋወልን ለረጅም ሰዓቶች በስልክ እናወራ ነበር። ለሀገሩ ሰው ያለውን ሁሉ ዕውቀት የማካፈል ምኞት ስለነበረው አብዛኛውን ጊዜ የሚናገረው እርሱ ነው። እጅግ ሰፊ ትንታኔና ሐተታ ማቅረብ ይችል ነበር።
በ1998 ዓ.ም ታትሞ የወጣውን "መጽሐፈ ሱባዔ ዘበአማን ካልዕ" እና የሰባ ቋንቋ መጽሐፍ ንድፉን ሲልክልኝ ወዲያውኑ የባለቤትነት መታወቂያ (Copyright) ክፍል ወስጄ በስሙ የባለቤትነት መታወቂያ ሰርተፍኬት እንዲደርሰው አደረግሁ። ሰርተፍኬቱ ሲደርሰው ደወለልኝና" የደረሰኝ ሰርተፍኬት ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀኝ።
"አንተ በየዋህነት የላክሃቸው የመጽሐፍ ንድፎች በቀላሉ ማንም ሰው ያንተን ስም ፍቆ የራሱን ስም ተክቶ የመጽሐፎቹ ደራሲ ነኝ ብሎ ማተምና መሸጥ ስለሚችል እኔንም ሆነ ማንንም ሰው እንዳታምን፣ በራስህ ስም የባለቤትነትህን ማረጋገጫ ሕጋዊ ሰነድ ሳትይዝ የጽሑፍህን ቅጂ ለማንም እንዳትልክ፣ እንዳታጋራ ለማስጠንቀቅ ያደረግሁት ነው" ብዬ ገለጥኩለት። ከዚህም በኋላ እንደሚያከብረኝ ደጋግሞ ገልጾልኛል።
አከታትዬም በጣም በረጃጅም ዓረፍተ ነገሮች የተነደፈውን ጽሑፉን በነጥብ ሥርዓት እያስተካከልኩ ለአንባቢ እንዳያሰለች ባጭር ባጭሩ እየከፋፈልኩ ሰርቼ መልሼ ላኩለትና ደስ አለው።
"የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ" በተሰኘው የመጀመሪያ መጽሐፉ ላይ የደራሲው ስም "ኤ. ኤም. በላይ" ተብሎ ለምን እንደቀረበ ላነሳሁለት ጥያቄ ሲመልስ በጥንቱ የነገድ ታሪክ ላይ መጽሐፍ የሚጽፍ ሰው ዕድሜው አጭር ነው ተብሎ ስለተነገረው እንደሆነና ማንነቱ እንዳይታወቅ ምህፃረ ቃል እንደተጠቀመ ገለጸልኝ። ማንነቱ እንዳይታወቅ ከፈራ አንድ ማህበር አቋቁመን በዚያ ማህበር ስም የሚጽፋቸውን መጻሕፍት ማሳተም እንደሚቻል ያቀረብኩለትን ሃሳብ ለጊዜው የተቀበለ መስሎ ችላ በማለት በስሙ መጠቀሙን ቀጠለ።
እውቀናችን እየጠበቀ ሲመጣም በአንድ ወቅት እርሱም እኔም ወደ ጎንደር የምንሄድበት አጋጣሚ ተፈጠረና እዚያው እንድንገናኝ ተቀጣጥረን ዓይን ለዓይን ለመገናኘት ችለናል። ቤተሰቦቹን አስተዋወቀኝ፤ እኔም ዘመዶቼን አስተዋወቅሁት። አንዱ ወንድሙ ጋር በተዋወቅንበት ወቅት የሀገር መድኃኒት አዋቂ ስለነበር የማከም ፈቃድ አውጥቶ እስከሐረር እየተጓዘ ያክም እንደነበር ነግሮኛል። የሀገር መድኃኒት ዝርዝር የያዘ የብራና መጽሐፍም አሳይቶኝ ነበር። ግን ብዙ ሳይቆይ ሳንባው ውሃ በመቋጠሩ በህክምና በመረዳት ላይ እንደነበረ አርፏል።
ከአማን በላይ ጋር ግንኙነታችን በስልክ በቀጠለበት ጊዜ እጅግ ከመቀራረባችን የተነሳ "ወንድሜ" ነበር የሚለኝ። በአንድ አጋጣሚ ጡረታ ስወጣ ጎንደር ከተማ አንድ ቤተ መጻሕፍት ከፍቼ አገልግሎት መስጠት እንደምመኝ ስላለኝ ሃሳብ ነግሬው "አንተ ይህን ያልከውን መጻሕፍት ቤት የምታቋቁም ከሆነ የምሰራበትን ዋናውን የብራና መጽሐፍ ላንተ ነው የምሰጥህ" ብሎኝ ነበር። በየጊዜው ስንደዋወልም ስለመጻሕፍት ቤቱ ጉዳይ ሳይጠይቅ አያልፍም ነበር።
አሁን ግን ይህ ሁሉ ነገር በተንጠልጠለ ቀረ።

# ከምርጫ ...

ከገፅ 12 የዞረ

የሚለውን ስራ ይጠይቃል፡፡ዝም ብሎ ምርጫው መራዘም አለበት የለበትም ማለት ተራ ወሬ ነው የሚሆነው፤በወሬ ደግሞ ምርጫ አይካሄድም፤ብጥብጥ ግን ይቻላል፡፡ እናም ህዝብን ለመራጭነት ማዘጋጀት እንደ ዘር ቅስቀሳው በሆያ ሆዬ የሚሰራ ሳይሆን የተመከረበት የታቀደ የአፈጻጸም ዝግጅት የተደረገበት ረዥምና ተከታታይ ስራ ይጠይቃል፡፡ ያለምንም ዝግጅት ምርጫ ምርጫ ማለት በመራጩ ህዝብ በመተማመን ሳሆን በየቦታው ያዘጋጁትንና የዘር ትጥቅ አስታጥቀው ጃስ ባሉት ቁጥር ድንጋይ የሚወረውርና ገጀራ ስሎ የሚነሳውን በጠቀም በምርጫ ተጭበርብሯል ስም ሁከት አስነስቶ በድርድር ሥልጣን መጋራት ይገኛል ብለው ለዚህ ተዘጋጅተው ከሆነ እነርሱ ከእነ አስተሳሰባቸው ባያረጁም ይሄ ስልት ግን አርጅቷል፡አያዋጣም፡፤

ሐ-በአስመራጭነት፤

ምርጫ ቦርድ በህገ መንግስት ድንጋጌ መሰረት ተቋቁሞ አመራሮቹ በፓርቲ የሚሾሙ ሆነው ለሾሙዋቸው ሰዎች አገልጋይ በመሆናቸው ተግባራቸውም ይህንኑ ስለሚያረጋግጥ ስናወግዝ ስንከስ ኖረናል፡፡ የሚገርመው ግን በአፍ ከማውራት እና በመግለጫ ከማውገዝ ውጪ የምርጫ ቦርድ ችግሮችን በማስረጃ ተንትኖ በጽሁፍ ያቀረበ ፓርቲ እኔ አላውቅም፡፡ አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ የምርጫ ቦርዱን ተግባራት ከተቋቋመባቸው የህገ መንግስቱና ሌሎች አዋጆች ጋር በማነጻጸር እንደ አቅምቲ ተከታታይ ጽሁፍ ለማቅረብ ሞክሬ ነበር፡፡ ሰሚ አላገኘሁም እንጂ፡፡ በነገራችን ላይ ምርጫ ቦርድ እንዳይጠናከር ተቃዋሚ ተብዬዎችም እንደማይፈልጉ ሰንቶቻችሁ ታውቁ ይሆን? ቦርዱ ተጠናክሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝጋባ አዋጅን ስራ ላይ ቢያውል አንድም ፓርቲ ባለበት መልኩ መቀጠል አይችልም፡፡

ነገርን ነገር ያነሳዋል ሆኖ ከመስመር ወጣሁ መሰል፤እዚህ ላይ ለማንሳት የፈለኩት ምርጫ ቦርድ አስመራጮችን በማግኘት በኩል ችግር እንዳለበት ለማሳየት ነው፡፡ የመጀመሪያው ነገር ገለልተኛ ሊባሉ የሚችሉ የህሊናቸው ጌቶች ናቸው ተብለው በብዙዎች አመኔታ የሚሰጣቸው ሰዎች እዚህ ቦታ መስራት አይፈልጉም፡፡ ተአማኒ ምርጫ እንዲኖር ግን ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ በእስከዛሬው ሁኔታ ወያኔ በግልጽ የማይታወቁ ሰዎቹን በአስመራጭነት ለማስቀመጥ ምቹ ሁኔታ ሲፈጥርለት ነበር፡፡ ተቀዋሚ ተብዬዎቹ ደግሞ በዚህ ረገድ ምን መሆን እንዳለበት እንደሚችልም በተግባር ማገዝ አይደለም ሀሳብ አይሰጡም ፡፡እነርሱ የሚያውቁት ምርጫ ቦርድ ነጻ አይደለም የሚለውን ጩኸት ብቻ ነው፡፡ እስከ አሁን ለፖለቲካው በአለኝ ቅርበት ኢዴፓ አማራጭ የምርጫ ህግ አዘጋጅቶ አቅርቦ ምርጫ ቦርድ ለዚህ ምላሽ በመጽሀፍ መልክ አዘጋጅቶ ማሰራጨቱን አውቃለሁ፡፡ ሌሎቹ በራሳቸው መስራቱ ቢቀር ኢዴፓ በሰራው ላይ እንኳን አስተያየት አልሰጡም መደገፍም አልፈለጉም ፡፡

ስለሆነም በአስመራጭ ምደባም በሉት ስየማ ላይ ህዝቡ ቀጥተኛ ንቁ ተሳትፎ ካላደረገ ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አንስቶ የሚመደቡትን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ አስመራጮች በጠራ እንኳን ባይቻል በተሻለ ሁኔታ ማስቀመጥ አዳጋች ነው፡፡ ይህ ስራ ቴሌቭዥን ጣቢያ ተግኝቶ ወይንም ከቢሮ ተቀምጦ እንደመናገር ቀላል አይደለም፡፡ መቼም እኛ ተወዳድረን ማሸነፍ አንችልም እንደሆነ ሆኖ ምርጫው ይካሂድና የምናውቅበትን የምንችለውን እናደርጋለን ተብሎ ሴራ ተሲሮ ካልሆነ በስተቀር፡፡

መ-በታዛቢነት-

የተወዳዳሪዎች አንዱ ፈተና ይህ ነው፡፡ በረዥም ግዜ ስራ ያላዘጋጁትን ሰው ምርጫው ወራት ሲቀሩት ታዛቢ ፍለጋ መንደፋደፍ ይጀምራሉ፡፡ አሳዛኙ ነገር ከእንቅልፋቸው ተነስተው ለይስሙላ አልያም የለመዱት እንዳይቀር አለያም ምርጫ ካልተሳተፍን እንሰረዛለን በሚል ተልካሻ ምክንያት የገቡበትን ምርጫ፤በአብዛኛው የድምጽ መስጫ ጣቢያ ታዛቢ ሳያቀምጡ ተጭበርብሯል ለማለት የማይሰንፉ መሆናቸው ነው፡፡ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውሎ ማስረጃ ቀርቶ መረጃ ሳይኖራቸው (ምክንያት ታዛቢ የላቸውምና) ከምን ተነስተው ምርጫው ተጭበርብሯል እንደሚሉ የሚያውቁት እነርሱ ናቸው፡፡ በምርጫ 2002 ማለዳ ላይ ምርጫው ተጭበርብሯል ብለው ቀትር ላይ ይቅርታ የጠየቁ የፖለቲካ ፓርቲ መሪንም እናስታውሳለን፡፡ ይህን አስነዋሪ ተግባር ፈጽመው እርሳቸውም አለቀቁ ፓርቲ ተብየውም አላወረዳቸው በሥልጣናቸው ቀጠሉ፡፡ ከላይ የጠቀስኩዋቸውና መሰል ተግባራት ሲፈጸሙ ጀሌው እየተቀባበለ ያስተጋባል፡፡ ሌላውም አይጠይቅ፡፡ ደፍሮ የሚጠይቅ ከተገኘ ደግሞ በእርዳ ተራዳ ወያኔ የሚለው የፍረጃ ናዳ ይወርድበታል፡፡ እነዚህ ሁሉ የደካማነትና የስንፍና መሸፈኛ ሰበቦች ግን በቀጣዩ ምርጫ የሚሰሩ አይመስለኝም፡፡ ፖለቲከኞቹ ቢነግሩሽ አትስሚ ቢመክሩሽ አትስሚ እንደ ተርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ የሚባልላው ቢሆኑም ህዝብ ነቅቷል ዘመንም ተለውጧል፡፡

ስለሆነም ህዝቡ በየአካባቢው ከላይ በጠቀስኳቸው ወሳኝ ጉዳዮች በባለቤትነት እንዲሳተፍ የማድረግ ስራ በተለይ ዛሬ ቀላል አይደለም፡፡ ያለ ህዝብ ንቁ ተሳትፎ የሚካሄድ ምርጫ ደግሞ ከቀደሙት ሊለይ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ያየናትን የዴሞክራሲ ጭልንጭል ጨርሶ ሊያጠፋና ሊያጨልምብን ስለሚችል ሆይ ሆይታ ፈጣሪዎቹን አደብ ግዙ ማለት ተገቢ ይሆናል፡፡ አስተውሎ መራመድ ካሰቡበት ያደርሳል የሚለው ብሂል ለዚህኛው ወገን በእጅጉ ታሳቢ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ኢትዮጵያ ትበታተን ሲሉን የኖሩ በጀመሩት መንገድ መበተኑ አልሳካላቸው ቢልም ህልም ቅዠታቸው ከውስጣቸው አልተነነምና ምርጫን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገሪያ ማድረግን ሳሆይን የዘመናት ቅዠታቸውን ማሳኪያ ለማድረግ አያስቡም ማለተ ሞኝነት ይሆንል፡፡ እናም በልብ አማላዩ ምርጫ ዲስኩር ተታለህ የሴረኞች ተባባሪ እንዳትሆን ወገኔ አስተውል፡፡

# ህገ መንግስቱ...

ከገፅ 13 የዞረ

በጣም ግራ የሚያጋባ ነዉ፡፡ ከህውሃት ጋር ነብስና ስጋችን የተወሀደ ነዉ ብሎ ህልቆ ሰራዊተ ህዝብ በሰልፍ ያለ ተቃዉሞ ድጋፉን ለሌቦቹ ሲሰጥ፡፡ የህውሃት ምሁራን ተሰብስብዉ ሂትለር እንዳደረገዉ አገር ማመስ ይቻላል ብለዉ አገራችን ላይ ሲያደቡ፤ ሲያቅራሩ፡፡ የዛሬ ሳምንት አማራን ልኩን እናሳየዋለን ሲሉ አሁን ደግሞ ተገልብጠዉ በአማራና በትግሬ ህዝብ መሀል ያለዉን ጥላቻ ለማርገብ የመቀሌ ምሁራን የተሰበሰቡት የትኛዉን አማራ ለማሞኘት ነዉ? ማስተዋላቸዉ በግፋቸዉ ብዛት ሳይሰረቅ አለቀረም፡፡ እነዚህን ሰዎች የሚነዳቸዉ ምንድነዉ? ጫት ነዉ እንዳይባል ትግራይ ዉስጥ ጫት በህግ እንዳይገባ መከልከሉን ሰምተናል፡፡ አማራን ግን ጤፍህን ወዲያ ብለህ ጫት አምርት ብለዉት ወጣቱ ጫታም ሆኖላቸዋል፡፡ ፡፡

የሰሞኑን የሰብአዊ ጥሰትና ዘረፋን የተመለከተ ሰብአዊ ፍጡር የህውሃት ሌቦችና ነብሰ ገዳዮችን ለመከላከል እንዴት ይደፍራል? ባለፈዉ እንዳሳሰብነዉ ለህውሃት በጀት ደሞዝና ሌላዉን በተመለከተ ከማእከላዊ መንግስት የሚላክ ይመስለኛል፡፡ የዶ/ር አብይ መንግስት እነዚህ አለም ላይ ታይቶ በማይታወቅ አይነት በዜጎች ላይ አስከፊ አካላዊ/ወሲባዊ/መንፈሳዊ ወንጀል አድርሰዉ መቀሌ መደበቃቸዉን እያወቀ በዝምታ ማለፉ አግባብ እንዳልሆነ ሳይረዳዉ አይቀርም፡፡ ሆኖም ያለበትን ችግር ግን የሚያዉቀዉ እሱ ብቻ ነዉ፡፡ ሊከላከላቸዉም ፈልጎ እንዳልሆነ ጠቋሚዎች ይታያሉ፡፡ ይህ ወንጀል በጸባዩ አለማቀፋዊ በመሆኑ አቅም ካነሰዉ አለም አቀፍ ተቋማትንና የኢትዮጵያን ህዝብ እርዳታ ጠይቆ እነዚህን ወንጀለኞች አባሮ መያዝ አማራጭ የሌለዉ አማራጭ ነዉ፡፡ እነዚህ ወንጀለኞች ታድነዉ ለፍርድ ካልቀረቡ ለትግራይ ህዝብም ጤና አይሰጡትም፡፡ በደል የደረሰበትም ዜጋም ፍትህን አያገኝም፡፡ የፋይናንስ ካሳን በተመለከተ በህውሃት በሚተዳደረዉ ሜቴክ፤ኤፈርት፤ ወደ ቤተሰብ ተላልፎ በሚተዳደረዉ ንብረትና ድርጅት፤ ወደ ዉጭ ተሻግሮ በተለያዩ አገሮች የተቀመጠዉ የትግሬ ማፊያ ንብረትና ሀብት ወደ ሀገር ገብቶ ለአካልና ለሞራል ጉዳተኞች እንዲሰጥ እያሳሰብን እነ ፕሮፌሰር መስፍን ይህን ሁሉ ጉድ ካዩ በኃላ አሁንም ህውሃት ማፊያ ንብረት ወደ መቀሌ ሺፍታ ይሸጋገር የሚለዉን ምልከታቸዉን እንዲተዉን እንጠይቃለን፡፡

ከዚህ ተያይዞ በቅርቡ ሮይተርስ እንደዘገበዉ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሀል በተደረገዉ ስምምነት የኢትዮጵያ ጦር ከቦታዉ በመልቀቁ ህውሃት ሆን ብሎ ካልተተናኮለ በዛ በኩል ችግር ባለመኖሩ በከፍተኛ ወጭ ተገዝተዉ ህውሃቶች ለማስፈራሪያነትና ለሽብር የሚጠቀምበት የኢትዮጵያ መከላከያ መሳሪያዎች ተቆጥረዉ ወደ ብሄራዊ የመሳሪያ ግምጃ ቤት እንዲተላለፉ እንዲደረግ እንደ ዜጋ እናሳስባለን፡፡ ያንን አልመልስም ካሉ የክልሉ መንግስት በማእከላዊ መንግስትና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ መሸፈቱ ስለሆነ የማእከላዊ መንግስትና የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረቱን ለማስመለስና ድምበሩን ለማረጋጋት መደረግ ያለበትን ያደረጋል የሚል ጽኑ እምነት አለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር semere.alemu@yahoo.com

# ኦነግ...

ከገፅ 3 የዞረ

ገልፀዋል፡፡ እኚህ አስተያየት ሰጪ ‹‹ኦነግ በኦሮሞ ልብ ዉስጥ ስላለ እኛን መንካት የኦሮሞን ህዝብ እንደመንካት ስለሚቆጠር መንግስት ምንም አያመጣም የሚል አስተሳሰብ እነ ዳወድ ኢብሳ ጋር ሳይኖር አይቀርም፡፡ ይህ ደግሞ አጉል መታበይ ነዉ፡፡ ተወደደም ተጠላ አሁን በሀገሪቱ እየሆነ ያለዉ ነገር የመጣዉ ከኦሮሞ አብራክ በወጡት በእነ አብይ አህመድና በሌሎችም ለዉጥ ፈላጊ ኢትዮጵያዊያን ነዉ፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ይህን በደንብ ጠንቅቆ ያዉቃል፡፡ ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እንደ መንፈስ የሚተይ ድርጅት ቢሆንም ላለፉት ሰላሳና አርባ ዓመታት ታግሎ ያመጣዉ ዉጤት የሚሰፈር አይደለም›› ሲሉ ፖለቲከኛዉ አክለዋል፡፡

እኚህ ፖለቲከኛ ሀሳባቸዉን ሲቀጥሉ ‹‹የዳወድ ኢብሳ ኦነግ አሁን እያራመደዉ ያለዉ ፖለቲካ እራስን የማጥፊያ ፖለቲካ ነዉ፡፡ በአብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ ቅቡልነት ያለዉን የወቅቱን መንግስት (ያዉም አበባ ሰጥቶ ወደ ከተማ ያስገባን አካል) በነፍጥ አንበርክኬዉ በስልጣን ወንበር ላይ እቀመጣለሁ ብሎ ማሰብ ራስን አለመግዛት ብቻ ሳይሆን ራስን ማጥፋት ነዉ፡ ፡ የዶ/ር አብይ መንግስት ኦነግን ወደ ሀገር ቤት ባስገባበት መንገድ ላይ የራሱ ችግር ቢኖርበትም ኦነግ ሰላማዊ ትግልን ከመሳሪያ ጋር የሚልበት ፍልስፍናዉ በአለም ላይ የሌለ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የዳወድ ኢብሳ የፖለቲካ ብስለት ጥያቄ ዉስጥ ይገባል›› ብለዋል፡፡

አፈንዲ ሙተቂ የተባሉ ፀሃፊ ደግሞ ለኦሮሞ ነፃነት ግንባር እና ለደጋፊዎቹ በፃፉት መልዕክት‹‹ ኦነግ ለኦሮሞ ህዝብ ነፃነትና መብት ለአርባ አምስት ዓመት በፅናት የታገለዉ ለዚህ አልነበረም፡፡ እኛ ኦነግ የኦሮሞ ብሔርተኝነት አባት ነዉ ብለን ስንከራከርለት የነበረዉ አባቶቻችን የመሰረቱትና የታገሉበት ግንባር በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ ትግልን በሚጎዳ ተግባር ላይ ይሰማራል ብለን ስለማንጠብቅ ጭምር ነዉ፡፡

‹‹እኔ አፈንዲ የኦነግ ጦር ትጥቁን ይፍታ የሚል ዘመቻ በሶሻል ሚዲያ ላይ በተከፈተበት ወቅት ለጦሩ ያለኝን ክብር ገልጩ ነበር፡ ፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሶሻል ሚዲያዉ የምናየዉ ነገር በጣም እያደናገረን ነዉ፡፡ በተለይ ወያኔ በፌስቡክ ላይ ያሰማራቸዉ ተላላኪዎች ኦነግንና መሪዉን ከልክ በላይ እያደነቁ የኦዴፓ መሪዎችን ሲወነጅሉ ማየት ብዙዎችን ለጥርጣሬ የሚጋብዝ ሆኗል›› ሲሉ ፅፈዋል፡፡

### የኦነግና የህወሃት አጉል ፍቅር

ከላይ በአፈንዲ ጠቆም እንደተደረገዉ በዚህ ጊዜ ኦነግና ህወሃት ጀምረዉታል የተባለዉ ወዳጅነትን ነዉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ቀደም ብለዉ ለአሃድ አስተያየታቸዉን የሰጡት የኦሮሞ ድርጅት አመራር‹‹ እዉነት በዚህ ወቅት ኦነግ ከህወሃት ጋር የወዳጅነት ወይም የአብሮነት እንቅስቃሴ እያደረገ ከሆነ ይሄም በራሱ ድርጅቱ እራሱን የሚያጠፋበት ሌላዉ መንገድ ነዉ፡፡

‹‹ባለፉት 27 ዓመታት ህወሃት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የፈፀመዉ ግፍ ተነግሮና ተፅፎ አያልቅም፡ ፡ ይህ እዉነታ ባለበት ኦነግ በኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ሲገፉ ህወሃትን እንደመደገፊያ አስቦ ወይም እንደ እስትራቴጂ ወስዶ ከተጠጋ ለኦሮሞ ህዝብ ያለዉን ህሳቤ እንዲመረመር ያስገድዳል፡፡

‹‹የኦሮሞ ህዝብ ሲያስረዉ፣ሲገድለዉ፣ሲጨፈጭፈዉ በነበረዉ በአረመኔዉ ህወሃት በኩል የሚመጣን ለዉጥ (ሲጀመር አይመጣም) አይፈልግም፡ ፡ ይህ በኦሮሞ ተወላጆች ነፍስ ላይ ቁማር እንደመጫወት ይቆጠራል፡፡ ኦነግ ትግሉን ያቀላጥፍልኛል ብሎ ከህወሃት ጉያ ዉስጥ ከተሸሸገ የከሰረ ድርጅት ስለመሆኑም ለኦሮሞ ህዝብ በግልፅ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡ ከከሰረ ድርጅት ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ዉጤት አይጠብቅም›› ብለዋል፡፡

ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን በበኩሉ ‹‹ለህወሃት ኦነግ በጥሩ ጊዜ ላይ የተመዘዘ ካርድ ሆኖለታል፡፡ መቀሌ ላይ ፍራሽ ጎዝጉዘዉ ለቅሶ የተቀመጡት የህወሃት መሪዎች በኦነግ የሰሞኑ ፌጥ ፌጥ ማለት ተፅናንተዉ የከዳቸዉ ወዝ ለጊዜዉም ቢሆን ተመልሶላቸዋል፡፡ የኦነግ እምቡር እምቡር ማለት ለህወሃቶች ሰርግና ምላሽ ነዉ፡፡

‹‹ሰሞኑን የኦነግ ጉዳይ ለህወሃቶች ቀዳሚ ጉዳይ ሆኖ እየተራገበ ነዉ፡፡ በኦሮሞ ስም ሰልፍ እስከመጥራትም ደርሰዋል፡ ፡ አጋጣሚዉ እንዳያመልጣቸዉ በሚችሉት ሁሉ እየተፍጨረጨሩ ናቸዉ፡፡ የኦዴፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ፅ/ቤት ሀላፊ እንደተናገሩት በኦነግ ዉስጥ የትግራይ ተወላጅ ወታደሮች ተሰልፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኦነግና የህወሃት ያልተቀደሰ ጋብቻ የትም አይደርስም›› ብሏል፡፡

ሰሞኑን እየተሰራጩ ባሉት መረጃዎች መሰረት መንግስት ሳወጣዉ የእርምጃ እወስዳለሁ የማስጠንቀቂያ መግለጫ የኦነግ መሪ አቶ ዳወድ ኢብሳም ሰራዊታቸዉን የመከላከል ዉጊያ አድርጉ ብለዉ ለማዘዝ ወኔ ያገኙት በህወሃት አይዞህ መባላቸዉን ተከትሎ ነዉ እየተባለ ነዉ፡፡ አቶ ዳወድ የሚመሩት ኦነግ ለጊዜዉ አጋር አገኘሁ ብሎ ከህወሃት ጋር ሽር ብትን ቢልም የሚያጋጥመዉ ኪሳራ ተደራራቢ እንደሚሆን እየተገለፀ ነዉ፡፡

ሲጀመር ኦነግ በዚህ ጊዜ ወዳጅ ያደረገዉ ህወሃት ከሞት መቃብር ላይ ቆሞ እያጣጣረ ያለ ድርጅት መሆኑ ፣ድርጅቱ ለራሱ ጥቅም እንጂ ለኦነግ አስቦ ያደረገዉ አለመሆኑ ኦነግን በብዙ መልኩ ተጎጂ ወይም ሰለባ ያደርገዋል እየተባለ ነዉ፡፡ ሌላዉና ኦነግ በደንብ ያልመረመረዉ ጉዳይ የህወሃት እጅ በኦሮሞ ተወላጆች ደም የጨቀየ መሆኑን ነዉ፡፡ ታዲያ ከዚህ ግፈኛ ድርጅት ጋር በኦሮሞ ልብ ዉስጥ ያለዉ ኦነግ ወዳጅነት የመመስረት ሞራሉን ከየት አገኘዉ? ብለዉም የሚጠይቁ አሉ፡፡

ዘላለማዊ ወዳጅ፣ ወይም ዘላለማዊ ጠላት የሚባል ፖለቲካን ብዙ የሆነን ህዝብ ወደ ጎን አስቀምጦ (ቁማር መጫወት) ይቻላል ወይ? በሚል ለአቶ ዳወድ ኦነግ ወሳኝ (ክሪቲካል) የሆነ ጥያቄ እየቀረበለት ነዉ፡፡

# አጀንዳህን...

ከገፅ 15 የዞረ

የሚረዱ ታሪካዊ ተሞክሮዎች በሀይማኖት አስተምህሮዎች ውስጥ አሉና በራስ መተማመን ስሜት ኢትዮጵያዬ እንቺ በላት፡ ፡ መቼም በኢትዮጵያ ቀርቶ በአጠቃላይ ህግ በሚባለው የትምህርት መስክ ሀይማኖት ከህግ ምንጮች ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ እንደውም የዘመናዊ ፖለቲካ ፅንስ ሀሳብ የዳበረው ሃይማኖታዊ ቀኖናዎች በየዘመኑ እየተሻሻሉ እና ተሃድሶ እያደረጉ ነው፡፡ ሴኩላር ተብለው ከምንተዳደርባቸው ህግጋትና ፖሊሲዎች ምን ያክሉ ምንጫቸው ሃይማኖታዊ እንደሆነ ለማወቅ የሮማን ታሪክ ማወቅ ይጠቅምሀል፡፡ ‹‹History of Political Thought››ን ስታነብ ይገለፅልሀል፡፡

እነዋበር ምን እንደሰሩ ታውቃለህ... ሃይማኖት እና ማህበራዊ ቲዎሪ (ሶሻል ቲዎሪ) ያላቸውን ዝምድና አጥንተው እኮ ነው ፖለቲካውን በሃይማኖት መዝሀብ በነፃነት የሚበተንበትን መንገድ የጠረጉት፡፡ እንደውም ዌበር የዓለም ሃይማቶችን ሲያጠና እስልምናን አቅዶ ሳይተገብረው ቀረ፡፡ ምናልባት ‹‹The protestant Ethics›› ብሎ እንደፃፈው ‹‹The Muslim Ethics›› ብሎ ፅፎ ይህን ጉዳይ እስከ ዛሬ እንዳይዘገይ ባደረገው ነበር፡፡ አንተ ግን ሰው የለህም ይሁን የሚሰራልህ፡፡


የዚህ ሁሉ ሐተታ መልዕክቱ ሰዎች ሲኖሩ ለእምነታቸውም ለአገራቸውም እየኖሩ እንደሆነ አምነውበት እንዲኖሩ ማድረግ፣ ሲሰሩም ለእምነታቸውም ለአገራቸውም እየሰሩ እንደሆነ አምነውበት እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡፡ የራስ መተማመን ስልጠና ‹‹ሀሁ›› ነው፡፡ ‹‹ሃይማኖት ሀገር የለውምና ድንበር አታበጅለት›› ብለህ ለመከራከር ያሰብክ ካለህ ደግሞ ‹‹የሃይማኖት ድንበር የለሽነት››ን እንደማውቅ አስታውሼህ ‹‹ነገር ግን ሳለህበት ድንበር እንዴት እንደሚሰራ ካላሳየኸን እንዴትስ ትውልድ የመቅረፁን ኃላፊነት በቸልታ ሳንተ እንተውዋለን?›› ስል በጥያቄ እመልስልሃለሁ፡፡ በእኛው ሀገር እንኳን አታይም እንዴ የፕሮቴስታንት ወንድሞቻችን አቋም!?

ልብ አድርግልኝ... እኔ ‹‹በእምነት ስም አንድ ዓይነት የፖለቲካ አመለካከት ወይም አደረጃጀት ውስጥ ጓዝህን ጠቅልለህ ግባ›› አላልኩህም፡፡ ይልቁንም ‹‹ስለ እምነቱ ብለህ የምትሰራው እና ስለድርጅትህ የምትሰራው አይምታቱብህ›› እያልኩህ ነው፡፡ ለምንስ ይምታቱብሀል? ድርጅትህን ለድብቅ ዓላማ እየተጠቀምክ እንደሆነ ለምን ይሰማሃል?

አይ ያንተ ነገር...! ‹‹እንደዚያ እንዲሰማኝ ለማድረግ የሚሰሩ አሉ›› ልትለኝ ነው አይደል? ታዲያኮ ይህን ማወቅህ በጣም ይጠቅምሃል! እነሱ እንደሚፈልጉት ሙስሊሙ የሚያስባት ኢትዮጵያ እና ሙስሊሙ እድሜውን እና አቅሙን የሚጨርስላት ኢትዮጵያ የተለያየች ነች ብለህ ተስፋ እንዳትቆርጥ የምትፈልጋትን ኢትዮጵያ በምትኖርባት ኢትዮጵ

በምስጋናው ታደሰ Misganaw2000@yahoo.com

# የሰር አሌክስ ፈርጉሰን አብዮት በኦልድ ትራፎርድ ዳግም ይወለድ ይሆን?




የትኛውም አሰልጣኝ ወደ ልምምድ ሜዳ ከመግባቱ በፊት ሊያውቀው የሚገባ ሃቅ አለ፡፡ ሰር አሌክስ ፈርጉሰን ከየትኛውም ነገር በፊት የተረዱት ይህንን ነው፡፡ የባለቅኔው ጆን ዶን “No man is an island” (ማንም ሰው ደሴት አይደለም) የሚለው ስራ ለብዙ ነገር መሰረት ሆኗቸዋል፡፡ የትኛውም ሰው ከዓለም ተነጥሎ አይኖርም፡፡ ሁሉም ሰው የሌሎች ውጤት ነው፡፡ በባህሪያችን ላይ ትልቁን ተጽዕኖ የሚያሳርፉት በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ናቸው፡፡

ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ሰንሰለት ነው፡፡ በተያያዙት ቀለበቶች ውስጥ ‹‹የላላ›› ቀለበት ካለ ሰንሰለቱ ይበጠሳል ፡፡ በፈርጉሰን ቡድን እንደዚያ ያሉ ደካማ ጎኖች እምብዛም ያልነበሩት ለዚያ ነው ፡፡ ከስንት አንድ ጊዜ እንደዚያ ዓይነት አጋጣሚዎች ሲከሰቱ ወዲያውኑ ይጠጋግኗቸዋል፡፡ መመከር ያለባቸውን ይመክራሉ፡፡ መገሰጽ የሚኖርባቸውን ይገስጻሉ፡፡

በጆዜ ሞውሪንሆ የአሰልጣኝነት ዘመን አሰልጣኙ በዋናነት ይወቀሱ የነበረው በፖል ፖግባ አቋም መውረድ እና ባህሪይ ነበር፡፡ ፈረንሳዊው ከዓለማችን ምርጥ አማካዮች አንዱ መሆኑ ይነገርለታል፡፡ የሚመቸውን ሲስተም ሲያገኝ ችሎታው ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም፡፡ ጎሎችን ያስቆጥራል፡፡ ጎል የሆኑ ኳሶችን አመቻችቶ ያቀብላል፡፡ ከቡድን ጓደኞቹ ጋር ድንቅ ጥምረት ይፈጥራል፡፡

ልጅነት የሚያጠቃው እና ልታይ ልታይ ባይነቱ ግን ለጥያቄ አይቀርብም፡፡ የሚዲያውን ትኩረት ለማግኘት የማይፈነቅለው ድንጋይ አለመኖሩንም አሳይቷል፡፡ ከሜዳ ውጪ በሚፈጠሩ ክስተቶች መወሰዱም የተለመደ ነገር ነው፡፡ ጥሩ ከባቢ ሲፈጠርለት ግን በተቃራኒው የዓለም ምርጡ አማካይ ይሆናል ፡፡

በፈርጉሰን ዘመንም እንዲህ ዓይነት ተጫዋቾች ነበሩ፡፡ ተሰጥኦዋቸው ለጥያቄ የማይቀርብ ነገር ግን በፋሽኑ ኢንዱስትሪ ትኩረት የሚሰጣቸው፡፡ ነገር ግን ከፖግባ በተሻለ በትጋታቸው የሚታወቁ፡፡ ዴቪድ ቤካም እና ክሪስቲያኖ ሮናልዶ ከእነዚህኞቹ ተርታ ይሰለፋሉ፡፡ ልታይ ልታይ ማለትን ይወዱ ነበር፡፡ ነገር ግን በቡድን ስራ አይታሙም ነበር፡፡

ፈርጉሰን ከክለብ የሚበልጥ ተጫዋች አለመኖሩን ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን ተጽዕኖ እና ተዋረድ ቦታ ነበራቸው፡፡ ተጫዋቾች የሚያከብሯቸው እና የሚታዘዟቸው ተጫዋቾች በቡድኑ ውስጥ እንዲኖሩ ይሹ ነበር፡፡

በፈርጉሰን ዘመን ከነበሩ በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ማሳረፍ ከሚችሉ ተጫዋቾች መካከል ሮይ ኪን እና ፖል ስኮልስ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ተጫዋቾች በቡድኑ ውስጥ ላሉ ሌሎች ተጫዋቾችን መመሪያ ይሰጣሉ እንጂ አይቀበሉም፡፡ አቅጣጫ ያሳያሉ እንጂ አይመሩም፡፡

ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን አንድ አጋጣሚ ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡ በአንድ ወቅት በፈርጉሰን ዘመን ተጫዋቾች ወደ ልምምድ ሜዳ ሲገቡ ኪዬረን ሪቻርድሰን በመኪናው ውስጥ ሙዚቃ እስከ ጣሪያ ድረስ በልቅጦ መኪናውን በክለቡ የመኪና ማቆሚያ አቁሞ ወደ ልምምድ ሲገባ ሲሞክር ከሮይ ኪን ቀጭን ትዕዛዝ ደረሰው፡፡ መኪናህን አስነስተህ ቀጥ ብለህ ወደ ቤትህ ተመለስ የሚል፡፡ ሪቻርድሰን አላንገራገረም፡፡ እንደተባለው አደረገ፡፡ ምክንያቱም በፈርጉሰን ቡድን ተዋረድ አለ፡፡

የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር ዳሚየን ሂውዝ የቀድሞውን የማንቸስተር ዩናይትደ አምበል ሮይ ኪን ‹‹cultural architect (የስነምግባር ደልዳይ)›› ብለው የጠሩት ለዚያ ነው፡፡ እንደእነዚህ ዓይነት ተጫዋቾች ለሌሎች ተጫዋቾች አርዓያ ናቸው፡፡ እነርሱ የሚሰሩትን ሌሎች እንዲከተሉ የማድረግ አንዳች አቅም አላቸው፡፡

የእግር ኳስ ክለብ የማህበረሰቡ ግልባጭ ነውና የችሎታ እና ስልጣን ተዋረድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ፈርጉሰን የተገነዘቡት ሌላኛው ዕውነት ይሄ ነበር፡፡ ዕውቀቱን የገበዩት ግን ወደ እግር ኳሱ ዓለም ከመቀላቀላቸው በፊት በወደብ ላይ በሚሰረቡት ወቅት ነበር፡፡

የሚከበር እና ትዕዛዙ የሚከበርለት ሰው ከሌለ ምንም እንደማይሰራ ያን ጊዜ ከተመለከቱት ነገር ተገንዝበዋል፡፡ በወቅቱ ሰራተኞችን የሚቆጣጠሩ ‹‹ካቦዎች›› ከአካባቢው ዞር ሲሉ ሰራተኛው ጥግ ጥጉን ይዞ ሲያሾፍ እና እነርሱ ሲመለሱ ተፍ ተፍ ይሉ እንደነበር ተመልክተዋል፡፡ ይህንን እውነታ እርሳቸው ወደ ቡድኖች አመጡት፡፡

ፔፕ ጋርዲዮላም ይህንን ዘዴ በባርሴሎና ተግብሮታል፡፡ ያንን ያደረገው የተወሰኑ ‹‹cultural architect›› በመለየት ነበር፡፡ ዣቪ ሄርናንዴዝ፣ አንድሬስ ኢኒዬሽታ እና ሊዮኔል

ወደ ገፅ 27 ዞሯል